## ምዕራፍ 2

## የካሣ ኃይሉ እድገት

ለምጩን መጽሔት መስከር 1991 ዓም ገጽ 15 "ከማለዳ ልደታቸው ጀምሮ ድል እየተቀዳጁ በሄዱበት ምሉዕ ጀግንነት በድል አድራጊነት ብቻ ሳይሆን ለዓላማቸው እስከመጨረሻው ታግለው በራሳቸው ላይ የወሰዱት ቆራጥ እርምጃ ይባስ አግንኗቸዋል" ሲል መጽሔቱ ጽፏል።

ካሣ ኃይሉ አባታቸው ስለሞቱባቸው ከእናታቸው ጋር ማደጋቸውን የተለያዩ ደራስያን ተስማምተውበታል። እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወይዘሮ አትጠገብ ቸንከር ተክለ ሃይማኖት ትምህርት ቤት እንዲማሩ አስገብተዋቸዋል። ቸንከር ተክለ ሃይማኖት የራስ አሊ ወታደሮች የጁዬዎች ቤተ ክርስቲያኑን ሆነ ተማሪውን ሲያጠቁ ካሣ ሩቅ ሁነው ይመለከቱ ስለነበር ጥቃት አልደረሰባቸውም።

ከዚህ በኋላ በጊዜው እንደ ዩንቨርስቲ ይቆጠር ወደ ነበረው ማኅበረ ሥላሴ ገዳም በመሄድ የጀመሩትን የቄስ ትምህርት ጠንክረው ተምረዋል። በተለይ በዚህ ገዳም ሊማሩ ከገቡ በኋላ ዝንባሌያቸው ከቅስና ትምህርት ላይ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ፍቅር አደረባቸው። ከገዳሙ ካሉት ከጥቂቶቹ እንጂ ከብዙኃኑ ጋር አልግባባ ብለዋል።

ምክንያቱም ወጣቱ ካሣ ብሩህ አእምሮ የነበራቸው በመሆናቸው የተነገራቸውን የማይዘነጉ ያነበቡትን የማይረሱ ከመሆናቸው በላይ ሸንበቆ ጠርቦ ቀለም አርጥቦ ቆዳ ፍቆ በብራና መጻፍ አይወዱም ነበር። ነገር ግን ሌሎች ተጨንቀውና ተጠበው የጻፉትን አንብበው እርማት ያደርጉ ነበር።

ካሳን በግል የሚያስተምሩአቸው ፈላሲ መነኩሴ የኢትዮጵያ ዳር ደንበር የተደፈረው በቱርኮች መሆኑን አስተምረዋቸል። በዚህ ወቅት የካሳ ትልቅ ወንድማቸው ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ቱርኮችን ለመውጋት ሲሄዱ ወደ ማኅበረ ሥላሴ ጎራ ብለው አባቶችን



እንዲጸልዩላቸው ሊማጸኑ ሲሄዱ ካሳ አብሬ መሄድ አለብኝ ብለው ተነሡ። ወንድማቸውም ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ አብረዋቸው እንዲሄዱ ፈቀዱ።

ወጣቱ ካሳም ደስ ብሉአቸው ከወንድማቸው ጋር አብረው ዘመቱ። በዚህ ጦርነት ካሣ ለመጀመሪያ ጊዜያቸው ቢሆንም ከፍተኛ ጀብድ ሠሩ። አንዳንዴ ወንድም ለወንድሙ ምቀኛ ነው እንደሚባለው ደጃዝማች ክንፉ በትንሽ ወንድማቸው የጦር ስልት መደሰት ሲገባቸው ቅናት አደረባቸው።

ከገዳሪፍ ደንቢያ ሲመለሱ ስለታቸውን ለማድረስ ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ወደ ማኅበረ ሥላሴ ሄዱ። ይህ እርኩስ መንፈስ ሰይጣን በአቤልና በቃየል መካከል ገብቶ እንዳስገደለው ሁሉ ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ልባቸውን ያስጨከነው ሰይጣን ገፋፋቸውና ከገዳሙ ዘግተው የተቀመጡትን ፈላሲ መነኩሴ "ማንኛው ልጄ ነው የኔን ሥልጣን የሚይዘው" ብለው ሲጠይቁ ያገኙት መልስ ግን ተቃራኒ ሆነ። ያም "ካንተ ልጆች መካከል የአንተን ሥልጣን የሚይዝ የለም። ነገር ግን ካሣ ይወስዳል" የሚል መልስ በማግኘታቸው ከማዘን አልፈው ተናደዱ። ይህን አስመልክቶ ከላይ ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ እንዲህ ይገልጹታል።

ስማቸው ያልታወቀው የቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉት ገጽ 4 "በኋላ አንድ መነኩሴ መጥቶ ለደጃች ክንፉ እንዲህ አላቸው። ልጅ ካሳ ሊገዛ ነው የርስዎ ልጆች ግን አይረቡም ብሉ ነገራቸው። ከዚያ ወዲያ ደጃች ክንፉ ቀንተው ካሳን ጠሉዋቸው" ሲሉ ሰፋ አድርገው ጽፈዋል።

ባሕሩ ዘውዴ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 25" የግብጽ ተስፋፊ ሠራዊትና የኢትዮጵያ ጠረፍ ገዥዎች ደንበር ላይ መጋጨት ጀመሩ። ይህን ባዲስ ጉልበት እየገፋ የመጣውን የግብጽ ኃይል ለማገድ በወልቃይት ደጃች ውቤ በደምቢያ ደጃች ክንፉ፣ ተሰለፉ። የክንፉ ወንድም (ባባት ወገን)የሆነው ካሣ ኃይሉም (የኋላው ቴዎድሮስ)ይህንኑ የድንበር ፍልሚያ ከወረሰ በኋላ ነው ጉልበቱም እየጠነከረ አጠቃላይ አመለካከቱም እየተለወጠ የመጣው"።

“ግብጾች ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ለመስፋፋት የሚያደርጉትን ጥረት በብርቱ ይፋለሙ ከነበሩት መሳፍንት አንዱ ደጃች ክንፉ ነበር። በ1829 ከልተቡ በተባለ ሥፍራ ግብጽ ጦር ላይ ትልቅ ድል በመጎናጸፉም በኢትዮጵያውያን ዘንድ ስመ ጥር ሆኖ ነበር። የአባቱ ልጅ ለሆነው ለካሣ ግን ብዙም ፍቅር አያሳየውም ነበር። የዚህም ምክንያት ክንፉ ካሣን የልጆቹ ጣውንት አድርጎ ስላየው ነው” ሲሉ ጽፈዋል።

ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም የተነገራቸውን ሰምተው የሆዳቸውን በሆዳቸው አድርገው ማኅ ቀመስ ደንቢያ ሲደርሱ ለዘመተውና እንኳን ደና መጡ ለማለት የተሰበሰበውን ሕዝብ ግብር በማብላት ላይ ሳሉ ካሣ በወራንታ ቁርጥ ሥጋ በመያዝ ያሳልፋሉ። በዚህ ወቅት ደጃዝማች ክንፉ ሲያዩአቸው ደማቸው ፈልቶ እየቆረጡ በሚበሉበት ካራ ወረወሩባቸው። ካራው ከካሣ ላይ ሳይሆን ያረፈው ከውራንታው ሥጋ ላይ በመሆኑ አላገኛቸውም። ከዚህ በኋላ ካሣ ሁሉን ትተው ወደ ጎጃም ደጃዝማች ጎሹ ዘንድ መሄዳቸው ተዘግቧል። ደራስያን ካሣ ከደንቢያ ወደ ጎጃም መሄዳቸውን ይስማማሉ።

በተለይ አቶ ገሪማ ታፈረ፥አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ መሪራስ ኤኤም አማን በላይና ሌሎችም ደራስያን ከደንቢያ ወደ ጎጃም መሄዳቸውን አሥምረውበታል። አንዳንዶች ካሣ በመጀመሪያ ሚስት ያገቡት ጎጃም ነው። የእርሳቸው ዘር ከጎንደር፤ከትግሬ ሽሬ፤ካለው ይበልጥ ጎጃም ነው የሚሉ አሉ። ወጣቱ ካሣ ጎጃም ከደጃዝማች ጎሹ ቤት አሽከር ሁነው መግባታቸው ታውቋል። ለምሳሌ ደብተራ ዘነብ ካሣ ጎጃም ሳሉ ደጃዝማች ጎሹ ከልጃቸው ከደጃዝማች ብሩ ጋር ሲዋጉ ወጣቱ ካሣ የደጃዝማች ጎሹ አሽከር ሁነው መዋጋታቸውን እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል።

<u>ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ያሳተመው ገጽ 5“ ደጃዝማች ጎሹም አንጋጣ ላይ ከልጃቸው ከብሩ ጋር በተዋጉ ጊዜ ልጅ ካሣ 1 ሰው ማርከው 2 ጦር ነቅለው ፈረሳቸውም ቆስሎ መጡ። ለደጃች ጎሹ በፈከሩ ጊዜ ፈረስና (ጃህ ለምድ ጃሐ) ለምድ ሰጡዋቸው” ሲሉ ጽፈዋል።



ከዚህ በኋላ ወጣቱ ካሣ በጎጃም ሳሉ ደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ መሞታቸውን በመስማታቸው በድንገት ወደ ጎንደር ተመለሱ። በዚህ ወቅት የደጃዝማች ክንፉ ልጆች ደጃዝማች ይልማ ክንፉና ደጃዝማች ጋረድ ክንፉ፤በአባታቸው ግዛት እኔ ይገባኛል እኔ ይገባኛል በመባባል ሲጨቃጨቁ ካሣ መጡ። ምንም እንኳን ካሣ በደጃዝማች ክንፉ ጭካኔ ከአገር የተሰደዱ መሆናቸው ባይካድም እርሳቸውም የወንድማቸውን ልጆች እንዲስማሙ ለማድረግ የነበራቸው ጥረት ሳይሳካ ቀረ። በዚያም ወቅት የደጃዝማች ክንፉ ልጆች ጦርነት በመግጠማቸው ካሣም ከክንዳቸው ላይ ቆሰሉ። ከቁስላቸው ገመም እንዳሉም ወደ ቋራ ወረዱ።

ቋራ እንደደረሱ የአባታቸው ባለሟሎች እነ አቶ ቢተዋ “የጌታችን ልጅ እንኳን ደኅና መጣህ”በማለት አቀባበል አደረጉላቸው። እነ አቶ ቢተዋም የቂስ ልጅ ዛሬ ድረስ ስሟ ያልታወቀች አጭተው አጋቧቸው። ቤትም ሠርተው ሰጡአቸው። ነገር ግን ካሣ ጎጆ ቀልሶ ቤት ሠርቶ መኖሩ አላስደሰታቸውም።

ያ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ሲማሩ በነበሩበት ወቅት ያስተማሯአቸው የኢትዮጵያ ዳር ደንበር መደፈር እንቅልፍ ይነሣቸው ጀመር። ከቤት ከማደር ይልቅ ከሽፍቶች ጋር ማደርና መማከር ሽፍቶች የሚለብሱትን መልበስና ሽፍቶችን ማጠናከር ጀመሩ። ሽፍቶች የድሃን ንብረት እንዳይበሉ ማስተማር አንዱ ተግባራቸው ሲሆን ሌላው ደግሞ ሽፍቶችን መክሮና አጠናክሮ ወደ ሱዳን እየገቡ ቱርኩን መግረፍና ነቅለው እንዲሄዱ ማድረግ ከነሱም የማረኩትን እያመጡ በንብረት መጠቀም እንደሆነ ማሰልጠን ተግባራቸው ሆነ።

Donald N.Levine <u>GREATER ETHIOPIA</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 84 “Ethiopia from the west by Egyptian forces under Muhmmad Ali.A young man named Kasa,a nephew of the chief of the frontier district raided by Muhammad Ali.s men in 1837 was roused by that event to mission to strngthen Ethiopia so it would not be vulnerable to such attacks.” ሲሉ ጽፈዋል።

አንዳንድ የውጭ ሆኑ የሀገር ተወላጆች ጸሐፊዎች “ከግብጽ ጦር ጋር ተዋጉ” እያሉ የጻፉት በዚህ ዘመን ግብጽን በበላይነት የሚያስተዳድሩት ቱርኮች ሲሆኑ ዘማቹ ወታደር የግብጽ በመሆኑ

እንጂ በዚያን ወቅት ግብጽ አቅም ኑሯት አልነበረም፡፡ በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት ከዛሬው ሱዳን ውስጥ ከደባዚን እስከ ከሰላ 42 ጊዜ የተደረገው ጦርነት ከቱርክ ጋር ነው፡፡ ወጣቱ ካሣ፣ በተደጋጋሚ ከቱርክ የማረኩትን ንብረት ሸፍቶች መሐላ አፍርሰው ለብቻቸው በመጠቀማቸው ካሣ በትንሽ ኃይል ደፍጥጠው ከሞት የተረፉት ሁለተኛ መሐላ እንዳያፈርሱ አስምለው አጠናከሩአቸው፡፡

ከዚህ በኋላማ ከሽፍትነቱ ይልቅ ፈር የያዘ አመራር ያለው ሠራዊት እንዲሆን ለማድረግ ሆዳሙንና ቀራጡን መለየት ተግባራቸው ሆነ፡፡ በመጀመሪያ 2 ጊዜ ጦርነት በከፍተኛ ጀብድ የተዋጉትን እንደ ጦር መሪ በማድረግ አጠናክረው 3ኛ ጊዜ ቱርክን ገዳሪፍ ላይ ደብድበው ሲመለሱ የአካባቢው ሕዝብ ልጅ ካሣ ይላቸው ጀመር፡፡ በተለይም ከጉምዝ ሕዝብ ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት ስለነበራቸው አንዱ ወዳጃቸውን "ጉምዝ እንዴት ነው" ሲሉት የሰጣቸው መልስ ይህን ይመስላል፡፡

"ካሣ ጉምዝ ይወልዳል
ጫቁ ይወስዳል፣
የጫቁ ነገር ጨንቋል"
በማለት ይመልስላቸዋል፡፡ የጉምዝን ሕፃናት ሽፍቶች እየሰረቁ ባሪያ አድርገው ይሸጡአቸው ስለነበር ነው፡፡

የካባ ሲሳይ አምባው <u>እግዚአብሔር አልረሳኝም የለመንኩትን አልነሳኝም</u> ያልታተመ
"ምኞቴ ኢትዮጵያ አገሬ ገብቼ
ደቡቡን ምሥራቅን ሰሜንን ጎብኝቼ
በምዕራብ ጀምሬ መሀሉን አይቼ
የአገሬ ሕዝብ በልቶና ጠጥቶ ተደስቶ አይቼ
ይህ ነው የእኔ ጸሎት ወጥቼ ገብቼ
የኢትዮጵያ ጠላት አልሞተም ከጥንቱ
አምላክ ይብቃ በላት ይዘጋ እንደበቱ፡፡"

"የቴዎድሮስ ዓይነት ሴቶች እንዲወልዱ፣
የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደዚያ ሲወዱ
ሕይወቱን ሰጠላት እንዳያፍር ትውልዱ
የሰው ልጅ መሆኑ ቀደም ተዘንግቶ



ሊሸጡ አወጡት እንደከብት ተነድቶ
ሰውን እንደ እንሰሳ ገበያ እያወጡ
እንኳንስ ሊያፍሩበት ወይ ሊደነግጡ
ሥራችን ነው ብለው ባርያ መለወጡ
መሳፍንት መኳንንት እንዲህ ሲቀናጡ
በቴዎድሮስ ሰይፍ ሁሉም ተቆረጡ" ሲሉ ጽፈዋል፡፡

ባሪያ ፈንጋዩ ሽፍታ ሁሉ ፀረ ካሣ ቅስቀሳ ቢያደርግ ካሣ ግን ሳይታሰቡ እየደረሱ ይገርፉት ጀመር፡፡ እጅና እግሩ ቅድሚያ የተቆረጠው የጫቁ ሕዝብ ሲሆን ባሪያ በማድረግ የጉምዝን ልጆች እየሰረቀ ወደ ቅማንቱና ወደ አርማጭሆ ይልክ ስለነበር ሲይዙት ሁለተኛ አታድርግ ብለው ያስምሉታል፡፡ መሐላው ደግሞ በቆላው ባህል መሠረት ጠበንጃ ተጋድሞ የሚምለው ሰው "ሁለተኛ ብደግም ይህ ጠበንጃ ይግደለኝ"እያለ ጠበንጃውን ይራመዳል፡፡ ይህን መሐላ አፍርሰው ጉምዝ ሲፈነግሉ የተያዙ በጥይት እየተጨፈጨፉ ተገደሉ፡፡

ካሣ በደም ማርከን ያመጣነውን ጥይት ከምናጠፋው የመሐላውን ቃል እንቀይረው በማለት መጥረቢያውን ከግንዱ ላይ አጋድመው ባሪያ ሲፈነግል የተያዘውን ሽፍታ "ሁለተኛ ብገኝ ይህ መጥረቢያ ይከትክተኝ"እያሉ እንዲምሉ አደረጉ፡፡ ከዚህ ወዲህ ባርያ ፈንጋይ ሽፍታ አልያዝም ካላለ በቀር ተይዞ ሲፈረድበት ጥይት ከማባከን በመጥረቢያ ከግንድ አስደግፈው ይቆርጡት ጀመር፡፡ የቆላው ሽፍታ መታረም ጀምሮ ቆራጡና ሆዳሙ ተለይቶ የቀረው መሠረታዊ የሆነውን ደንበሩን የማስጠበቁን ተግባር እንዲይዝ ከፍተኛ ቅስቀሳ ካሣ ማድረግ ጀመሩ፡፡

ከእርሳቸው ጋር አብረው ለነበሩ እንዳይራቡ ቀደም ሲል ከቱርክ ከተማረከው ንብረት በሥርዓት እንዲያዝ ሁኖ ቀለባቸው ይዘጋጅ ጀመር፡፡ ልጅ ካሣ ሸህ እንዲሪስ የተባሉም ወዳጅ ነበራቸው፡፡ ሸክ እንድሪስ ቱርኮች ከአፍሪካ ምድር መውጣት እንዳለባቸው ያምኑ የነበሩ ሲሆኑ ለካሣ እንደ ወንድምም ያዩአቸው ነበር፡፡ አንዴ በቋራ የህል ችግር ገብቶ በነበረበት ወቅት ለካሣ ሸክ እንዲርስ 200 ግመል እህል አስጭነው ላኩላቸው፡፡ ካሣም ሠራዊታቸውንና የቋራን ሕዝብ በችግር እንዳያልቅ በሥርዓት አከፋፈሉ፡፡

በዚህ ወቅት የልጅ ካሣ ዝና ይበልጥ በቋራና በደንቢያ አልፎም ጎጃም አገው ምድር ይሰማ ጀመር:: ካሣ ሠራዊታቸው ወደ አርሶ አደሩ ቤት እንዳይገባ መደረጉ ሕዝቡ እንዳይሰቀቅ ወዶ ቀለብ እንዲሰጣቸው እንጂ እንዳይዘርፉ በማደድረግ የቋራ ሕዝብ "ልጅ ካሣን ይወዳቸው ጀመር:: በዚህ ወቅት ደጃዝማች ዓለሜ ከቋራ ደጃዝማች ገልሞ ከጭልጋ ቅማንት÷ፊታውራሪ ገብርዬ ከጋይንት፤ ራስ እንግዳ ከጎጃም ተራ በተራ ወደ ልጅ ካሣ ሠፈር ገቡ::

## ምዕራፍ 3

## ልጅ ካሣ

የልጅ ካሣ ጀግንነትና ቆራጥነት ከኅብረተሰቡ አልፎ ጎንደር ግንብ ጠባቂ ለነበሩት 3ኛው አጤ ዮሐንስ ባለቤት ለእቴጌ መነንና ለልጃቸው ለራስ አሊ አሉላ ሰላም ይነሣቸው ጀመር:: መሳፍንቶች እንደካሣ ያለ ወንድ ብቅ ሲል ወደ መንደራቸው እንዲመጣ ሺህ መልእክተኛ ይልኩና ያስመጡታል:: ከመጣላቸው በኋላ ደግሞ ሞራሉን አድቅቀው ይለቁታል:: ይህን በማድረግ የተካኑት መሳፍንቶች ካሣን "ከማራቅ ማቅረቡ መልካም ነው የልጅ ልጃችን ተዋበች አሊን እንሰጠዋለንና ይምጣ"የሚል ውሳኔ ይደርሳሉ::

መልእክተኛው ቋራ ደርሶ ልጅ ካሣ ካሉበት ገብቶ ሲመለከት ባለትዳር ናቸው:: አፌን በጠጅ ብሎ የሰላም ውይይት ብቻ አድርጎ ወደ ጎንደር ተመለሰ:: ለእቴጌ መነን "ባለትዳር በመሆኑ ሳልናገር መጣሁ ነገር ግን ሰውየው መያዝ ያለበት ቆራጥ ጀግና ነው:: የታዘብኩት ጉዳይ ቢኖር በሕዝቡ ዘንድ እንደ ንጉሥ የሚታይ የተወደደ ወጣት ነው"በማለት ሲነግራቸው እቴጌ መነን ክፉኛ ተበሳጩ "ታዲያ ምን ይሻላል" ሲሉ ሌላው ሚስቱን እንዲፈታ ማድረግና በአማችነት መያዙ አማራጭ የለውም በማለቱ ያው መልክተኛ ቋራ ተመለሰ::

መልእክተኛው ቋራ ደረሰ:: በተነገረው መሠረት ቀጥታ ለልጅ ካሣ ከመንገሩ በትላልቅ ሰዎች በተለይ በአቶ ቢተዋ በኩል እንዲነገራቸው አደረገ:: አቶ ቢተዋና ሌሎችም የጌታው ኃይሉ ወዳጆች ከቤተ መንግሥት ስንፈለግ ግድ የለም ይችን ፍታ ጎንደር ሀድና አግባ



በማለት አሳመኑአቸው:: ልጅ ካሳም የቋራ ባላባቶችንና ከመለመሉአቸው ሠራዊታቸውም በግማሹ ይዘው ወደ ጎንደር ሄዱ:: የራስ አሊ አሉላን ልጅ ወይዘሪት ተዋበችን አጋቧቸው:: ልጅ ካሣ ጎንደር የመሳፍንቶችን አሠራር ሲመለከቱ ሰንብተው ወይዘሮ ተዋበች አሊ አሉላን በመያዝ ወደ ቋራ ሄዱ::

ከጎንደር እንደተመለሱ ወዲያው ሳይውሉ ሳያድሩ 16 ሺህ ሠራዊት አሰልፈው ሱዳን ዘመቱ:: በዘመናዊ የጦር መሣሪያ የደነደነውንና በወታደራዊ ስልት የሠለጠነውን ቱርክን መሸነ ከተቀመጠበት የልጅ ካሣ ሠራዊት ገብቶ ይነድፈው ጀመር:: በዚህ ወቅት ልጅ ካሣ ቆሰሉ:: ባለቤታቸው ወይዘሮ ተዋበች አሊ ተማረኩ:: ልጅ ካሣ ባለቤታቸው ከታሰሩበት ራሳቸው ገብተው አስወጥተው ወደ አገራቸው በድል አድራጊነት ተመለሱ::

ከጦርነቱ መልስ በደንቡ መሠረት ባለቤታቸውን ከወላጆችዋ ማገናኘት ስላለባቸውና ሱዳንም ካገኙት ምርኮ ቆንጠር አድርገው በመያዝ ጎንደር መጡ:: ሕዝብን መዝረፍ የለመዱት መሳፍንት ያልተበላ ሰው በማግኘታቸው ተደስተው ስጦታውን ተቀበሉ:: ሰንበት ብለው እቴጌ መነን "ልጅ ካሣ አንተን የሚረዳህ ሰው አብሮህ ይሄዳል"በማለት የበላይ ሹመው ሊልኩባቸው ወሰነዋል:: ከዚህ በፊት ይህን ያህል ስጦታ ያመጣ መኳንንት ስላላዩ የራሳቸውን ሰው ቢልኩማ ከዚህ የበለጠ ንብረት እንደሚሰበስብ በማመን ነበር ውሳኔያቸው:: ልጅ ካሣም እሽም እምቢም ሳይሉ ሰነበቱ::

በዚህ ወቅት ልጅ ካሳ ኮሶ ታያቸውና መንገድ ከመጀመራቸው በፊት ሽረው ለመሄድ ስላሰቡ "ኮሶ ይጠጣሉ" ተብሎ ተነገራቸው:: 3ኛው አጤ ዮሐንስ መሲና ሲያዘጋጁላቸው እቴጌይቱ ልጅ ካሣን በመናቅ" ለቆለኛ ወርች ይበቀዋል"በማለት ወርች ላኩላቸው:: ይህ የልጅ ካሣን ክብር የሚነካ በመሆኑ አኮረፉ:: ባለቤታቸው ወይዘሮ ተዋበች በነገሩ በጣም ተበሳጩ ልጅ ካሣም "ተዋበች ዛሬውኑ ወደ ቋራ እንሄዳለን" ሲሏቸው ተዋበችም "የአንተ መናቅ የእኔ መናቅ ነው አገር የለህም እንዴ?" አሉአቸው::

<u>የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 248 " በዘመኑ ከቤተ መንግሥት ኮሶ የተጣባው ሰው ሲኖር እንደየሰውየው የክብር ደረጃ ማዕረግ ሙሉ በሬ፤ መሲና ላም፤ የበግ

ሙክት፣ የብልት ሥጋ፣ እየተላከ ኮሦውን ከሻረ በኋላ ይመገባል:: ሆኖም ግን ከንግሥቲቱ ቤት መብሉ መጠጡ..ሁሉ ነገር ሞልቶ እያለ መሲናም ሆነ ፍሪዳ ወይም የበግ ሙክት ሲገባቸው አንድ እግር ሥጋ መላካቸው ለእኔ ክብር ቦታ ባለመስጠታቸው ነው በማለት ልጅ ካሣ እጅግ ተቆጡ:: ለባለቤታቸው ለወይዘሮ ተዋበች እናትሽ በእኔ ላይ ያደረጉትን ግፍ ትመለከቻለሽን? አሏት:: እሷም በልጅ ካሣ ያደረው የቁጣ መንፈስ በተዋበች ላይ ሰርስሮ ስለገባ ካሣ ኃይሉ በወገብህ ዝናርህን ታጠቅ ስፍራ የለህም እንዴ? ብለው ሲናገሯቸው በሌሊት ፈጥነው በመውጣት ወደ ቋራ ሄዱ" ሲሉ ጽፈዋል::

ልጅ ካሣ እቴጌ መነንን ሆነ ግንብ ጠባዋቂ 3ኛው አጤ ዮሐንስንና መኳንንቱን ሳይሰናበቱ ጉዞአቸውን ወደ ቋራ አደረጉ:: የባልና ሚስቱ መጥፋት በቤተ መንግሥቱ ሲሰማ እቴጌ መነን "ይህ የፍየል እረኛ ልጅ ምንኛ ቢንቀን ነው? ሳይሰናበተን ልጃችን ይዞ የሄደ" በማለት ይጮሁ ጀመር:: በዚሁ ወቅት ልጅ ካሣን ከመንገድ አንቆ ይዞ የሚያመጣ ጦር ወደ ቋራ ተላከ::

ልጅ ካሣም የመጣውን ጦር ደምስሰው ማረኩ:: ከጎንደር ወደ ቋራ የሄደው ሠራዊት መደምሰሱ ወሬው ጎንደር ሲሰማ እንዴት ቢደፍረን ነው ይህን ያደረገው ይባልና ይሳቅም ጀመር:: እቴጌ መነን ግን ተበሳጩ ደጃዝማች ወንድ ይራድ በዚህ ቀን "ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ አንገቱን አንቄ አመጣዋለሁ በማለት በብርሌ ጠጃቸውን እንደያዙ ፎከሩ:: ደጃዝማች ወንድ ይራድ የአራት ደጃዝማቾች ጦር መሪ በመሆን ወደ ልጅ ካሣ ሰፈር ገሰገሱ:: በሌሎች የታሪክ አጻጻፍ ደጃዝማች ወንድ ይራድ እንጅ ቀኛዝማች ወንድ ይራድ አይባሉም ደብተራ ዘነብ ግን ቀኛዝማች ይሏቸዋል:: ስለዚህ ደብተራ እንዲህ ይላሉ::

ደብተራ ዘነብ <u>የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ያሳተመው ገጽ 10 "መኳንንት ብዙ ነው 1000 ነፍጥ ተማረከ:: ልጅ ካሣም አራት መቶ ጋሻና 22 ነፍጠኛ ይዘው ነው የገጠሙት:: ተወይዘሮ መነንም አንድ መኮንን ቀኝ አዝማች ወንድ ይራድ እንዲህ ብሎ ፎከረ:: ለወይዘሮ መነን ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ አሁን እንደ ሙጭልጭላ አንገቱን አንቄ አመጣልሻለሁ አይዞሽ ብሎ ወይዘሮ መነን እንደ ደነገጡ አይቷልና ልጅ ካሣ ሸፈተ ባልዋቸው ጊዜ ጫቆ ከተያዙት መኳንንት አንዱ ቀኛዝማች ወንድ ይራድ ነው::"



"የኮሶ ሺያጭ ልጅ ብሎ ልጅ ካሣን የሰደበ:: ልጅ ካሣም እሱን እንደ ተያዘ ባዩ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑ:: ወታደርንም ሁሳ እንዲህ አሉት:: ወታደር ዛሬ ለምኘሀለሁ ኮሶ የሚመገብ እንግዳ መጥቶብኛልና ብለው ብዙ ኮሶ በተሰበሰበ ጊዜ አስደቁሰው በታላቅ ጽዋ ሙሉ አድርገው ለቀኛዝማች ወንድ ይራድ እንዲህ ብለው ሰጠዎው:: እናቴ ከገበያው ኮሶ ሳይሸጥላት ቀረ:: እህል ታጣና ይህንን ኮሰውን ተመገቡ ባሉ ጊዜ አኩሌታው እስተፋው ልጅ ካሣ ጦራቸውን ከጭናቸው አኑረው ነው" ሲሉ ጽፈዋል::

በዚህ ወቅት የልጅ ካሣ ጦር አስቀድሞ ጥሩ ጉድብ ምሽግ ይዞ ስለነበር የደጃዝማች ወንድ ይራድን ጦር ያነጥፉት ጀመር:: ወዲያውኑ ደጃዝማች ወንድ ይራድ ተማረኩና ከልጅ ካሣ ፊት ቀረቡ በአፍ ይበላበታል እንጂ ግፍ አይነገርበትም እንደሚባለው ሁሉ ደጃዝማች ወንድ ይራድ ጎንደር እቴጌ መነንን ለማስደሰት የፎከሩት ፍከራ ቀድሞ ከልጅ ካሣ ሰፈር ደርሶ ኑሮ ካሣም በሚያምር የቆላ ሽክና "እንቆቆውን በጥብጡና ይስተናገድ ስጡት ይጠጣ" በማለት ግብግቦ ቀረበላቸው:: ደጃዝማች ወንድ ይራድ÷ የእንቆቆ ጠላ እየተጋቱም ለልጅ ካሣ ወታደሮች ምግብ እንዲፈጩ ታዘዙ:: በዚያው ወቅት ልጅ ካሳ እንዲህ እያሉ መናገራቸው ተጽፏል::

"የጀግናውን እናት የኔ የመይሳው
ኮሶ ሻጭ ናት ብሎ የነገረህ ማነው?" አሉት ልጅ ካሳ::

ደጃዝማች ወንድ ይራድ እንደ ሴት ወፍጮ ሲፈጩ የተመለከቱ ሰዎች ከመሳቅ አልፈው አንዳንዶቹ ያለቀሱም አልታጡም:: ይህን ያደረገው ጡር ነው ያሉም ነበር:: ጡር ማለት መስቃ መናገር ማለት ነው:: ሌላው ደግሞ የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም እንደማለት ሲሆን ዋናው ያስገረማቸው ግን ለሁሉም ጊዜ አለው ለወንድም ወንድ አለው በማለት የተገረሙም አልጠፉም:: ይህን የደጃዝማች ወንድ ይራድ መፍጨት የተመለከቱ ይህን ገጠሙ::

ደጃዝማች ወንድ ይራድ ምነው የማይከራ
ነውር አይደለም ወይ መግባት በሴት ሥራ
ደጃዝማች ወንድ ይራድን የሚመክረው ጠፍቶ
ሲፈጭ አደረ አሉ በሴት ሥራ ገብቶ

እያሉ ገጠሙባቸው::

ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር <u>እነሆ ጀግና</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 27 "ወንድ ይራድ ተማረከ ወንድ መሆኑ ነው እንጂ አስቸጋሪው ወንድ ይራድ፣ መሳደብ ቀላል ነው:: ለቁርስ፣ለምሳ ለእራት ኮሶ እንቆቆ እየጠጣ ወንድ ይራድን በቁርጠትና በተቅማጥ ገደለው" ሲሉ ጽፈዋል::

## ምዕራፍ 4

### ካሣ ኃይሉ የኮሶ ሻጭ ልጅ አልነበሩም!

ሰዎች የወደዱት ሲታማ ደስ አይላቸውም:: ለምን? ታሪኩን በዋቢ ማቅረብና ማስረዳት እንጂ የሰፈር ልጅ ጠበቃ መሆን አያስፈልግም:: ሌባ ቢሆን የሌባ ጠበቃ መሆን አያስፈልግም:: ለምሳሌ ወንድሙ ገንዘብ ቢቀማው ቃሉን ቢክድ ወንድሜ ስለሆነ ክህደቱን አልነግርበትም የሚል ሰው የለም:: ለወንድሙ ክህዲነቱን ካልደበቀ የአገሬ የሰፈሬ ልጅ ስለሆነ ብሎ የሌላውን ሰው ስም በሀሰት ማጥፋት የታሪክ ደራሲ ሊሆን አይገባውም:: እያንዳንዳችን በተወለድንበት ክፍለ ሀገር አጭበርባሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ::

ለእነዚህ አጭበርባሪዎች ጠበቃ ሁነን ሥራቸውን አንደብቅላቸውም:: ይህን ልልበት የቻልኩት እኔ ለአጤ ቴዎድሮስ ጠበቃ ለመሆን ሳይሆን ትክክሉን ታሪክ ለመጻፍ ስለፈለኩ ነው:: አጤ ቴዎድሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ አለመሆናቸውን በሚመለከት አቶ ጳውሎስ ኞኞ በጣም ለፍተዋል:: መንሥኤው የት እንደሆነ ፈልገው መልስ ሰጥተውበታል:: በሥነ መንግሥት በፖለቲካ የተወራ እንጂ በእውነት አጤ ቴዎድሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ ሁነው አይደለም:: ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በሰው ደም ይታጠቡ ነበር ተብሎም ተጽፏል:: የንግሥት ዘውዲቱ በሰው ደም ይታጠቡ ነበር ተብሎ የተጻፈውን የጻፉትን ስንመለከት ውሸት ሁኖ ይገኛል::

ባቢሌ ቶላ <u>አንድ ትውልድ ለመምተር ቀይ ሽብር በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 9 "ኢትዮጵያውያን ግን ንግሥት ዘውዲቱ ዕድሜያቸው እንዲረዝም በሰው ደም ይታጠቡ እንደነበር" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሁኖ ወደ



አማርኛ የተረጎሙት ወያኔ በ1983 ዓም ያሰራቸው እስካሁን ይሙቱ ይዳኑ የማይታወቁት አቶ ጸጋየ ገብረመድኅን ወይም አበበ ደብተራው ናቸው::

በሰው ደም መታጠብን ካነሣን አይቀር ሌሎች እየሞቱ እርሳቸው አውሮፓ ቁጭ ብለው ሌሎች የሞቱበትን የሚመዝቡ ይህን መጽሐፍ የጻፉት ግለሰብ ናቸው:: መጽሐፉን የጻፉት ደራሲ የተጠቀሙበት የብዕር ስም ነው:: በድርሰት ሥርዓት መሠረት ዋቢ መጠቀም ከመጽሐፉ ባለው ስም ልህድ በማለት እንጂ ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዕድሜያቸው እንዲረዝም ብለው በሰው ደም መታጠብ ቀርቶ አልፈው ሲሄዱ ሕፃን ሲያለቅስ ቢያዩ ሊያባብሉ የሚቆሙ ደግ ነበሩ::

ምን ይህ ብቻ ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴም ቆሪጥ የተባለ ሰይጣን ጠንቋይ ነበራቸው ተብሎ ይወራል:: ታዲያ ቆሪጥ ለምን የሚሞቱበትን ቀንና ማን ሊገድላቸው እንደተሰለፈ አልነገረም? በ1943 ዓም በነደጃዝማች ነጋሽ በዛብህና በሌሎቹም መኳንንቶች መገልበጠ መንግሥት ሲታሰብ በ1953 ዓም በነጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ በ1959 ዓም የግድያ ሙከራ በጄኔራል ታደሰ ብሩና ኋላም በደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ሲሞከርባቸው ብሎም ደርግ መስከረም 2 ቀን በ1967 ዓም ከሥልጣን ሲያወርዳቸው ለምን ቆሪጥ አልነገራቸውም? ይህን ሁሉ ስናጤን ውሸት መሆኑን እንረዳለን:: የአጤ ቴዎድሮስ እናት ኮሶ ሻጭ ናቸው በማለት በዚህ ዓይነት ታሪክ የተበላሸ መሆኑን ያስረዳል::

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ <u>ከአጤ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 1 "በኢትዮጵያ ምዕራብና ሰሜን የቱርክና የግብፅ መንግሥት ተስፋፍቶ ራሷንም ኢትዮጵያን በሚያስጋበት ጊዜ በኢትዮጵያ ምዕራብ በቋራ በተለይ ሻርጌ ከሚባለው ሥፍራ ምንም እንኳ የነጋሢነት ዘር ባይኖረው ስሙ ከመግነን ጋራ ያሸናፊነት ዕድል ያለውን አንድ ሰው አሥነሥቶ ኢትዮጵያ የታፈረች ሆና እንድትኖር እግዚአብሔር ስለ ፈለገ ኃይሉ የሚባሉ የቋራ ተወላጅ::"

"ከደንቢያ ባላባት ከሚወለዱት ከእመት አትጠገብ ልጅ ካሳን (በኋላ ቴዎድሮስ የተባሉትን) ባ1811 ዓም ወለዱ:: ሌሎች ታሪክ ጸሐፊዎች

አባታቸው እንጂ እናቲቱ ባላባትነት የላቸውም እንዲያውም በድህነት ምክንያት ኮሶ ይሸጡ ነበር ይላሉ:: ይሁን እንጂ በሁለቱም ዐይነት ቢሆን ልጅ ካሣ ባላባትነት ካላቸው ውስጥ እንደ ተወለዱ አባታቸው ስለ ሞቱ ከእናታቸው ጋራ ተቀመጡ" ሲሉ ጽፈዋል:: እርሳቸው በይላሉ ማለፋቸው የተጠራጠሩ ያስመስላቸዋል::

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፋ ገጽ 7 "ካሣ ወይም በኋለኛው ዘመን ቴዎድሮስ የተባሉት የኮሶ ሻጭ ልጅ መሆናቸውን አንዳንድ የውጭ አገር ጸሐፊዎች ጽፈዋል:: ያገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች ይህንኑ አምነውበት ቴዎድሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ ናቸው እያሉ ተርከዋል:: እናቲቱ ኮሶ ለመሸጣቸው ግን ያቀረቡት ማስረጃ የለም:: እኔም አላገኘሁም:: ወይዘሮ አትጠገብ በምን ምክንያት ኮሶ ይሸጡ እንደነበር በዚያ ዘመን ኮሶ ከየዱሩ በሚሸመጠጥበት ጊዜ የኮሶው ገበያ ምን ያህል የኑሮ መግፊያ ጥቅም ይሰጣቸው እንደነበረም የሚተርክ የለም::"

"የወይዘሮ አትጠገብን የኮሶ ሻጭነት ወሬ ያባዛውና በመጽሐፍ ለዓለም ያዳረሰው እስቲቨ የተባለው ሚሲዮናዊው ሄነሪ እስተርን ነው:: እሱም የጻፈው ከሰዎች የሰማውን የሐሜት ወሬ ይዞ ነው:: ካሳን ከድሃ ቤተሰብ ልጅነት አውጥቶ ከሀብታሞች ጉያ ለመጨመር መከራከሬ ሳይሆን እውነተኛውን ወይም እውነት የሚመስለውን ታሪክ ለመከተል ብዬ ነው:: የካሣ ወይም የአጤ ቴዎድሮስ አያት ማለት የአቶ ኃይሉ አባት ወልደ ጊዮርጊስ ደጃዝማች ናቸው" ይሉና ገጽ 10 "ራሳም በ1ኛ ቮልዩም መጽሐፉ ላይ ስለዚህ እስተርን እንደጻፈው እናትየዋ ኮሶ ሻጭ መሆናቸውን ለማጣራት ሞክሬ ነበር::"

"አንድም ሰው ኮሶ ሲሸጡ አይቻለሁ የሚል የዓይን ምስክር አላገኘሁም:: ያነጋገርኳቸው ሁሉ የሚነግሩኝ የባላባት ዘር መሆናቸውን አባታቸውም መሆናቸውን ነው:: በአበሻ ውስጥ ታላላቅ ከሚባሉት ዘር መወለዳቸውን ነው ያጣራሁት:: እስተርን በንጉሡ ችሎት ቁሞ ቴዎድሮስ ሲያነጋግሩት የድፍረት ቃል እየመለሰ ጣቱን በማስጮህ በለው በለው ብለው በሽመል ሲመታ ከኪሱ የማስታወሻ ደብተሩ ወደቀች:: በዚያችም ደብተር ላይ ንጉሡ ገዳይ ናቸው የሚል ቃል በመገኘቱ ዕቃው ሁሉ ተፈትሾ ታሰረ::



ከዚህ በኋላ ሲለቀቅ ያን ቂሙን ለመወጣት ያዋረደ መስሎት የኮሶ ሻጭ ልጅ ብሎ ጻፈ ብሏል በዚህ ይብቃን" ሲሉ ጽፈዋል አቶ ጳውሎስ ኞኞ የሚሰዮኗውን እስተርን አጻጻፍ ታሪክ ትክክል አለመሆኑን ራሳም ከጻፈው መጽሐፍ መንሥኤውን ዘርዝረው ጽፈዋል:: እስተር የጻፈው ትክክል አለመሆኑን ራሳም ካጣራ የተወራው ሁሉ ውሸት ነው ማለት ነው:: ስለዚህ አቶ ገሪማ ታረፈ ከመነሻው ጀምረው የኮሶ ሻጭ መንሥኤው እንዴት እንደተጀመረ አንድ ባንድ ዘግበውታል::

<u>አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው አንበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 19-20 "ኮሶ ሻጭ ወይም የኮሶ ሻጭ ልጅ የተባለው ስም እንደምን እንደተራባ ለማስረዳትና ምክንያቱንም ከመሠረቱ ማጣራት ስለአስፈለገ ከእውነተኛ ምንጭ አትጠገብ ወንድ በወስን በየአውራጃውና በየወረዳው የሚወለዱ ወይዘሮ መሆናቸው ከዚህ ቀጥሎ እንደተዘረዘረው የትውልድ ሐረግ ተገልጿል:: ወይዘሮ አትጠገብ ወይና ደጋ ወረዳ በአውሊድ ማርያም ሰበካ ከሚገኙት ወላጆቻቸው ጋር በመሬት ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ ልዩ ስሙ ኮሶ አላየ የሆነው ስፊ መሬት የእርሳቸው ድርሻ ይሆናል::"

"ይሁን እንጂ ወይዘሮዬቱ በዕጣ የደረሳቸው መሬት ኮሶ የመላበት ስለሆነ ይህንኑ መሬት ለማልማት ሲያስመነጥሩ በመሬቱ መካከል አንድ የኮሶ ዛፍ ኮሶ ያፈራ ስለተገኘ እንደ አትክልት ቆጥረውት እንዳይቆረጥ ከልልለው ወደ ጎንደር ተመለሱ:: በሌላው ጊዜ ደግሞ ልሚቱን ለማየት ከጎንደር ወደ መሬታቸው ሂደው ልማቱን ሲመለከቱ የኮሶው ዛፍ አብቦና አፍርቶ የተመለከተች ገረድ ኮሶው አፍርቷልና ለቤተሰብ የሚሆን ለቅሜ ልያዝ ትላቸዋለች"

"እርሳቸውም ከሆነ መልካም ነው ለቅመሽ ያዥ ይላሉ:: ገረድ ያፈራ ያፈራውን ለቀመችና ቋጥራ ወደ ጎንደር ይመለሳሉ:: በዚህ ጊዜ ይህን የተመለከተ የመሬት ባላንጣ ጠላት ይቀባል ጥላት እንደተባለው ሰንበቴ ከሚጠጣበት ሂዶ አያችሁ ወይዘሮ አትጠገብ በአለባበሷና በሁኔታዋ ወይዘሮ ትመስላለች:: በአንድ በኩል ደግሞ ኮሶ እያስለቀመች ጎንደር ወስዳ ትሸጣለች በማለት እያባዛ ይናገራል::"

“ከዚህ በኋላ ስም ይወጣል ከቤት ይቀበላል ጎረቤት እንደሚባለው ከዚህ ሰው ወሬ የተነሣ ኮሶ ሻጭ የሚለው ትርፍ ምላስ በቀል እንጂ ወይዘሮ አትጠገብ በጎንደር ሰፋፊ የከተማ ቦታ በገጠር ርስትና ጉልት ያላቸው ራሳቸውን ችለው የሚተዳደሩ ሴት ወይዘሮ ናቸው:: ይሁን እንጅ በግእዝ የተጻፈው የጎንደር ታሪክ ነገሥት ስለ አጤ ቴዎድሮስ ስርወ ትውልድ ሲናገር ፥ወተንሥአ ብእሲ ኃያል ቴዎድሮስ ወጥንተ ስሙ ደጃዝማች ካሣ ዘእምነገደ ሄት ወልደ አምኖን ወልደ ዳዊት ንጉሥ እያለ ከዳዊት ወገን መሆናቸውን ያትታል” ሲሉ ጽፈዋል::

Harold G.Marcus <u>A HISTORY OF ETHIOPIA</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 59 Dej.Hailu Wolde Giorgis, who governed Kwara,and woizero Attetegab, both of whom later received invented Solomonic genealogies. There was no binding church marriage and around 1820,the dejzmach chose a new consort,and Attetegab took her son to Gonder, where she eked out a living by selling koso,a powerful purgative” ሲሉ ጽፈዋል:: እኒህ ጸሐፊም የእስቴርን ወሬ ወርሰው መሆን አለበት::

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ <u>ከአጤ ልብነ ድንግል እስከ አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 374 “ይኸውም አጤ ቴዎድሮስ ሊነሡ የቀረበበት ጊዜ ዋዜማ መሆኑ ነው:: በዚህ ጊዜ ርሳቸው መዠመርያ የራስ አሊ አሽከር ሆነው በኋላ ደግሞ ልጃቸውን ወይዘሮ ተዋበችን አግብተው ያንኑ ያሽከርነት ሥራቸውን ይቀጥላሉ” ሲሉ ጽፈዋል:: እንዲሁም ደግሞ ከዚህ በሚከተለው መጽሐፍ ላይ ደግሞ ቃሉን ደግመውታል::

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ <u>ከአጤ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊኃይለ ሥላሴ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 2 “በኋላም ሽፍትነቱን ትተው ከደጃች ጎሹና ከራስ አሊ ቤት በነበሩ ጊዜ የቤተ መንግሥት አስተዳደግና የወታደርነት ሥራ ሲለምዱ ኖሩ:: ስናር (ሱዳን ውስጥ) በሚባለው ስፍራ ከግብጾች ጋራ ጦርነት በተደረገ ጊዜ ብዙ ጀብድ ሠርተው ስለ ነበር ዝናቸው በያለበት ተሰማ” ሲሉ ጽፈዋል::

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ <u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 63 “ቴዎድሮስ በዚህ ዕድሜያቸው አካባቢ ላይ ከደጃች ክንፉም ከልጅ መኮንንም ካቶ ቢተዋም



ከደጃዝማች ጎሹም አሽከርነት ነጻ ሆነው ሥልጣን ለመያዝ ወደሚያስችላቸው ወደ ሽፍትነት እንደ ተሰማሩ” ሲሉ ጽፈዋል:: ከላይ ከራስ አሊ አሽከርነት መግባታቸውን ጠቅሰው ከታች ደግሞ ለምን ረሱት::

ደራሲ ኮራዶ ዞሊ ትርጉም ዘሪሁን ገብሬ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጤ ናአድ እስከ አልጋወራሽ</u> ራስ ተፈሪ መኮንን በተባለው መጽሐፍ ገጽ 94 “ለመሆኑ የራስ አሊ ሎሌ የነበሩት ካሣ ኃይሉ ማን ናቸው? ካሣ ኃይሉ የተወለዱት በጣም ድኻ ከሆነ ቤተሰብ ሲሆን ትውልድ ሀገራቸው ጎንደር የተወለዱበት ቦታ ልዩ ስሙ በቋራ ወረዳ ጨርጌ ተብሎ በሚጠራው ቦታ ነው:: ዘመኑም በ1820 ዓም” ሲሉ ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስን በተመለከተ የውጭ አገር ደራስያን ሆኑ የአገር ልጆች ከጻፉት ሰነድ የሚያመለክተው የራስ አሊ አሽከር መሆናቸውን ከዚህ ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ በቀር በማንም ተጠቅሶ አላነበብኩም:: ባይሆን አንዳንዶች ግብር ለራስ አሊ ወስደው ነበር የሚሉ ሰነዶች ጥቂት አሉ::

“የኮሶ ሻጭ ልጅ ናቸው” የሚለው ታሪክ በኢትዮጵያውያን ከተጻፈ መጻሕፍት ሁሉ አቶ ጳውሎስ ኞኞ የጻፉትን የሚያስንቅ አልተጻፈም:: በአጠቃላይ አቶ ጳውሎስ ኞኞ የውጭ አገር ደራስያንን በተመለከተ ማስተዋል እንዳለብን መክረውናል:: የውጭ አገር ደራስያን ብቻ ሳይሆን በእኛ ወገኖች የተጻፈውንም በጥሞና ስናነበው አንዳንድ ስህተት ስላለበት በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ግርሃም ሐንኮክ የላሊበላን አብያተ ክርስቲያናት የሠሩት ነጮች ቴምፕላሮች ናቸው ይላል::

ግራሀም ሐንኮክ እንደጻፈው ጌታቸው ተስፋዬ ጎጂ እንደተረጎመው <u>ታቦተ ጽዮንን ፍለጋ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 70 “የተሠራውም በነጮች ነው፥እነሱም የሠሩት በንጉሥ ላሊበላ ታዘው ነው” ይሉና ገጽ 237 “ቴምፕላሮች ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በንጉሥ ላሊበላ ዘመነ መንግሥት መሆኑ ይታወሳል:: አሁን ደግሞ የማኅበራቸው መለያ የሆነውን መስቀል አክሱም ውስጥ አገኘሁ:: ተጨማሪ ተመሳሳይ የመስቀል ቅርጸችንም በካሌብ ቤተ መንግሥት ፍርስራሽ ውስጥ ልመለከት ነው” ሲሉ ጽፈዋል::

ላሊበላ ሕንጻን ነጮች ከሠሩት ለምን በፈረንሳይ አገር ቴምፕላሮች ከተመሠረቱበት አገር ይህን መሳይ ሕንጻ ሊኖር አልቻለም? ደግሞም “አሁን የማኅበራቸው መለያ የሆነውን መስቀል አክሱም ውስጥ አገኘሁ ተጨማሪ ተመሳሳይ የመስቀል ቅርጾችም በካሌብ ቤተ መንግሥት ፍርስራሽ ውስጥ ልመለከት ነው” ሲሉ ራሱን በራሱ ይቃረናል::

አጤ ካሌብ በ485 እስከ 515 የነበሩ ሲሆኑ ቴምፕላሮቹ የተመሠረቱት በ11ኛው ክፍለ ዘመን የፈረንሳይ ሊቀ ጳጳስ ያቋቋማቸው ሲሆኑ መስቀላቸው እንዴት ቀድሞ አክሱም ከአጤ ካሌብ ቤተ መንግሥት ሊገኝ ቻለ? እንግዲያውስ ከኢትዮጵያ ተሰርቆ የተወሰደ የቴምፕላሮቹ ቅርስ የኢትዮጵያ ነው:: ግራሀም ሐንኮክ በዚህ ስህተት ብቻ ሳይሆን ሌላም ስህተት ጽፈዋል::

ገጽ 22 “ከ1270 ጀምሮ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እስከ ወደቁበት 1974 ድረስ ለስድስት መቶ ዓመታት ከአንድ ንጉሥ በስተቀር የኢትዮጵያ ነገሥታት አማሮች ነበሩ” ሲሉ ጽፈዋል:: በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ከ1270.8 ሲቀነስ 1262 ዓም ይሆናል ከዛጉዬ ወደ ሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ያመጡት ተማሪ ተስፋ ልደት የኋላው አጤ ይኩኖ አምላክን ማነው አማራ ያደረጋቸው? ከእርሳቸው ወዲህ የነገሡት ሌሎች ቢሆኑ ማነው አማራ?

የአጤ ይኩኖ አምላክ ቅድመ አያቶች ከአክሱም ወደ መንዝ የተሰደዱት በ912 ዓም ሲሆን ሸዋ መጥተው ከከንባታ ሐድያ ከሌሎችም ጎሳዎች ጋር የተዋለዱ ናቸው:: በ1262 ዓም ከዛጉዬ ሥርዎ መንግሥት ሲያመጡ እርሳቸው የተዋለዱ በብዛት ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ሲሆን የአጤ ልብነ ድንግል እናት እቴጌ እሌኒ የከንባታ እስላም ነበሩ::

ክርስትና ተነሥተው አጤ ልብነ ድንግልን ወለዱ:: አጤ ልብነ ድንግል ሚስታቸው ትግሬ የመቀሌ ተወላጅ እቴጌ ሰብለወንጌል ሲሆኑ ልጃቸው አጤ ገላውዴዎስና አጤ ሚናስ ሌሎችም ሸዋ ቀሩ የሚባሉት ሁላ እናታቸው ትግሬ ናቸው:: ጎንደር የገባው መንግሥት የቱ ነው አማራ? አጤ ኢዮአስ የወሎ ኦሮሞ ሌሎችስ?አጤ ምኒልክስ አማራ፤ኦሮሞ፤ጉሬጌ አይደሉምን? አጤ ኃይለ ሥላሴም ትግሬ ከላይ የሚወርድ ዘር ሲኖራቸው አማራ በትንሹ የወይዘሮ



የሽመቤት እናት ንጹሕ ጉራጌ አባታቸው የወሎ ኦሮሞ በሃይማኖታቸው እስላም የነበሩ ናቸው::

አጤ ኃይለ ሥላሴ ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 1“ በዚሁም ዘመን የሕግ ሚስታቸውን ወይዘሮ የሽመቤትን (የእኔን እናት አገቡ” ሲሉ እርሳቸውን አባት አልባ አስቀሯቸው:: ለምን ጃንሆይ የእናታቸውን አባት ስም አልጠቀሱም? ምክንያቱም ወይዘሮ የሽመቤት አሊ የወሎ ኦሮሞ እስላም ስለነበሩ ምናልባት አፍረው ይሆናል:: ከዚያም የወይዘሮ የሺመቤት እናት ጉራጌ ናቸው:: የአባታቸውን ትውልድ ግማሹን ግማሹን ጠቀሱ:: ለምሳሌ “አባቴ ልዑል ራስ መኮንን የሸዋ ንጉሥ የሣሕለ ሥላሴ ልጅ የልዕልት ተናኘ ወርቅ ልጅ ናቸው::”

“አባታቸውም የዶባና የመንዝ ባላባት ደጃዝማች ወልደ ሚካኤል ወልደ መለኮት ናቸው”:: ሲሉ በሌላ ታሪክ ደግሞ የኦሮሞ ዘር ከንጉሥ ሣሕለ ሥላሴ ባለቤት በወይዘሮ በዛብሽ በኩል የሚወርድ ሲኖር ሌላው ዋናው ታሪክ ደግሞ ከትግራይ ሐውዜን ወልደ ጊዮርጊስ ሸዋ መጥቶ ኦሮሞ አግብቶ ጉዲሳን ይወልዳል::

ጉዲሳ ወልደ ጊዮርጊስን፤ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ መለኮትን ይወልዳሉ ወልደ መለኮት ወልደ ሚካኤልን፤ወልደ ሚካኤል ራስ መኮንንን·ራስ መኮንን አጤ ኃይለ ሥላሴን ይወልዳሉ ይህ ነጥሮ የወጣው ታሪክ ሲሆን የውጭ አገር ደራስያን ብቻ ሳይሆኑ መንደርተኞች ደራስያንም ይህን ማስተጋባታቸው አልቀረም:: የውጭ አገር ደራስያን ብዙ ስህተት ይፈጽማሉ:: ያም በ2 ምክንያት ሲሆን የመጀመሪያው በመሰሪነት ሆን ብለው የሚፈጽሙት ተንኮል ነው:: 2ኛው ግን የአገሩን ባህልና ቋንቋ የማያውቁ በመሆናቸው ተርጉሞ የሚነግራቸው ሰው ታሪክ ጠንቅቆ ካለማወቅና ወይም አንዱን ጎሳ ጠልቶ የሚያስጠላ በመሆኑ ነው::

አውቀው የሚያጠፉት ደራሲያን ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ቀይረው አቢሲንያ ብለው የሚጥፉ አልያ ደግሞ አበሻ ብለው የሚጽፉ ናቸው:: አቢሲንያ የሚለውን ለማስረዳት ጥረት የሚያደርጉት ቀደም አቡሳ የሚባል አጤ በመኖሩ ከርሱ ጀምሮ የመጣ ነው ይላሉ:: ይህም ውሸት ነው:: ሐበሻ የሚለውንም ለማስረዳት የሚጥሩት ቅይጥ ሕዝብ በመሆኑ ከእስራኤል ጋር የተዳቀለ በመሆኑ ነው ይላሉ:: ይህም

ውሸት ነው። ኢትዮጵያ የሚለው ስም ኢትጵስ ከተባለው አጤ ጀምሮ የሚጠራ ነው የሚሉት ሁሳ ውሸት ነው።

ኢትዮጵያ ብለው ስም ያወጡልን ግሪኮች ናቸው እያሉ የሚያላዝኑትን ግለሰቦች ጥያቄ ልጠይቃቸው ግሪኮች መጥተው ኢትዮጵያ እስኪሏት ድረስ የኢትዮጵያ ስሟ ማን ይባል ነበር? ይህን ካልመለሱ ሀሰት ነው እንላቸዋለን። ኢትዮጵያ ብለው ስም ያወጡልን አባቶቻችን እንጂ ግሪኮች አይደሉም። ስለዚህ የአገሪቱ ስም ኢትዮጵያ እንጂ አቢሲንያም አበሻም አይደለም። አበሻ ማለት በዐረበኛ ጥቁር ባሪያ ዝቅተኛ ሕዝብ ማለት ነው። ዛሬም አበሻ የሚሉ ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ለመሸሽ ነው። ለምን?

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 10 “የውጭ አገር ታሪክ ጸሐፊዎች ማንኛውንም ሐሜትና ወሬ እያግበሰበሱ ስለሚጽፉ እያጣሩ ማመኑ የኛ ድርሻ ይመስለኛል። ወደፊት እንደምናነበው ቴዎድሮስ ከትቢያ ላይ የተነሣሁ ነኝ እያሉ የሚናገሩት 1ኛ ለትሕትና ብለው ነው። 2ኛ ዳዊት ደጋሚ ስለነበሩ በዳዊት መዝሙር ውስጥ የእስራኤሉ ንጉሥ ዳዊት ስለራሱ ሲናገር ከትቢያና ከዓመድ ላይ የተነሣሁ ነኝ እያለ ስለጻፈ በአገራችን እምነት መሠረት ለትሕትና በዚያ መመራታቸው ነው” ሲሉ ጽፈዋል። ምክሩንማ ምን አቶ ጳውሎስ ብቻ ሊቅ (ዶ/ር)ላጲሶም ከወቀሳ ጋር አስጠንቅቀዋል።

ዶ/ር ላጲሶ ጌ.ደሌቦ <u>ኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች</u> በተባለው መጽሐፉ ገጽ 12 “አውሮፓውያን የፈጠሩ ታሪካቸውን አስተማሩን የነጻ ትምህርት እድል ሰጡን። እኛም ያስተማሩንን አጠናን። ያንን ለሌሎችም ማስተማር ጀመርን። የአርኪዮሎጂ ዕውቀት እየሰፋ ሲሄድ ግን የተማርነው ትምህርት ስህተት ሆኖ ተገኘ” ሲሉ ጽፈዋል።

አንዳንድ ጥቃቅን ስህተቶች ሊፈጠሩ ይችሉ ይሆናል የዚህ ዓይነት የጎላ ስህተት መጻፍ ግን ሆን ተብሎ እንጂ ስህተት ሊባል ስለማይችል አንባቢም ስለ አንድ ታሪክ ከአንድ ቦታ ሲያገኝ ለማመሳከር ጥረት ማድረግ እንጂ ደራሲውን ስለወደደው አልያም ስለሚያውቀው እንዳለ መቀበል የለበትም። ስለዚህ አእምሮ የተፈጠረው ለማመዛዘን እንደመሆኑ መጠን ማመዛዘን ማጣራት ጥሩ ነው የሚል እምነት አለኝ።



ዘራሁን ገብሬ ትርጉም ጸሐፊው ኮራዶ ዞሳ <u>የኢትዮጵያ ታሪክ</u> ካጼ ናዖድ እስከ አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 94 “አባታቸው ገበሬ እናታቸው ኮሶ ሻጭ ነበሩ” ሲሉ ጽፈዋል። የውጭ አገር ደራስያን እንዲያውም አባታቸው ገበሬ ናቸው ብለው ጽፈዋል። ተመልከቱ ሌሎች የሀገራችን ደራስያን አንድም ኃይሉ ወልደ ጊዮርጊስን ገበሬ ነበሩ ብሎ የጻፈ ማንም የለም።

አቶ ገሪማ ታፈረ ሆኑ አቶ ጳውሎስ ኞኞ የኮሶ ሻጭ ልጅ የተባሉበትን ከመነሻው ጀምሮ ዘርዝረው ጽፈዋል። ለዚህ ምዕራፍ መነሻ የሆነው ዋናው አጤ ቴዎድሮስ የኮሶ ሻጭ ልጅ አይደሉም ለማለት ነው። ከላይ የተጠቀሰው ደጃዝማች ወንድ ይራድ እቴጌ መነንን ለማስደሰት ሲሉና በጠጅ ሞቅታ “ይህን የኮሶ ሻጭ ልጅ እንደ ፍየል አንገቱን ይዤ አመጣልሻለሁ” ብለው መፎከራቸው አይዘነጋም።

ይህ የአፍ ወለምታ እርሳቸው ገና ጎንደርን ሳይለቁ ለልጅ ካሳ ደርሶ ኑሮ በሥዕል ተደግፎ ታሪኩ እንደቀረበው ወፍጮ የፈጩበት መንሥኤው ይህ ነው። የእኛ ሰው ደግሞ አንዳንዴ የጠላነውን ሰው አንዴ ጠልተነዋልና የምንታረቅ ስለማይመስለን የተወራውን ማናፈስ ተግባራችን በመሆኑ ከእኛው ሰዎች አልፎ ከውጭ አገር ሰዎች ጀሮ በመድረሱ ዛሬ ታሪክ ሁኖ በመጻፍ ላይ ነው። ነገር ግን ከላይ እንዳልኩት የተጻፈውን ጽሑፍ በጥንቃቄ ካልመረመርነው ጉድለት ሊያመጣ ይችላልና ማመዛዘን ይኖርብናል። ለዚህም ነው አቶ ጳውሎስ ኞኞ በጥንቃቄ መርምረው መልስ የጻፉልን። እኔም ካሳ ኃይሉ የኮሶ ሻጭ ልጅ አይደሉም እላለሁ።

## ምዕራፍ 5

### ደጃዝማች ካሳ

የደጃዝማች ወንድ ይራድ ድል መሆንና የአራት ደጃዝማች ጦር በልጅ ካሣ መማረክ ልጅ ካሳም ደጃዝማች ተብለው መጠራታቸውንና የተማረከው ሠራዊት "የያዝከውን መሣሪያ አስቀምጥና መሄድ የምትፈልግ ሀድ፤የእኔ አሽከር መሆን የምትመርጥ ካለህ ፈቅጄለሃለሁ ብለው ሲነግሩት "እንኳን ተፈቀደልን እንጂ የአንተ አሽከር እንሆናለን" ብሎ ሠራዊቱ ቀረ"ተብሎ ለእቴጌ መነን ተነገራቸው::

ይህን ወሬ ሲሰሙ ቅዠት እንጅ እውነት መስሎ አልታያቸውም:: በአገራችን ታሪክ ደጃዝማችን የማረከ ጀግና ደጃዝማች ተብሎ ይጠራል:: ልጅ ካሳ ደጃዝማች ወንድ ይራድን ከማረኩ በኋላ ደጃዝማች ካሳ ተብለው መጠራት ጀመሩ:: ልጅ ካሣ በዚህ ዓይነት ደጃዝማች ወንድ ይራድን ኮሶ አጠጥተው ወፍጮ እያስፈጩ፤ አድክመው በተቅማጥ እንዲሞት አድርገውታል::

ደብተራ ዘነብ <u>የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ያሳተመው ገጽ 3 "የአበሻ ሰዎች ሁሉ ፍርድን መልካም መሠረትን እግዚአብሔርን መፍራትን በተዉ ጊዜ በስም ክርስቲያን ተብለው በኢየሱስ ወንጌል ፈንታ አስማት ምንዝር ስካር ቧልት ጥመት ባደረጉ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ቀናዒ ነውና ቴዎድሮስን አስነሣ የሚቀጣ" ሲሉ ጽፈዋል:: "ወግዱ ደጃዝማች ወንድ ይራድ ነው ለዚያ ፍየል እረኛ የሚማረከው"በማለት ቢጮሁም ታሪኩ ትክክል መሆኑ ተነገራቸው::

እቴጌ አሁንም ሌሎችን ደጃዝማቾች ሰብስበው "ይህን የፍየል እረኛ ልጅ ታሳዩኛላችሁ"በማለት ላኩ:: ይህ ሲሆን ደጃዝማች ካሣ ደግሞ ከቆላው ለቀው ወደላይ መጥተዋል የሚባለው ወሬ ሲሰማ ዝመት የተባለው ደጃዝማች ሁሉ ይንቀጠቀጥ ጀመር:: ደግሞ በሴት የታዘዙ በመሆናቸው ደጃዝማቾች አንዘምትም ማለትም አልፈለጉም:: የተሰጣቸውን ሠራዊት ሰብስበው ወደ ደንቢያ ወረዱ::



ደጃዝማች ካሣ ከበርሃ ጀምሮ አንጸው ያወጡትን ሠራዊት አዲስ ለሚገቡትና ከደጃዝማች ወንድ ይራድ ጋር የተማረኩትን በእርሳቸው ዘዴ አሠልጥነው ከጎንደር የሚመጣውን ጦር ጣቁሳ ሰቀላ ዋርካ ላይ ውጊያ ጀመሩ:: ነገር ግን ድል የደጃዝማች ካሣ ሆነ:: ይህም ወሬ ጎንደር ደረሰ:: አሁንም እቴጌ ሌላ ጦር አሰባስበው ላኩ ይህ ጦር በጣና አጠገብ ተዋጋ አሁንም ድል የደጃዝማች ካሣ ሆነ:: ይህ ወሬ መልሶ ጎንደር ገባ::

ይህ ድግግሞሽ ድል የደጃዝማች ካሣ መሆኑ ለእቴጌ መነን ፈጽሞ እውነት አልመሰላቸውም፡ ምክንያቱም በአንድ ወጣት ይህን ያክል ደጃዝማች ጦር ድል የሚሆን አልመስላቸው በማለቱ ማመኑ አቃታቸው:: ከዚህ በኋላ እቴጌ መነን ሌላ መላ ታያቸው:: ራሳቸው ዘምተው ደጃዝማች ካሳን አስረው ጎንደር ለማምጣት ወሰኑ:: ግንብ ጠባቂውን 3ኛ አጤ ዮሐንስንና 7 ደጃዝማች ጦር ራሳቸው በመምራት ከጎንደር ደጃዝማች ካሣ ሰፈር ዘመቱ:: ከሰፈሩ ሲደርሱ በእርሳቸው በኩል ያለውን ሠራዊት ብዛት ተመልክተው እንደገና ደግሞ የደጃዝማች ካሣን ሠራዊት አንሶ በማየታቸው "ይህ ቆለኛ የፍየል እረኛ ልጅ የት አባቱ ሊገባ ነው ደፍሮ ከእኔ ጋር ለመዋጋት ሊመጣ ነው" እያሉ እየተመጻደቁ ሄዱ::

የእቴጌ መነን ጦርና የደጃዝማች ካሣ ጦር ገጥሞ ሲዋጋ እቴጌ መነን ከጭናቸው ላይ ቆስለው ተማረኩ:: ምንም እንኳን እቴጌ መነን የያዙት የመሳፍንት አስተዳደር ለኢትዮጵያ የተበላሸ ቢሆንም በቆራጥነታቸው ሴቶች ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ ወንዶች ልንኮራባቸው ይገባል:: ምክንያቱም አልበገሬ መሆናቸውና ወንዶች ሲርበደበዱ ሴቷ ጦር ሰብስበው መዝመታቸው ጀግና ናቸው::

ወደ ነበርኩበት ልመለስና ደጃዝማች ካሣ ስለ እቴጌ መነን ወግ ሲወጋ ቀደም" ይቺን ቆፍጣጣ አንድ ቀን ባቄላ ሳላስፈጫት አልቀርም" በማለት ይፎክሩ ነበርና ተማርከው ከደጃዝማች ካሣ ፊት ሲቀርቡ ደጃዝማች ካሣ "ባቄላ አቅርቡላት ትፍጭ"በማለት ወደ ወፍጮው ጋበዟቸው:: ከእቴጌ መነን ጋር አብራ የመጣች ሠራተኛ እኔ ልፍጭ ስትል ጥፊ ቀመሰች:: በዚህ ወቅት እቴጌ መነን መቀነታቸውን ጠበቅ አድርገው መፍጨት ሲጀምሩ የደንቢያ ዘፋኝ::

"እቴጌ መነን ምነው ምን ሁነዋል?
ማስተዳደር ቀርቶ መፍጨት ጀምረዋል፤
ያን ሁሉ ደጃዝማች ያዘዘች እመቤት፤
ሁሉን ተወችና ገብታለች ወፍጮ ቤት
ጊዜው በማለቁ በመገባደዱ
እቴጌ መነንም መጅ መያዝ ለመዱ"

እያሉ ዘፈኑባቸው:: እቴጌ መነን ያመጡት የ7 ደጃዝማች ጦር ሙሉ በሙሉ በደጃዝማች ካሣ ጦር ተማረከ:: በዚህ ወቅት ልጃቸው የወይዘሮ ምንትዋብ አባት ራስ አሊ ነዋሪነታቸው ደብረ ታቦር ስለሆነ የእናታቸውን መማረክ ሰሙ:: እንደናታቸው ከልጃቸው ባል ጋር አታካሮ ከመግባት ይልቅ ነገሩን ለስለስ አድርጎ በምርኮ ያሉትን የእንጀራ አባታቸውን 3ኛው አጤ ዮሐንስንና እናታቸውን እቴጌ መነንን ለማስፈታት ድርድር ገቡ::

ደጃዝማች ካሣም የባለቤታቸውን አያት እቴጌ መነንንና ግንብ ጠባቂው 3ኛው አጤ ዮሐንስን ሌሎችንም መኳንንቶች መሄድ የፈለጉትን ሁሉ በሰላም ወደ ጎንደር ሰደዷቸው:: ይህ ከሆነ በኋላ ደጃዝማች ካሣ ከቋራ እስከ ደንቢያ የ3 ደጃዝማች ግዛት ጠቅልለው ይገዙ ጀመር:: በዚህ ወቅት ከሁሉም መሳፍንቶች የበላዩ ራስ አሊ በመሆናቸው ለጎጃሙ ደጃዝማች ጎሹ ደንቢያን ሰጡ:: ደጃዝማች ጎሹ ደንቢያ ሲመጡ ደጃዝማች ካሣ መመለስ እንዳለባቸው ላኩባቸው::

ደብተራ ዘነብ <u>የቴዎድሮስ ታሪክ</u> ሊትማን ያሳተመው ገጽ 11 "ደጃዝማች ካሣም እንዲህ ብለው ላኩ:: እናንተ (ዋሾች ሽሹ) ትላላችሁ አሉ:: አሁንም መጣሁ እንጋጠም ባሏቸው ጊዜ እነደጃዝማች ጎሹ ዝም ብለው ሄዱ:: ወደፎገራ ላሙን ዘርፈው ሰውን ገድለው ቆራጣ ገዳሙን ሰብረው ሰውንም ሁሉ ገድለው ወደ አገራቸው ጎጃም ትሻገሩ" ሲሉ ጽፈዋል:: ከላይ በቅንፍ ያስቀመጥኩት በእኔ እምነት "እናንተ ዋሾች ሽሹ ትላላችሁ አሉ" ለማለት ፈልገው ይሆናል እኔ ግን እንዳለ ነው የገለበጥኩት::

እነደጃዝማች ጎሹ በዚህ ወቅት ኃይል ያነሳቸው ሳይሆን አይቀርም:: ወዲያው ዘርፈው ወደ አገራቸው የተሻገሩት:: ነገር ግን ብዙ ሳይቆዩ የተጠናከረ ኃይል ይዘው ተመልሰው ወደ ደንቢያ መጡ:: አሁንም



ደጃዝማች ካሣ እነ ደጃዝማች ጎሹ መመለሳቸውን ሲሰሙ "አባክዎን ከእርስዎ ጋር ልዋጋ አልፈልግምና ግዛቴን ይልቀቁ"በማለት የቤተ ክርስቲያን አባቶችን ላኩባቸው:: ደጃዝማች ጎሹ "እንዴት ቢደርፍር ነው ይህን መልእክት ለእኛ የሚልከው? ሴት መማረክ መስለው እንዴ ይምጣ እጄን ይቅመስ ይህ ወጠጤ" በማለት ተቆነጠነጡ አዝማሪያዊ መቅጫ ከመሐል ሁኖ እርሳቸውን ያደፋፍር ጀመር::
የወንዶች ባል ነው ደጃዝማች ጎሹ፤
እጃችሁን ስጡ ሳትበላሹ፤
ያንጃብባል እንጂ መቼ ይዋጋል ካሳ፤
ወርደህ ጥመድበት ከሽንብራው ማሳ፤

እያለ ይፎክር ጀመር:: በደጃዝማች ጎሹ ሰፈር የሚፎከረውና የሚገጠመው ግጥም ለደጃዝማች ካሣ ደረሳቸው እርሳቸውም አባቴ ናቸው በማለት በሰላም ወደመጡበት የሚሄዱ መስሎኝ እንጂ እምቢ ካሉማ የወንድ እጅ ይቀምሳሉ:: ጀግኖቼ ማጥቃት ልምድ አላቸው በማለት ወደ እራስ እንግዳ ዘወር ብለው ምን ይመስልሃል ሲሏቸው ራስ እንግዳ "እንበለው ይህን ጉሪታም ከገባበት ገብተን እናስጓጉረው ይህን ቀፈታም ይሉና ቀደም ሲል ደጃዝማች ካሳ የፈከሩትን ፍከራ እንዲህ ሲሉ ደገሙላቸው::

"አምሣ ቢወለድ አምሳ ነው ጉዱ
መይሳው ካሣ ይበቃል አንዱ"
ብለው ከፈከሩ በኋላ ደጃዝማች ካሳን ተመለከቱ:: ደጃዝማች ካሳም ጦሬቸውን አደራጅተው "መጥቻለሁ ታጥቀው ይጠብቁኝ" ሲሉ ላኩባቸው:: ደጃዝማች ጎሹ "ይህስ ደፋር ነው መጥቻለሁ በማለት ላከብኝ ይህን ወጠጤ አይቀጡ ቅጣት እቀጣዋለሁ" አሉ:: ለደጃዝማች ጎሹ ደጃዝማች ካሳ አሽከራቸው እንደ ነበሩ ከላይ ተጠቅሶአል:: ስለሚያውቋቸው ከምንም አልቆጠሩአቸውም::

ጉራምባ ላይ ጦርነቱ ተጀመረ:: የደጃዝማች ጎሹ ኃይል ወደ ድል መቃረቡ ሲጠጋ የደጃዝማች ካሣ ጀግና ደጃዝማች ገልሞ በጉንጫቸው ጦር ሲወጋቸው ልባቸው ተሰውሮ እንደመሮጥ ሲሉ የጎጃም ጀግና አዋጊ ሴት ተመልክታ ወደ ደጃዝማች ካሳ ፊትዋን አዙራ ይህን ገጠመች::

አይሸሽም ያልከው ገልሞኮ ሸሸ፤

የደንብያን ሜዳ እያበላሽ፤
ሲሉ ደጃዝማች ካሳ ከሚወዱትና ከሚኮሩበት ጀግና መካከል ደጃዝማች ገልሞ ከፈረሱ ላይ እንዳሉ ጦራቸውን ከጉንጫቸው እየነቀሉ ደም ወርሷቸው ይመለከቱ ነበርና ለጎጃሚዋ ዘፋኝ ይህን ብለው መለሱላቸው::
"አብለሽ ነው እንጂ አልተናገርሽም፤
በዙበት እንጂ ገልሞስ አልሸሽም፤
ገልሞ የፈሪ ባላ፤
እርሱ ከሸሸ ማን ይቆማላ?"

ብለው ሲገጥሙ ደጃዝማች ገልሞ ከጉንጫቸው የገባውን ጦር ነቅለው ጣሉና የደጃዝማች ጎሹን ተዋጊ እያለፉ ከፈረስ ላይ እንዳሉ አባረው በጦር የወጋቸውን ለይተው ጣሉት:: ከዚያ በኋላማ ማን አቁሟቸው:: ደጃዝማች ገልሞ፤ የደጃዝማች ጎሹን አዋጊ ጀግና ሴት የገጠመችባቸውን ግጥም እንዲህ ሲሉ መለሱላት::

"ተይኝ አንች ሴት ደም አስክሮኛል፤
የታጠቅ አሽከር ድሉ ጠምቶኛል፤
ያነን ያጨደው ማን ይመስልሻል፤
ወጊ እንደጌታው እንደ አባ ታጠቅ፤
ሕግ አስከባሪ ደርሶ እንደመብረቅ"ሲሉ መለሱላት::

በዚህ ወቅት የደጃዝማች ጎሹ ተዋጊ ጀግና የደጃዝማች ገልሞን አድራጎት ተመልክተው ይህን ሲሉ ገጠሙ::

"የወጋውን መታው ለይቶ
የጎሹ አልሆንም ጀግና እንዲህ ሞልቶ"

በማለት ከባልንጀሮቻቸው ተለይተው የደጃዝማች ካሣ አሽከር መሆንን መረጡ:: ወዲያው ደጃዝማች ጎሹ ሞቱ:: ልጃቸው ደጃዝማች ብሩ ተማረኩ:: ጦራቸው እጁን ሰጠና ምርኮ በምርኮ ይሆን ጀመር:: በዚህ ወቅት ከላይ ደጃዝማች ካሳን አናንቀው ግጥም ገጥመው ሲያቅራሩ የነበሩት የደጃዝማች ጎሹ አዝማሪ መቅጫ ይማረኩና ወደ ደጃዝማች ካሳ ይቀርባሉ:: እርሳቸውም "ለምን ተሳደብህ" በማለት አንዴ የቃሪያ ጥፊ ሲያቀምሱአቸው የሚድኑ መስሎአቸው እንዲህ ብለው ራሳቸው ጥፋተኛ መሆናቸውን ገጠሙ::



"አወይ የእግዜር ቁጣ አወይ የአምላክ ቁጣ
አፍ ወዳጁን ያግል የሚሠራው ሲያጣ
ሽመል ይገባዋል የአዝማሪ ቀልባጣ" ሲሉ ገጥመዋል::

የደጃዝማች ጎሹ ጦር ድል መሆን ደብረታቦር ለራስ አሊ ሲነገራቸው ደነገጡ:: ቢሆንም ራሳቸው ጦር ሰብስበው ሊዘምቱ ወሰኑ:: ከ90 ሺህ ጦር በላይ አሰልፈው ደጃዝማች ካሣ ወዳሉበት ጎርጎራ ሲያመሩ የአሪንጎ አቦ አባውንት ጦሩን ተመልክተው እንዴት አይነት ሰው ቢሆን ነው ይህ ሁሉ ጦር ሊዘምት የቻለው በል!

ብለው ባልንጀራቸውን ሲጠይቁ ሌላው የደጃዝማች ካሣ አድናቂ ትንግርት ተናገሩ:: አንተው ዝም በል በዚህ ጦር ሰልፍ አትደነቅ የሚጠቃ ጦር ነው፤ ምነው ምን ሆንክብኝ በል? ግድ የለህም በእኔ ይሁንብህ ራስ አሊ ሁለተኛ ወደዚህ አይመለሱም:: ጻድቁ አቦ ያውቃሉ ቃሌ በጨርቅ ይህ ካሣ የተባለ ልጅ ኃይሉን የሰጠው እግዚአብሔር ነው! የዳዊትና የጎልያድ ጦርነት ሁኖ እንጂ እንግዲያ ያን ሁሉ ደጃዝማች ድል አድርጎ ወፍጮ ያስፈጫቸው ነበር? በእኔ ይሁንብህ የራስ አሊ ዘመን አልቋል::
ጻድቁን ስልህ! የራስ አሊ ጦር ሰልፉ እሚደነቅ
በደጃዝማች ካሣ ይመታል ድባቅ
ይህን ብለው ለባልንጀራቸው ነገሩአቸው::

<u>ስሚቸው ያልታወቀው ደራሲ</u> ገጽ 12 "ራስ አሊ የደጃዝማች ካሳ ሰዋቸው ጥቂት ሁኖ በርሳቸው ጦር ብዛት አሻግረው አዩና እንዲህ አሉ:: ሠርገኛ እንዳንለው በዛ ጦረኛ እንዳንለውም አነሰ ብለው በንቀት ተናገሩ:: ከዚህ በኋላ የመይሳው ልጅ ጦራቸውን በሥርዓት አሰልፈው መሀል ለመሀል ገቡና ይራኮቱ ጀመር:: ወዲያው የራስ አሊ ጦር ድል ሆነ ወዲያውም ራስ አሊ በፈረስ ሁነው ሸሹና የጁ ገቡ" ሲሉ ጽፈዋል:: አንድን ሰው መናቅ ጥሩ አይደለም ምክንያቱም የተናቀ ብዙ ይሠራል:: ዛሬም እንኳን በዘመናችን ሰዎች ሰዎችን ሲንቁ እንመለከታለን ይህ አግባብ አይደለም:: ራስ አሊ አሉላ ሌሎችም መኳንንቶች አጤ ቴዎድሮስን ንቀው ለውርደት በቅተዋል::

በተለይም በዚያ ጊዜ ዘጠና ሺህ ጦር በጣም ከፍተኛ ነው:: ይህ ሁሉ ጦር ይጠቃል ብሎ ያሰበ ባይኖርም ጦርነቱ ተጀምሮ 4 ሰዓት እንኳን ሳይዋጋ ድል የደጃዝማች ካሣ ሆነና ራስ አሊም አመለጡ:: ከዚያም ደራ ከተባለው ቦታ ላይ እንዱ ራስ አሊን ያዛቸው:: ሸዋ ለንጉሥ ኃይለ መለኮት ሲደርሳቸው ራስ አሊን ለማስፈታት መጡና ካስለቀቁ በኋላ ሁለቱ ሲወያዩ "ንጉሥ ኃይለ መለኮት እንጠናከርና እንውጋው በማለት ሐሳብ ሲያቀርቡ ራስ አሊ እግዚአብሔር እኛን ለመቅጣት ያመጣው በመሆኑ አንችለውምና ወደመጡበት ይመለሱ" በማለት መከሩአቸው:: ንጉሥ ኃይለ መለኮት የራስ አሊን ምክር ተቀብለው ተመለሱ:: ራስ አሊም ዋድላ ሂደው ተቀመጡ::

አሁን ለደጃዝማች ካሣ የቀራቸው አንድ ጉልበተኛ ብቻ ነበር:: እርሳቸውም ከሰሜን እስከ ምጽዋ ለብዙ ዘመን የገዙ ደጃዝማች ውቤ ኃይለማርያም ናቸው:: ደጃዝማች ውቤ፣ ከዚያ በፊት ራስ አሊን ለመውጋት ደብረታቦር ዘምተው ድል አድርገው ከቤት ሲንጎማለሉ ራስ አሊ ዋድላ ሲገቡ የሐሙስ ወንዝ ጅግና አሽከራቸው ደጃዝማች አሊጋዝ እጄን ልሰጥ መጥቻለሁ በማለት ወደ ደብረታቦር ሲመጡ ትጥቅህን ፍታ ብሎ የጠየቃቸው ባለመኖሩ ደጃዝማች ውቤን ማርኮ ራስ አሊን ቢያስፈልግ ያጣቸዋል::

አንዱ ገበያ ውሎ ወደ ቤቱ የሚመለስ ፋርጤን ሌላው ከተማ ያልዋለ ፋርጤ እንደምን ዋልክ አያ ብሎ ሰላምታ ከሰጠው በኋላ ጦርነቱ ከምን ደረሰ ብሎ ሲጠይቀው "ደጃዝማች ውቤ ተማርከዋል ራስ አሊ ጠፍተዋል "ሲለው በቅጡ አድርገህ ንገረኝ እንጂ ምነው አያ ሲለው እነሱ በቅጡ ያላደረጉትን እኔ እንዴት በቅጡ አድርጌ ላውጋህ" ብሎታል::

ደጃዝማች ውቤ ቀልጣፋ ቢሆኑም በዚህ ጦርነት ወቅት አልቀናቸውምና ለመንገሥ በማሰባቸው ጳጳስ አስመጥተው ደረስጌ ማርያምን አሠርተው የሌሎችን ደጃዝማቾች መዳከም ሲጠባበቁ ሳለ ራስ አሊ ተጠቁና ተራው የእርሳቸው ሆነ:: ደጃዝማች ካሣ ከዚህ ወዲህ እንደሚነግሡ ሙሉ በሙሉ ተማመኑና ሠራዊታቸውን ሰብስበው "ስሜን በሰሜን እነግርሃለሁ ያነን ቆፍጣጣ ደጃዝማች ውቤን እጃቸውን እንይዛቸዋለን"ብለው ካበረታቱ በኋላ ዘመቻ ወደ ሰሜን አደረጉ::



# ምዕራፍ 6

## የደጃዝማች ካሣ ዘመቻ ወደሰሜን

የደጃዝማች ካሣ ጦር ወደ ሰሜን መገስገስ እንደጀመረ ለደጃዝማች ውቤ ሲነገራቸው "ተዉት ይምጣ"እያሉ ሲፎክሩ ቀደም ሲል አስመጥተዋቸው የነበሩት ጳጳስ አባ ሰላማ እኔ ልሸምግል በማለት ወደ ደጃዝማች ካሣ ሰፈር መንገድ ሲጀምሩ ልጆች ሰብስብ ብለው ይጫወታሉ::

በወቅቱ በኢትዮጵያ ባህል መሠረት ሟርተኛ ማለት እንደዛሬው ጋዜጠኛ ዓይነት ማለት ነው:: ሟርተኛ ቃሉ የልጆች ጨዋታ ሲሆን ውሎ አድሮ ግን ወደ ጥንቆላ አስገብተውት ጠንቋይ ለማለት ሲፈልጉ ሟርተኛ ይላሉ:: በቀድሞ ጊዜ ላም ጠባቂ ሕፃናት ሲጫዎቱ የሚሉትን በስላዮቻቸው ሰብስበው ይጠቀሙበት ነበር:: በዚህ ወቅት ልጆች ላም ሲጠብቁ ሳለ ይህን ብለዋል::

"አህያ መጣች ተጭና እንጀራ፣
የውቤ ፈረስ ገባታለች ቋራ"

እያሉ ሲዘፍኑ ሰምተው ለአቡነ ሰላማ ሲነግሯቸው ደጃዝማች ካሣን ሳያዩ ገና በልጆች ሟርታ በቃሉ ትርጉም አምነውበት ሄዱ:: ደጃዝማች ካሣም ጳጳሱን በክብር ተቀብለው አነጋገሩአቸው:: ጳጳሱ የደጃዝማች ካሣን ጦርና ቆራጥነት ሲመለከቱ ወደ ደጃዝማች ውቤ ሰፈር መመለስን አልፈለጉም:: በዚህ ሁነው ወጣቱን ጅግና ለማንገሥ ፍላጎታቸው ሆነ:: ከግብጽ የሚመጡት ጳጳሳት በእጃቸው ባርከው ካነገሡ በታሪክ እንደማይረሱ ያምናሉ:: ደግሞም እኔ ያነገሥኩህ ነኝ በማለት የፈለጋቸውን የሚሠሩ ናቸው::

ይህን ቀደም ብለው ስለሚያውቁ ከደጃዝማች ካሣ ጋር የተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማጠናከር እምነታቸው እንደሆነ ጳጳሱ ለማስረዳት ሲሞክሩ ደጃዝማች ካሣ ይበልጥ በተዋሕዶ ሃይማኖት መዳከም

የተበሳጩ መሆናቸውንና ጥሩም ተማሪ የነበሩ መሆናቸውን ሲመለከቱ ደጃዝማች ውቤን ከድተው የደጃዝማች ካሣ ደጋፊ ሆኑ።

ደጃዝማች ካሣ ለደጃዝማች ውቤ እጃቸውን እንዲሰጡ ሲልኩባቸው "ይህ ልጅ ምን ይላል እንዴት ሳልዋጋ እጄን እሰጣለሁ"አሉና ለጦርነት ይዘጋጁ ጀመር። ደጃዝማች ውቤ ከራስ ገብሬ የሚወለዱ በመሆናቸው ለእርሳቸው ይህ ቃል የሚዋጥላቸው አይደለም። በቃላቸው መሠረት ጦራቸውን ሰብስበው ደጃዝማች ካሣን ይጠባበቁ ጀመር። ጦርነቱ ተጀምሮ ብዙም ሳይቆይ ደጃዝማች ውቤ ተማርከው ከደጃዝማች ካሣ ፊት ቀረቡ።

"ከሰሜን ቀይ ባሕር የገዛው መኳንንት፣
አሉኝ ተማረከ በኩል ቀን ጦርነት"

ተብሏል። የደጃዝማች ውቤና የደጃዝማች ካሣን ጦርነት አስመልክቶ በወቅቱ የአጤ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል ጸሐፊዎች የጦርነቱን ታሪክ እያንዳንዳቸው አስፍረውታል። ምንም እንኳን ጦርነት መጥፎ ቢሆንም ቅሉ ታሪክ ነውና ተጽፏል መጻፍም አለበት። ታዲያ ስማቸው ያልታወቀው ጸሐፊ እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል።

<u>ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ</u> ገጽ 13 "የመይሳው ልጅም ከአምባ ጫራ ተጉዘው ወገራ ሰፈሩ። ከዚያው ሁነውም ደጃች ውቤን በፍቅር ይግቡ ብለው ላኩ። ከዝያ በኋላ ደጃች ውቤም አልገባም ብለው ወደ ደጃች ካሣ ላኩ። ከዝያ በኋላ ደጃች ካሣ ከወገራ ወደ ሰሜን ተጓዙ፡ አባ ማሬ ውቤም በሰሜን ደረስጌ ወገን ተሰልፈው ቆይተው ተታኩሱ በስከ ወዲያው ቆስለው ተማረኩ። ልጃቸውም ደጃች ጓንጓልና ደጃች ካሣ ተማረኩ።"

"ደጃች ውቤን የማረከው ሰው ወደ ደጃች ካሣ ይዞአቸው ሄደና እጅ ነሥቶ እንኳ ቀናዎ አለ። እሳቱ የመይሳው ልጅ ወዲያው ደጃች ውቤን እንዲህ ብለው ወረፍዋቸው። አንተ ቁርጥማታም ሽማግሌ በክብር ግባ ብየ ብልክብህ ምን ብለህ ሰደብከኝ አሁንም ቶሎ ነፍጤንና ገንዘቤን አግባ አልዋቸው"ይሉና ገጽ 14 "ከዚያ ወዲያ ደጃች ውቤን ድል አድርገው ወዲያው በሰሜን ደብረ ጽጌ ድል ባደረጉ በሶስተኛው ቀን በየካቲት 3 ነገሡ" ሲሉ ጽፈዋል።



አለቃ ወልደ ማርያም <u>የዳግማዊ ቴዎድሮስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋ ገጽ 5 "በመጋቢት በ3 ቀን ዓርብ ማታ ሁኖ አለና ደጃች ካሣ አያሳድረኝ ይህን ቁርጥማታም አላሳድረው ብለው ፊትውራሪውን ገጠሙት ድል አደረገት። በኋላ ግን የደጃች ካሳ ጦር ተመልሶ ገጠመ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ለደጃች ካሳ ረድቶአልና ሁሉም ድል ሆነ ደጃች ውቤም ተያዙ" ሲሉ ጽፈዋል።

አለቃ ወልደ ማርያም የመጀመሪያው ጦርት በመጋቢት ሲሉ ደብተራ ዘነብ ደግሞ በየካቲት 3 ቀን ብለዋል። በሁለቱ ደራስያን መካከል የአንድ ወር ልዩነት ሲኖር ሌሎች ደራስያን ግን የደብተራ ዘነብን ደግፈው የካቲት 3 ቀን መሆኑን ጽፈዋል።

<u>ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስን ታሪክ</u> የጻፉት ሊትማን ያሳተመው ገጽ 17" በየካቲት 3 ቀን ደጃች ካሣ ሂደው ደጃዝማች ውቤም ቦታው ቧሂት ድንኳን በተከሉ ጊዜ የእንግሊዙን ሊቀ መኳስ ዮሐንስን ደጃዝማች ካሣ በመነጸር አይተህ ንገረኝ አሉት። የሸማ ድንኳን ባየ ጊዜ ነገራቸው ደጃች ካሣም እንዲህ አሉ፡ አላሳድረውም ያን ጊዜውንም ተነሣ አሉ። ባሳለፉትም ጊዜ እንዲህ ብለው በፍከራ ተናገሩ። እንኳን ይህን ቁርጥማታም ወሎን ወግቼ የሸዋውን ንጉሥ እይዘዋለሁ። ስሜን በሰሜን እንግርሃለሁ ያልሁህ ወታደር ስሜ ቴዎድሮስ ነው አሉ።"

"አዕቀድመው ገና በንጉሥ አምላክ በል ስሜን እነግርሃለሁ ብለው ነበርና ያን ጊዜውን እንዲህ አለ። ወታደር አይዞህ አትፍራ የውቤ ነፍጥ ቢሉህ የተለጎመው ጨርቅና ባሩድ ነው። አይነካህም አሉት። እኔ የክርስቶስ ባርያ ሁሉንም አሳይሃለሁ ወታደር ባሉት ጊዜ ሰልፉ ገጠመ ከንጉሥ ቴዎድሮስ በጅሮንድ አየለ አዛዥ እሸቱ ጥቂት ሰው ሞተ። ከደጃዝማች ውቤም ደጃዝማች እሸቱ ልጃቸው ደጃዝማች ማጠንቱ ብዙ መኳንንት ሞቱ። ደጃዝማች ውቤም ተያዙ። በየካቲት 5 ቀን ነገሡ። ዘውድ ጫኑ፣ ደረስጌ ማርያም ላይ በእግዚአብሔር ፈቃድ አቡነ ሰላማ ቀብተዋቸው ነገሡ። ንጉሥ ቴዎድሮስ ተባሉ" ሲሉ ጽፈዋል።

ደጃዝማች ካሳ በሰላም እጅዎን ይስጡ ብየዎት እምቢ በማለትዎ እነሆ ይህን ውርደት ተቀበሉ አሁንም ያለወትን ንብረት አስረክቡኝ በማለት ጠየቁአቸው። ደጃዝማች ውቤ ምንም የለኝም ወታደሬ

በእጄ የያዘው ካልሆነ በቀር ሌላ ንብረት የለኝም አሉ:: ደጃዝማች ካሣ የደጃዝማች ውቤን ንፉግነት ሰምተው ነበርና "ደጃዝማች እንኳን ንብረትዎ እርስዎ በእጅ ስለሆኑ ቢያስረክቡኝ ይሻላል በማለት ቢጠይቁአቸው የለኝም አሉአቸው::

የደጃዝማች ካሣ ወታደር በዋሻ የተደበቀውን ንብረት ሲፈትሽ ገንዘቡን ብቻ ሳይሆን በጋን መርፌ ሞልቶ ተገኘ:: ደጃዝማች ካሣ ደጃችማች ውቤን አስጠሩና "ንብረት የለኝም ብለውኝ ነበር ይህ የማነው? ሲሉ ጠየቋቸው ደጃዝማች ውቤም "ለክፉ ቀን ይሆናል ብዬ ነው" ሲሉአቸው ደጃዝማች ካሣ "ቆፍጣጣ ከዛሬ ወዲያ ምን ክፉ ቀን አለ ለክፉ ቀን ያስቀመጡትን መጠቀም ከተቻለ ምን ክፉ ቀን አለ" አሉአቸው::

የደጃዝማች ውቤ አሽከሮች ለሽምግልና ቀደም ከአቡነ ሰላማ ጋር ሁነው ሲመላለሱ የነበሩ እየፈከሩ ወደ ደጃዝማች ካሣ መጡና "እኛ ልንሸለም ይገባናል:: ምክንያቱም የደጃዝማች ውቤ ጦር ድል እንዲሆን አስተዋጽኦ አድርገናል ይህን ያደረግነው እርስዎን ለመርዳት ብለን ነው" አሉ:: ደጃዝማች ካሣ "እኔ ጌታውን ከከዳ አሽከር ጋር አንድነት የለኝም እሰረው ከጌታው ጋር" ሲሉ አዋረዱአቸው:: ፊታውራሪ ኮከቤ እንዲያውም በደጃዝማች ካሣ የቃሪያ ጥፊ ቀመሱና ወደ እስር ቤት ተወረወሩ::

## ምዕራፍ 7

## ከደጃዝማችነት ወደ አጤነት

ደጃዝማች ካሣ የቀራቸው ዘውድ መጫን ሲሆን ይህን ለማድረግ የጎደላቸው ነገር ባለመኖሩ ደጃዝማች ውቤ ባሠሩት ቤተ ክርስቲያን ደረስጌ ማርያም በአቡነ ሰላማ እጅ እሁድ የካቲት 5 ቀን 1845 ዓ.ም ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ተብለው ጎንደር ክፍለ ሀገር ሰሜን አውራጃ ጃናሞራ ወረዳ ደረስጌ ማርያም ላይ ነገሡ:: የነገሡበትን ቦታ አንድ የውጭ አገር ደራሲ አድዋ ነው በማለት ጽፏል::

ኮራዶ ዞሊ የጻፈው ትርጉም ዘሪሁን <u>ገብሬ የኢትዮጵያ ታሪክ</u> ከአጼ ናኦድ እስከ አልጋወራሽ ራስ ተፈሪ መኮንን በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 100 "ከዚህ በኋላ ደጃዝማች ካሣ ኃይሉ ጠላቶቻቸውን ሁሉ



አሸንፈው ካስገበሩ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ወደ አድዋ ከተማ ሄደው ከዚያ በፊት ለአንድ መቶ ዓመታት ያህል ዝናዋ ጨርሶ ጠፍቶ በነበረውና በወቅቱ ክብርዋ ተመልሶላት በነበረችው ቤተክርስቲያን ውስጥ በአቡነ ሰላማ እጅ ቴዎድሮስ 2ኛ በመባል የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ጫኑ" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህን ታሪክ ከዚህ ላይ ልጠቅስበት የፈለኩት ምክንያቱ ትክክል ባለመሆኑ ነው:: አጤ ቴዎድሮስ የነገሡት ደረስጌ ማርያም እንጂ አድዋ አይደለም:: ደራሲው ባለማወቅ ይሁን በሴረኝነት ባይታወቅም ተርጓሚዎች በቅንፍ ማስቀመጥ ነበረባቸው:: እንባቢ የዚህ ዓይነት የታሪክ ሰባራ ሲፈጠር ወዲያው ካልታረመ ውሎ ካደረ "ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል" እንደሚባለው ስለሆነ መታረም አለበት::

አጤ ቴዎድሮስ የነገሡ ደረስጌ ማርያም ላይ መሆኑን ብዙት ያላቸው የታሪክ መጻሕፍት መደርደር ይቻላል:: ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ በወቅቱ አብረው የነበሩ ናቸው:: ሌሎች ሁለቱ ጸሐፊዎች ማለትም አለቃ ወልደማርያምና ደብተራ ዘነብ ከአጤ ቴዎድሮስ ጋር የተገናኙት ታኅሣስ 1848 ዓም አቤቶ ምኒልክን ይዘው ከሸዋ ወደ ጎንደር ሲመጡ ነው:: እነዚህ ከሸዋ የመጡ ደራስያን አጤ ቴዎድሮስ የነገሡት ሰሜን ደረስጌ ማርያም መሆኑን ጽፈዋል:: ሌሎችም የታሪክ መጽሕፍት መጨመር ይቻላል::

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 138 "በደረስጌ ማርያም ዕጨጌው በግራ ጳጳሱ በቀኝ ተቀምጠው መጽሐፈ ተክሊል እየተነበበ በአቡነ ሰላማ እጅ ሥርዓተ መንግሥት ተደረገላቸው" ሲሉ ክቡር አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ጽፈዋል::

<u>ርእሰ አድባራት ወገዳማት ጽርሐ ጽዮን ቅድስት ደረስጌ ማርያም</u> የተባለው መጣጥፍ ገጽ 2 "መሳፍንቱ በማያቋርጥ የርስ በርስ ጦርነት ምክንያት በሀገሪቱ ላይ በደረሰው ከፍተኛ የመከፋፈልና የእርስ በርስ ጦርነት በተፋፋመበት ጊዜ በዚህ ጎን ለጎን የቱርኮች፤የግብጾች፤ የሌሎችም ወረራ በሚያሰጋበት ወቅት ሳይታሰቡ ካንዲት ወረዳ ከቋራ ተነሥተው ለመከፋፈሉ ደንበኛ ምክንያት የሆኑትን መሳፍንት በማሸነፍ አንደኛ የሀገር አንድነትን ሁለተኛ የማዕከላዊ መንግሥትን

ለማቋቋም አጤ ቴዎድሮስ የነገሡት በዚ.ች በጽርሐ ጽዮን ቅድስት ደረስጌ ማርያም ነው" ሲል ጽፏል።

አቤ ጎበኛ አንድ ለናቱ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 414 " ደጃዝማች ካሣ ይህን ሁሉ ድል ካደረጉ በኋላ ከዋናው ግባቸው ከመድረስ የሚያግዳቸው ምክንያት ስላልነበራቸው ደጃች ውቤ ለመናገሻነት ተጨንቀው ባሠሩት የደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በአቡነ ሰላማ እጅ ተቀብተው እጅግ ከፍ ባለ ግርማና ድምቀት ዘውድ ጫኑ" ሲሉ ጽፈዋል።

ጳውሎስ ኞኞ አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 78 "ደጃዝማች ካሣ ደጃች ውቤን ድል ካደረጉ በኋላ በዚያው በየካቲት ወር 1845 ዓም አጤ ቴዎድሮስ ተብለው በደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ እጅ ነገሡ" ሲሉ ጽፈዋል።

ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ዘውድ እንደጫኑ ታሪካዊ ንግግር አድርገዋል። በነገሡ ቀን የተናገሩትን ንግግር ብዛት ያላቸው ደራስያን አልጠቀሱትም። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሰው የአቶ አቤ ጎበኛ መጽሐፍና የመሪ ራስ ኤ.ኤም አማን በላይ አስፋው አሊ ይመር መጽሐፍ ዘግቦታል።

አስፋው አሊ ይመር ቁስለኛዋ አገር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ162 ላይ አጠር አድርገው የነገሡ ቀን ያደረጉትን ንግግር ዘግበውታል። ሌላው ታሪካዊነቱ ተመሳሳይ ይሁን እንጂ የቃላት ልዩነት አድርጎ የጻፈው አቤ ጎበኛ ነው። ይህም አንድ ለእናቱ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 416-419 ተጠቅሷል። ሌላው የታሪክ መጽሐፍ የነገሡ ቀን የተናገሩትን ዘርዘር አድርጎ የጻፈው የትናንትናዋ የኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ የተባለው መጽሐፍ ነው። ለዚህም ሙሉውን ገልብጨዋለሁ።

መሪ.ራስ.ኤ. ኤም በላይ የትናንትናዋ ኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 260-262 "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤አንድ አምላክ በሆነ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምኜ አብን ወላዲ ወልድን ተወላዲ መንፈስ ቅዱስን ሰራጺ ብዬ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ጸንቼ ኢትዮጵያ ሀገሬን ላገለግልና በሕዝቦችዋ ላይ የተበላሸውን አስተዳደር አስወግጄ



ትክክለኛ የሆነውን ፍርድ ልሰጥ እኔ ቴዎድሮስ ቃል ኪዳን ገብቻለሁ። ለዚህ ቃል ኪዳን ረዳቴ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!አምላክህ አምላኬ ድሌ ድልህ የአንተው የእኔ የእኔ የአንተ ክብር ነው።"

"የኢትዮጵያ አምላክ እኔን ሲያስነሣኝ በእርሱ ኃይል ክንዴን አጠንክሮ የኢትዮጵያን ጠላት ከምድረ ገጽዋ ሳጠፋውና የተስተካከለ ፍርድና ሕግ ያጣውን ሕዝቧን ሳደራጅና ስመራ ከዳር እስከዳር አንድ ሳደርገው አምላካችን እንደላከኝ ያን ጊዜ ቴዎድሮስ መሆኔን ፈጽመህ ታውቃለህ።"

"ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግና የጥንቱን ገናና መንግሥት መልሶ ለማቋቋም በማደርገው ተጋድሎ ያገኘነው ነገም የምናገኘው ድልና ሥራ ይመሰክራል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! አንተ ለአቋቋምከው መንግሥትና ለአነገሥከው ንጉሥ ተገቢውን ግብር እንድትከፍል ሕግ ይወስንብሃል። "ይህ ያቋቋምከው መንግሥት አንተን ኢትዮጵያዊውን እንዲያገለግልና እንዲጠብቅ ለመለመልከው ወታደር (ነፍጠኛ)ስንቅና ቀለቡ ሳይጓደል እንዲሰፈርለት።"

"ከዚያም ሌላ መተዳደሪያ የሚሆን አበል እንዲሰጠው እንጂ በአንተ ላይ እንዳለፈው የመሳፍንት ጭፍራ ዘረፋና ተፅዕኖ እንዳያደርስብህ ይደረጋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ከአሁን በፊት ስትገድል ስትቀማ ቤት ስታቃጥል፤በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረውን ወንድምህን ባርያ አድርገህ ስትሸጥና ስትገዛ የነበርከ ከአሁን በፊት ስለተሳሳትከው ምሕረት ተደርጎልሃል ወደ ቤትህና ወደ ሀገርህ በሰላም ተመልሰህ በግብርናህና በእጅ ሞያህ በእየአባትህ ተሰማርተህ እንድትኖር።"

"ስለዚህ ያለፈውን ወንጀልህን ሳላይ የሚመጣውን በማስተዋል ሙሉ ምሕረት ተደርጎልሃል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ይህ አዋጅ ከተነገረህና እግዚአብሔር ያነገሠው ንጉሠ ነገሥትህ ቴዎድሮስ ከነገሡበት ጀምሮ ወደ ቤትህ ሳትመለስ በሽፍትነት ሁነህ የምትቀማና ወንድምህን አድብተህ የምትገድል ባሪያ ብለህ ሰውን የሸጥክና የገዛህ እንደ አውሬ ታድነህ ተይዘህ በአደባባይ እጅና እግርህ ፈጽሞ እንዲቆረጥና ርኀራኄ እንደማይደረግልህ እወቅ። ለተጣለብህ ቅጣት አንተ እንጂ የሚቀጣህ ንጉሕ ነው። የኢትዮጵያ

ሕዝብ ሆይ!ትናትናና ከትናንትና ወዲህ ባሪያ ብቻ ሳይሆን ለሥልጣን ለሹመት ሲባል ሴት ልጅህን ሸጠሃል::"

"በገንዘብ ቀይረሃታል አንተም አንድ ስትሆን ሁለት ሴት ይዘሃል ከእንግዲህ ግን ይህ ቃል ተስተካክሎ በሕግ እስኪጸድቅና እስኪታወጅልህ ድረስ እንድታስብበትና እንድትመርጥ ቀን ሰጥቼሃለሁ:: ነገር ግን ከዚያች ቀን ጀምሮ ባሪያ ተብሎ በግድ ከጌታው ቤት ሲያገለግል የተገኘበት ሴት ልጁ ሳትወድ ተገዳ በክርስቲያን ቤት ሁለተኛ ሚስት ሁና የተገኘችበት ወዮለት::"

"ይሄን ሕግ ልደነግግ የተበላሸውን ሥርዓት ልጠርግ ግዴታየና የመጀመሪያው ዓላማየ ነው:: ይሄንም ላደርግ የሚገባኝና የሚፈጽምልኝ ቅዱስ አምላኬ ነው አሜን ወአሜን" ብለው መናገራቸውን ጽፈዋል::

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አጤ ቴዎድሮስ የነበሩአቸውን ቁባቶች አሰናብተው ከእቴጌ ተዋበች አሊ ጋር በሥጋ ወደሙ ተወስነው መኖር ጀመሩ:: አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ብቻ መኖር እንዳለበት ራሳቸው በመጀመራቸው ሌሎች መኳንንቶች ይህን ሕግ ተቀብለው የነበሩአቸውን ቁባቶች ሁሉ አሰናበቱ" ሲሉ አላማቸውን የነገሡ ቀን የተናገሩትን ከታሪክ ሠነድ አገኘሁ ሲሉ ዘርዝረው ጽፈዋል::

## ምዕራፍ 8

### አጤ ቴዎድሮስ የነገሡበት ዓመት መለያየት!

አጤ ቴዎድሮስ የነገሡበትን ቀንና ዓመት አስመልክቶ የተለያዩ ዓመታት የጠቀሱ ደራስያን ብዙ ናቸው:: ይህን በማስመልከት በዛ ብሎ ዘርዘር ተደርጎ ለመጣፍ ያስፈለገበት ምክንያት አለ:: አንዳንድ ደራስያን ባለማስተዋል ይሁን በግድየለሽነት የጻፉት ትክክል ስላልሆነ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ለማስተካከል ጥረት አድርገዋል::

በእርሳቸው ጥናት መሠረት አጤ ቴዎድሮስ የነገሡት የካቲት 5 ቀን 1845 ዓም መሆኑን የታሪክ መጻሕፍት ዋቢ ጠቅሰው ጽፈዋል:: እኔም እርሳቸው በጀመሩትና እርሳቸው ያላገኙአቸውን የታሪክ



መጻሕፍት በመንተራስ አጤ ቴዎድሮስ የካቲት 5 ቀን 1845 ዓም ነገሡ ብዬ ተቀብዬ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የታሪክ መጻሕፍት ዋቢ በማድረግ አቅርቤአለሁ::

<u>ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ</u> ገጽ 14 "የኢትዮጵያ መንግሥት በቀረ በ70 ዓመት ከዚህ በኋላ በነገሡት" ሲሉ ጽፈዋል:: ከ1761 ዓም እስከ 1845 ዓም ድረስ 70 ዓመት ሲቀነስ 70 ዓመት ብቻ አይሆንም:: ስለዚህ የኒህ ሰው አጻጻፍ የትኛውን ዓመት መውሰድ እንዳለብን አይገልጽም:: አጤ ኢዮአስ በሻሽ ታንቀው የተገደሉት ግንቦት 8 ቀን በ1761 ዓም ነው::

ታዲያ በኢትዮጵያ ዘመነ መሳፍንት የተመሠረተው እርሳቸው ከሞቱ በኋላ ነው:: በነገራችን ጎንደር ከከተማ የማይወጡ ግንብ ጠባቂ ነገሥታት ሁሌም ነበሩ:: ደጃዝማች ካሳ የማረኳቸው 3ኛው አጤ ዮሐንስ ነበሩ:: ሥልጣኑ የመሳፍንት ነው እንጂ ዘውዱ እኮ ሁሌም ከጎንደር አልተየለም ነበር:: ስለዚህ እኒህ ደራሲ አጤ ቴዎድሮስ የነገሡበትን ቀን በእኔ እምነት በትክክል አልገለጹም::

<u>ደብተራ ዘነብ የቴዎድሮስ</u> ታሪክ ሊትማን ያሳተመው ገጽ 12 "ንጉሥ በጠፋ በ71 ዘመን እግዚአብሔር ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሣ:: (የኦሮሞዎች)የጋሎች ግዛት በበጌምድር በጎጃም፤በላስታ በየጁ፤በወሎ ከዚህ ነው ያለቀው" ሲሉ ጽፈዋል::

የደብተራ ዘነብ ከላይኛው ደራሲ ጋር በአንድ ዓመት ይለይ እንጅ የትኛውን ቁጥር እንደያዙት ለእኔ ግልጽ አይደለም:: ከዚህ በታች ደግሞ አቶ ጳውሎስ ኞኞ አመሳክረው በጻፉት ላይ እኔም እርሳቸው ያላገኙአቸውን የታሪክ መጻሕፍት ጨምሬ ለማስረዳት ልሞክር ቅድሚያ ወደ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ትንታኔ::

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፋ ገጽ 78 "ደጃዝማች ካሣ ደጃች ውቤን ድል ካደረጉ በኋላ በዚያው በየካቲት ወር 1845 ዓም አጤ ቴዎድሮስ ተብለው በደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ እጅ ተቀብተው ነገሡ፤ ቴዎድሮስ የነገሡበትን ዘመን በደብተራ ዘነበና በአለቃ ወልደ ማርያም በጻፉት ታሪክ በ1847 ዓም ነው ይላሉ:: አለቃ ተክለ ኢየሱስ ግን በ1845 ዓም ነው ብለው ጽፈዋል:: በእነዚህ መጻሕፍት የሁለት ዓመት ልዩነት አለ::"

“እንደነደብተራ ዘነበና አለቃ ወልደማርያም ዘመን አገላለጽ ከሆነ ቴዎድሮስ የነገሡት 13 ዓመት መሆኑ ነው:: አለቃ ታዩ አጤ ቴዎድሮስ 15 ዓመት ነገሡ ስለሚሉ የነገሡበት ዘመን ከአለቃ ተክለ ኢየሱስ ትረካ ጋር ይጋጫል:: አቶ መንግሥቱ ለማ የአባታቸውን የአለቃ ለማን ትረካ በጻፉበት መጻሕፍት ትዝታ ውስጥ ቴዎድሮስ በ1845 ዓም ነግሠው በ1860 ዓም ሞቱ ይላሉ:: ባላምባራስ ማኅተመ ሥላሴም በዝክረ ነገር መጽሐፋቸው በ1845 ዓም ነገሡ ይላሉ:: ስለዚህ እኔም አብዛኛዎቹ በተናገሩት በ1845 ዓም ነገሡ ብያለሁ ”ሲሉ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ጽፈዋል::

እነዚህ 2 ደራሲዎች አጤ ቴዎድሮስ ሲነግሡ በአካባቢው አልነበሩም:: ወደ አጤው የመጡት አጤ ቴዎድሮስ ሸዋን አስገብረው አቤቶ ምኒልክን ይዘው ሲመጡ የመጡ ናቸው:: ከእነዚህ ሁለቱ ደራስያን መካከል አለቃ ዘነብ፣የአጤ ቴዎድሮስን ታሪክ የጣፉት አጤው ከሞቱ ከ10 ዓመት በኋላ ነው:: ደብተራ ዘነበ የእንግሊዝ ወታደር እስከ ግብጽ ወስዷቸው ስለነበር የጻፉትም አሌክሳንደርያ ግብጽ ሁነው ነው::

በዚህ ምክንያት ዘንግተውት ይሆናል እንጂ ደብተራ ዘነብ ሆኑ አለቃ ወልደ ማርያም አጤ ቴዎድሮስን ከመጥላት የተነሣ ታሪክ ለመቀነስ አስበው አይመስለኝም:: አጤ ቴዎድሮስ የነገሡበትን ዘመን አስመልክቶ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ሳያገኙአቸው ከቀሩት ሰነዶች እርሳቸው ካልጠቀሷቸው የታሪክ መጻሕፍት የእርሳቸውን ትረካ የሚደግፉ ሰነዶች እኔም ጀባ ልበል::

1ኛ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ታሪክ ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በተባለው መጽሐፍ ገጽ 125 “ባጼ ቴዎድሮስ 15 ዓመት ባጼ ተክለ ጊዮርጊስ 3 ዓመት ባጼ ዮሐንስ 18 ዓመት የቆየችው መንግሥት ከዳዊት ከሰሎሞን ከምኒልክ ገባች” ብለዋል::

2ኛ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ዋዜማ፣ በማግሥቱ የኢትዮጵያ ነገሥታት የታሪክ በዓል ለማክበር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 51 “አጤ ቴዎድሮስ 15 ከ1845-1860” ሲሉ ጽፈዋል::



3ኛ የጎንደር ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ አንጻር በተባለው መጽሐፉ ገጽ 259 “የአጤ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ከ1845-1860 ዓም” ሲሉ ጽፈዋል::

4ኛ በላይ ግደይ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 175 “ቴዎድሮስ ጀግና ንጉሥ ስለነበር በዚህ የተነሣ ከ1845-1860 ዓም በነበራቸው የ15 ዓመት መንግሥት ኢትዮጵያን እንደ ጥንቱ በአንድ ንጉሠ ነገሥት ሥር ተጠቃላ ለመተዳደር አበቃት” ሲሉ ጽፈዋል::

5ኛ በላይ ግደይ ኢትዮጵያ ሀገሬና ትዝታዬ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 150“ አጤ ቴዎድሮስ 1845-1860 ዓም በመሳፍንት አገዛዝ ተበታትና የኖረችውን ኢትዮጵያ አንድ አድርገው በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ለማስተዳደር በመጣራቸው ከፍተኛ አድናቆትን ያተረፉ ታላቅ መሪ ከመሆናቸው በላይ ጥቅም ሳያስቡና የድሎት ኑሮን ከምንም ሳይቆጥሩት እንደ አንድ ተራ ወታደር ከቦታ ቦታ እየተንከራተቱ በዋሻና በድንኳን እያደሩ ትውልድን የሚያኮራ ተግባር መፈጸማቸው በታሪክ የተመሰከረ ሐቅ ነው” ይሉና “አክሱም፣ጎንደር፣ ላሊበላ፣ በተባለው መጽሐፋቸውም “ለ15 ዓመት”መንገሣቸውን ጽፈዋል::

6ኛ ብርሃኑ ድንቄ የኢትዮጵያ አጭር ታሪክ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 55 “አጤ ቴዎድሮስ በጊዜያቸው የነበሩትን ኃይለኞች ካሸነፉ በኋላ የንጉሥ ተወላጅነት ሳያስፈልጋቸው የንጉሠ ነገሥቱን ዘውድ በኃይላቸው ብቻ ተቀዳጅተው የተከፋፈለችውን ግዛት አንድ አድረገው ኢትዮጵያን 15 ዓመት ገዙ“ሲሉ ጽፈዋል::

7ኛ መኮንን አበበ አንድነት በተባለው መጽሐፍቸው ገጽ 60 “አጤ ቴዎድሮስ በ1845 ዓም ነገሡና በመሳፍንት የተከፋፈለች ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥትና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር 15 ዓመት ከጣሩ በኋላ ከእንግሊዞች ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ሽጉጣቸውን ጠጥተው አረፉ” ሲሉ ጽፈዋል::

8ኛ አለቃ ኤልያስ ነቢየልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት በወርኃ የካቲት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 3 “ጀግናው አጤ ቴዎድሮስ በ1845 ዓም የካቲት 5 ቀን በዕለተ እሑድ ሰሜን በምትገኘው

በደረስጌ ማርያም ጽርሐ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነገሡ" ሲሉ ጽፈዋል።

9ኛ ጥላሁን ብርሃን ሥላሴ ቤተ የ<u>20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ አንደኛ መጽሐፍ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 7 "አጤ ቴዎድሮስ አባ ታጠቅ በ1845 ዓም ነገሡ" ሲሉ ጽፈዋል።

10ኛ መሪጌታ አእምሮ በሪሁን <u>የኢትዮጵያ ፊደል ታሪክ እና ክፍለ ዘመን</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 115 "አጤ ቴዎድሮስ 2ኛ ጎንደር ደብረታቦር 15 ዓመት 1845-1860"ሲሉ ጽፈዋል።

11ኛ ዲ.ን ዳንኤል ክብረት <u>የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 425 "ደጃዝማች ውቤ ዘመነ መሳፍንትን አክትመው ለመንገሥ ያስቡ ስለነበር ደረስጌ ማርያምን ለሥርዓተ ንግሣቸው ጭምር አዘጋጅተዋት ነበር። ይሁን እንጂ የካቲት ሦስት ቀን 1845 ዓም ከደጃዝማች ካሣ/በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ጋር ቧሂት ላይ ባደረጉት ጦርነት ተሸነፉ3፡ አጤ ቴዎድሮስም ደጃዝማች ውቤ ባሠሯት ደብርና ባዘጋጁት አልባሳት ሥርዓተ ንግሣቸውን በደረስጌ ማርያም አከናወኑ" ሲሉ ጽፈዋል።

12ኛ አባ ዘሐቅለ ዋለ. <u>ታሪክህንና ሃይማኖትህን እወቅ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 34 "አጤ ቴዎድሮስ በ1845 ዓም ነገሡና በመሳፍንት የተከፋፈለች ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥትና የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ለ15 ዓመት ከጣሩ በኋላ ከእንግሊዞች ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ሽጉጣቸውን ጠጥተው አረፉ። ዘመናቸውም ከ1845-1860 ዓም ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

13ኛ ዘማሪ ዲ/ን ወንድወሰን ተገኝ <u>ጎንደር ጥንታዊ ታሪኳ</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 45 "አጤ ቴዎድሮስ ቋረኛው  አባ ታጠቅ 15 ዓመት 1845-1860" ሲሉ ጽፈዋል።

14ኛ ቀሲስ ከፍያለው መራሒ. <u>ምንትዋብ</u> በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 26 "በኢትዮጵያ ለሰባ ሁለት ዓመት ያህል ማለት ከፍጻሜ መንግሥት ተክለ ጊዮርጊስ እስከ ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ (1773-1845 ዓም)በኢትዮጵያ ማዕከላዊ አስተዳደር ተዳክሞ ኢትዮጵያ



በተበታተነ ሁኔታ በመሳፍንት (በባላባት)ስትመራ ከኖረች በኋላ በዘመነ መሳፍንት መጨረሻ ላይ የተበታተነች ኢትዮጵያን አንድ እንዲያደርጉ የታፈረችና የተከበረች አንዲት ጠንካራ ኢትዮጵያን መልሶ ለመገንባት የኢትዮጵያ አምላክ ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስን አስነሣ"ሲሉ ጽፈዋል።

15ኛ መምህር ቡሩክ ገብረ ሊባኖስ <u>ማደስ ወይስ ማፍረስ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 30 "አጤ ቴዎድሮስ 1845-1860 ፍላጎታቸው ኢትዮጵያን በቴክኖሎጂ ለማበልጸግ ስለነበር በኢትዮጵያ የነበሩትን የአውሮፓ ሚሲዮናውያንን ሁሉ ከያሉበት ለቃቅመው ከጋፋት የጦር መሣሪያ እንዲያመርቱ አድርገዋቸው ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

<u>16ኛ ደብረታቦር ዳግማዊ ቴዎድሮስ</u> ት/ቤት የ50ኛ ዓመት በዓል መጽሔት ገጽ 7 "ደጃዝማች ካሣ የሰሜኑን ደጃች ውቤን ድል ካደረጉ በኋላ በየካቲት ወር በ1845 ዓም አጤ ቴዎድሮስ በሚል ስም በደረስጌ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነው በአቡነ ሰላማ እጅ ዘውድ ደፍተዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

<u>17ኛ የየካ ደብረ ሣሕል ሚካኤል የ1660 ዓመት ታሪክና</u> የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልማት ዕቅድ በተባለው መጽሔት ገጽ 36 "አጤ ቴዎድሮስ በ1845 ዓም ነገሡና በመሳፍንት የተከፋፈለች ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥትና የበለጸገች ኢትዮጵያ ለመፍጠር ለ15 ዓመት ከጣሩ በኋላ ከእንግሊዞች ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ሽጉጣቸውን ጠጥተው ዐረፉ"ሲል ጽፏል።

18ኛ..ተክሌ ዮኋላ <u>ጀርመን ሬዲዮን</u> በ1999 ዓም የአማርኛ ቋንቋ ዘጋቢ ጋዜጠኛ "ደጃዝማች ካሳ አጤ ቴዎድሮስ የነገሡት የካቲት 5 ቀን 1845 ዓም ሲሆን" ሲሉ ጽፈዋል።

19 ልሳነ ሕዝብ መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 8 መጋቢት 1996 ዓም ገጽ 25 "ባለፉት 151 ዓመታት (ከ1845-1860) ከአጤ ቴዎድሮስ እስከዛሬው የኢሕአዴግ መንግሥት 13 የሥርዓትና የመንግሥት ሥልጣን ሽግግር ተደርጓል" ሲል ጽፏል።

20ኛ ገዘሙ ሀብተየስ ምኒልክ መጽሔት ሐምሌ 1993 ዓም ገጽ 14 "ቴዎድሮስ 2ኛ 1845-1860 ዓም" ሲሉ ጽፈዋል::

21ኛ ብርወርቅ ታየ ገናናው ጋዜጣ መጋቢት 25 ቀን 1990 ዓም ገጽ 7 "በተወለዱ 50 ዓመታቸው በነገሡ 15ኛው ዓመታቸው ታሪካዊ ሥራቸው ያበቃው ካሣ ኃይሉ ቴዎድሮስ በዚህች ሀገር ላይ የገነነ ታሪክ ባለቤት ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

አንባአብያን 15 ዓመት ነው የነገሡ የሚሉት ደራስያን ቁጥር ከዚህ በላይ የዘረዘርኩአቸው ናቸው:: ከዚህ በታች ያለው ደግሞ በ14 ዓመት ነግሠዋል በማለት የጻፉት ደራስያን ቁጥር በተመለከተ ልዘርዝር:: 14 ዓመት ነግሠዋል የሚሉት ደራስያን ቁጥር ብዙ አይደሉም:: ነገር ግን የታሪክ ሠነድ መኖሩን ለመግለጽ ነው::

1ኛ 10ኛ ልደት መታሰቢያ ቀ.ኃ.ሥ የተባለው መጽሔት ሐምሌ 16 ቀን 1994 ዓም ገጽ 16" አጤ ቴዎድሮስ ከ1846-1860 ዓም በገባር ይተዳደር የነበረው ወታደር በደመወዝ እንዲተዳደር ቋሚ እንዲሆን በማድረግ የዘመናዊውን ውትድርና ያደረጃጀት ሥርዓት መሠረት ጥለዋል" ሲል ጸሐፊው 14 ዓመት መንገሣቸውን ያሳያል::

2ኛ አምባሳደር አሐዱ ሳቡሬ ኢትዮጵያ ርቪው መጽሔት መስከረም 1984 ዓም ገጽ 32" አጤ ቴዎድሮስ 14 ዓመት" ሲሉ ጽፈዋል::

1ኛ ፊንታዬ ወ/ዘሊባኖስ የአባ ጠቅል አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 25 "ለሰማንያ ዓመታት በኢትዮጵያ ሰፍኖ የነበረው ዘመነ መሳፍንት አገዛዝ በቆራጡ የጦር ዘዴ ስልትና የተፈጥሮ ተሰጥኦ በነበራቸው በቋረኛው መይሳው ካሣ መሪነት የጎጃሙን መስፍን ጉርአምባ ላይ የአማራውን ገዥና የእጤ ዮሐንስን ሣልሳይ እንደራሴ የነበሩትን ትንሹ ራስ አሊን አንድ ጊዜ ድል በማድረግ በ1842 ዓም ወደ ሰሜን ተጉዘው የስሜኑንና የትግሬውን ገዥ ደጃች ውቤን አሸንፈው ከማረኩ በኋላ ደረስጌ ማርያም በአቡነ ሰላማ ተቀብተው ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ተብለው በይፋ ታውጇል" ሲሉ ጽፈዋል::

18 ዓመት ነግሠዋል በማለት አንድ ደራሲ ብቻ ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ወደሰሜን የዘመቱት ደጃዝማች ውቤን ድል አድርገው



የነገሡት በ1842 ዓም ከሆነ 18 ዓመት ነገሡ ማለት ይሆናል:: ነገር ግን በ1842 ዓም አልነገሡም:: በ1842 ዓም የእንግሊዝ ጉዳይ ፈጻሚ አቶ ፕላዲ ደብረታቦር ላይ ከራስ አሊ አሉላ ጋር የተዋዋሉበት ዘመን ነው::

ታሪክ ለሚጽፍ ሰው ስለአንዱ ነገር ሲጽፍ ሲደጋግም እያጠናከረለት እንደሚሄድ ግልጽ ነው:: ያም በመጀመሪያ ስለ አንድ ታሪክ የጻፈውን ራሱ በራሱ ማረም ይችላል:: ምክንያቱም እየቆዬ ሲሄድ ምርምሩ ይነጥራልና ነው:: "በዚህ ወቅት ይህን ብዬ ነበር አሁን ሳጠና ግን ይህ ሁኖ አገኘሁ"ብሎ መጻፍ የተለመደ ሲሆን በኢትዮጵያ ደራስያን ላይ መሳሳቱን እያወቀ ያነኑ አንዴ ያለውን ሲደጋግመው ይገኛል::

ስለዚህ አንዳንዶቹ ራሳቸውን በራሳቸው ማረሙ ይቅርና ሌሎች ሲያርሟቸው እንኳን አይቀበሉም:: ሁሌም እኔ ትክክል ነኝ የሚለው ጠባይ በሥነ መንግሥት በፖለቲካ ዘንድ ብቻ ሳይሆን በሥነ ጽሑፍ በኩል በተሰለፉት ታላላቅ ደራስያንም ሲከሠት ይታያል:: ለምሳሌ ስለ አጤ ቴዎድሮስ የነገሡበትን ቀን አስመልክቶ ክቡር አቶ ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ የጻፉትን እንመልከት::

4 ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ካጤ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ አጤ ኃይለ ሥላሴ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 39 "በተወለዱ በ50 በነገሡ በ14ኛው ዓመት በ1860 ዓም ሚያዝያ 6 ቀን አርፈው በመቅደላ መድኀኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ" ይሉና ገጽ 137-138" በየካቲት 5 ቀን 1847 ዓም ራሳቸው ደጃዝማች ውቤ እነግሣለሁ ብለው ባሠሩት" ይሉና::

ዝቅ ብለው "በይፋ ሲነግሡ 35 ወይም 36 ዓመት ሙሉ ጎልማሳ ናቸው"ይሉና በገጽ 265" አጤ ቴዎድሮስ አባትና እናታቸው ያወጡላቸውን ስም 35 ዓመት ሙሉ ሲጠሩበት የነበረው ካሣ የሚባለውን መጠሪያ ስማቸውን ለውጠው ሲነግሡ የቴዎድሮስን ስያሜ ተቀበሉት" ሲሉ ከዚህ ላይ 35 ዓመት ሲሆናቸው ካሳ የሚለውን ስም ወደ ቴዎድሮስ ሲቀይሩት 15 ዓመት መንገሣቸውን ይጠቁማሉ::

ሌላው የፈረንጆችን አቆጣጠር የያዙ ብዛት ያላቸው ደራስያን ደግሞ "በ1855-1868" ብለው የሚጽፉ ደራስያን እጅግ ብዙ ናቸው:: በብዛት ፈረንጆች ሲሆኑ ኢትዮጵያውያንም ፈረንጅ አይሳሳትም ያሉ ይመስላሉ ቁጥሩን ወደ ኢትዮጵያ ቀመር እንኳን ሳይተረጉሙ እንዳለ የፈረንጆችን ዘዬ በመያዝ (ከ1855-1868)የሚሉትን ደራስያን በተለይም ፈረንጆች የሚበዙ ቢሆኑም ኢትዮጵያውያንም የእነርሱን ድርሰት ከዚህ መጽሐፍ ላይ አልጠቀስኩም:: ብዙ ናቸው ገጽ ማጣበብ ይሆናል በሚል ብዛታቸውን አይቼ እኔ ግን አገር ቤት ኢትዮጵያውያን የጻፉትን በመያዝ መኖራቸውን አምኜ አልፌዋለሁ:: ከዚህ በታች ያሉት አንድ ደራሲ ብቻ የጻፉት ሲሆን እርሳቸውም 12 ዓመት ብቻ ነግሠዋል የሚል እምነት ያላቸው ሊቀ ጠበብት ጌታቸው ኀይሌ ናቸው::

4ኛ ጌታቸው ኃይሌ <u>ኢትዮጵያን ሪጅስተር መጽሔት</u> ጥር 1996 ወይም 1988 ዓም ገጽ 52" ቴዎድሮስ ቀዳማዊ 1848 ዓም "ሲሉ ጽፈዋል:: የሊቀ ጠበብት ጌታቸው ኃይሌን የዓመቱን ብቻ ሳይሆን ሌላም መልስ የሚሰጥበት ስላለ ከታች ራሱን ችሎ ምዕራፍ ተሰጥቶታል:: ስለዚህ እንኳን በሊቀ ጠበብት ጌታቸው ኃይሌ በ1848 ዓም ነገሡ ባሉት አተራረክ ቀርቶ በ1846 ዓም ወይም በ1847 ዓም ነገሡ" የሚሉትን ትረካ ያፈርሰዋል::

ምክንያቱም በስሌት ሊመጣ አይችልምና ነው:: ትክክለኛው ትረካ አጤ ቴዎድሮስ የነገሡት የካቲት 5 ቀን 1845 ዓም ነው:: አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ትናንትም ዛሬም ነገም የተባለውን መጽሐፍ ስጽፍ ከላይ በተዘረዘሩት የኢትዮጵያውያን የታሪክ መጻሕፍት ላይ ጥናት ለማድረግ ሞክሬአለሁ:: በእኔ እምነት በሰነዶቹ መሠረት የካቲት 5 ቀን በ1845 ዓም መንገሣቸውን አምኜ ተቀብያለሁ::



# ክፍል አራት

## ምዕራፍ 1

### የአጤ ቴዎድሮስ ሕግ አዋጅ!

<u>ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ</u> ገጽ 14 "አዋጅ አስነገሩ፤እንዲህ ብለው አራሽ እረስ፤የወንድ መኮንን የሴት ወይዘሮ ባለ ጉልት ባለ ርስት በእየ አባትህ ሰጥቸሃለሁ፤ነጋዴም ነግድ በተቀማህበት ቦታ ደንጊያ ደርድረህ ወደኔ ና:: ተወኝ ሌባ ተወኝ ወምበዴ ግባ እቀማለሁ እሰርቃለሁ ብትል ለአካልህ እዘንለት:: አይዞህ ድኃ አይዞህ ወታደር፤ ደስ ይበልህ በክርስቶስ ኃይል መጥቻለሁ" ሲሉ ማወጃቸውን ጽፈዋል::

አጤ ቴዎድሮስ እንደነገሡ "አባት ያለህ በየአባትህ ግባ፤አባትና ግዛት የሌለህ እኔ አባት እሆንሀለሁ፤ግዛትም እሰጥሃለሁ" በሚለው አዋጃቸው ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት መሠረቱ:: የሰው ልጅ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ በመሆኑ ሊሸጥ አይገባውም አይሸጥም !የኢትዮጵያ ዳር ደንበር ጠረፏ በመንግሥት ወታደር ሊጠበቅ ይገባል!

የሰው ልጅ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ እኩል መሆኑን ቀድመው የተረዱት አጤ ቴዎድሮስ ናቸው:: በአሜሪካ መንግሥት ጥቁር ሕዝብ እንዳይሸጥ ያወጁት ርእስ ብሔር አብርሃም ሊንከን ሲሆኑ እንደጎርጎርዎስ አቆጣጠር ጥር 1 ቀን 1863" ጥቁሮች የአሜሪካ የጦር ኃይሎች ሙሉ አባል ሆነው ከነጮች እኩል ናቸው" ብለው አወጁ"::

አሜሪካ ጥቅምት በ1492 በጎርጎርዮስ አቆጣጠር በክርስቶፎር ኮለምቦስ ተገኝታ የአውሮፓን ሕዝብ አጠራቅማ የምትኖር አገር ስትሆን ከእንግሊዞች ሐምሌ 4 ቀን በ1774 እንደጎርጎርዮስ አቆጣጠር ነጻ ወጥታ ሰብአዊ መብት አልጠበቀችም ነበር:: ርእሰ ብሔር አብርሃም ሊንከን እስኪያውጁ ድረስ ማለት ነው:: አጤ

ቴዎድሮስ በ1845 ዓም ሲነግሡ ወደ ጎርጎርዮስ ቀመር ስንተረጉመው በ1853 ማለት ነው።

የኢትዮጵያ ዳር ደንበር ተከብሮ ብሔራዊ ወታደር ተቋቁሞ የኢትዮጵያ ቁሳቁስ መጤ ነጋዴ ዐረብና ፈረንጅ በነጻ ሳይወስደው በውል ይመሥረት ማለት አገራዊ ፍቅር የተላበሰ ሥልጡን አስተዳደር ነበር። የአገር ልማት እንዲጠነክር በአገር ጠንካራ ማዕከላዊ አስተዳደር ተመሥርቶ ድንቁርና እንዲጠፋ መጣር መልካም ራእይ መሆኑን ማንበብና መረዳት ለሚችል የሰው ልጅ ሁሉ የሚረዳው ይመስለኛል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በመንግሥት ደረጃ ብሔራዊ ክብር ያላት መሆንዋን ማሥመራቸው የኢትዮጵያን ታሪክ ጠንቅቀው በመረዳታቸው ነው። ይቅርታ አድርጉልኝ ዛሬ ዘመናዊ በሆነ ሃይማኖት በእኛ ቄሶች ድክመት ወደ ሌላ ሃይማኖት የተራመዳችሁ ወገኖቼ ብዙ ናችሁ። በትክክል ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤ ክርስቲያን ስሕተት የለባትም። ስህተቱ የበስማም ቄሶች እንጅ የሃይማኖቱ አይደለም። አጤ ቴዎድሮስ ይህ ሃይማኖት ይከበር ብለው በአዋጅ እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነታቸው ደካማ ጎኑን የሚችሉትን ያህል አርመዋል።

ቤተ ክህነቱን እንደእርሳቸው ጠንካራ አጤና እንደ አለቃ አካለወልድ ያለ አስተማሪ ሐዋርያ ኑሮ ቢሆን ዛሬ ፕሮቴስታንት በኢትዮጵያ አይጨፍርባትም ነበር። አጤ ቴዎድሮስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር "አንድ ወንድ ላንድ ሴት" ያለውን ከልብ በማመን የነበሩአቸውን ቁባቶች አስወግደው ግንባር ቀደም" ራሳቸው በሥጋ ወደሙ ተወስነው ሌሎችን በዚህ ተግባር እንዲጠኑ ለማድረግ አዋጅ ማወጃቸው ያስመሰግናቸዋል ዳሩ ግን ጌታችን ካስተማራቸው ሐዋርያት መካከል ይሁዳ በ30 ብር እንደሸጠው ሁሉ የእኛም ቄሶች እነሱ ያላደረጉትን አጤ ቴውድሮስ በማድረጋቸው ጠላት ሆኑአቸው። ከተራ ቁጥር 1-7 ያሉት በዚያን ወቅት ለነበሩት መኳንንቶች የማይዋጥላቸው እንደ መቅሠፍት የሚፈሩአቸው ነበሩ።

"1ኛ ከአሁን በፊት የነበረ ሃይማኖት ክርስቲያን በክርስቲያንነቱ፥ እስላም በእስላምነቱ ጸንቶ እንዲቀመጥ፥ ነገር ግን ክርስቲያን



ከአንድ ሃይማኖት ወጥቶ ሌላ ሃይማኖት ተከትሎ፥እስላሙም ከእስልምና ሃይማኖት ወጥቶ ሌላ አዲስ የእስላም ሃይማኖት ሲያስተምር ቢገኝ አስተማሪውም ተማሪውም አንገቱን በሰይፍ ይቆረጣል፥ደረቱም በጦር ይወጋል።

2ኛ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከአንዲት ሴት በቀር ሌላ አግብቶ ቢገኝ ሀብቱን ሁሉ እንዳለ ለመጀመሪያ ሚስቱ ጥሎ እንዲወጣና ርስትም ሆነ ሹመት እንዳይሰጠው።

3ኛ "ከጥንት የቆየው የቄስና የደብተራ መሬት የመንግሥት ይሆናል። ገበሬው መሬት ተሰጥቶት አርሶ ግብር የሚከፈለው ለመንግሥት እንጂ ለካህናት ለደብተራ አይደለም። "የሚለውን አንዳንድ ሠነድ እንዲህ ሲል መዝግቦታል "ከጥንት የቆየው የቄስና የደብተራ የመሬት ግብር እንደነበር ሆኖ ይቆያል" ይላል። ይችን ቄሶች ያስገቧት ሳትሆን አትቀርም።

4ኛ የቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች በዕለት ተግባራቸውና በደመወዝ እንዲሠሩ እንጅ ባርያ መግዛትና መሸጥ እንዳይፈጽሙ ሲሸጡና ሲገዙ ቢገኙ እንደነፍሰ ገዳይ በአደባባይ እንዲሰቀሉ ወይም በግዞት እንዲኖሩ።

5ኛ ማንም ሰው ሴት ልጁን ለአቅመ አዳም ሳትደርስ ለሹመትና ለሥልጣን ተብላ እንዳትዳር ይሁን። የቤት ሠራተኞች ገረድና አሽከሮች ለሥራ ከመቀጠራቸው በፊት ደመዎዝ እንዲከፈላቸው በውል ማድረግ ይገባቸዋል። ከአሠሪያቸው ጋር ተጣልተው ቢወጡ በውላቸው መሠረት የሠሩበት ገንዘብ ይከፈላቸው።

6ኛ ማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ በየሞያው ተሰማርቶ መተዳደር ይገባዋል። ማንኛውም ሰው በሙያው እንዲሰለፍ ይሁን ሲባል ካህኑ አርሶ ይብላ እንጂ ሞያዬ ቅስና ስለሆነ ሕዝቡ ይቀልበኝ ሊል አይገባውም። ነገር ግን ወታደር በውትድርናው ደመዎዙን መንግሥት ይከፍለዋል። ገበሬም በግብርናው፥ነጋዴም በንግዱ በየሞያው ይደር።

7ኛ ገበሬው ከጥንድ በሬ በላይ የሚያርስና ነጋዴ ከአጋሰስ ጭነት በላይ የሚነግድ ግብር እንዲከፍል፤ነገር ግን በትክሻው ተሸክሞ

የሚነግድና ቆፍሮ የሚዘራ ገበሬ ግብር ለመንግሥት ከፈል መዋጮ አውጣ ተብሎ እንዳይገደድና እንዳይከፍል ይሁን"ሲሉ አወጁ:: ይህ አዋጅ ሲተላለፍ ምድረ መኳንንትና ካህናት ደብተራ ሰነፍ የበስማም ቄስ ይንሽቀሽቅ ጀመር:: ምክንያቱም የሰው ጉልበት እየበዘበዙ የኖሩ በመሆናቸው ይህ አዋጅ ሲታወጅ ጥቅማቸው እንዳይቀር ተሰለፉባቸው::

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 192 "የቤተ መንግሥትም ወገን ሰው ሁሉ በዕለት ተግባሩና በደመወዙ እንዲያድር እንጂ ባሪያ መሸጥ ወይም መሸፈት እንዳይኖር በጠቅላላው በነገሡበት ቀን ከዚህ በፊት እንዳወጁት ገበሬው ወደ እርሻው ነጋዴም ወደ ንግዱ የቀረውም ሰው በየሥራው እንዲመለስ ባዋጅ አስታወቁ" ሲሉ ጽፈዋል::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ ዓላማዎች አጤ ቴዎድሮስ በመያዝ ሲነሡ ችግር ገጠማቸው:: በዘመነ መሳፍንት ሥር የሰደደው ሌብነት እንደ ሞያ ሆኗልና ሌቦች ተሰባስበው ጃንሆይ ሁሉም በየሞያው ሠርቶ ይኑር ካሉ የኛ ሞያ ሌብነት ነውና ይፍቀዱልን አሉ::

አጤ ቴዎድሮስ ይህማ መልካም ነው ለእኔ የግል አሽከር ስለምትሆኑ ተሰባስባችሁ ኑ:: ነገር ግን በሌብነት ያላስመሰከረ ሰው ይዛችሁ እንዳትመጡ ብለው አሰናበቱአቸው:: ሌቦችም መሰሎቻቸውን ሰብስበው መጡና መምጣታቸውን አስነገሩ:: አጤ ቴዎድሮስም ሁሉ ሌቦች መሆናቸውን በያንዳንዱ አንደበት ካዳመጡ በኋላ ክበብና በልልኝ ብለው አስፈጁአቸው::

አጤ ቴዎድሮስ እንደነገሡ "ከዚህ በፊት ሸፍተህ የነበርክ ግባ ላለፈው ጥፋትህ ምሬሃለሁ ነገር ግን ይህ አዋጅ ከታወጀበት ቀን ጀምሮ ባትገባ መድኃኔዓለም አይማረኝ ሳልምርህ" ብለው ማወጃቸው አይዘነጋም:: ሌቦች ይህን የመሰለ አዋጅ መታወጁን እያወቁ እነሱ ለራሳቸው የምትስማማቻቸውን "አባት ያለህ በያባትህ ግባ አባት የሌለህ እኔ አባት እሆንሃለሁ:: ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየሞያው ሠርቶ ይደር" የሚለውን ይዞ በመምጣት ሌቦች ተሳሳቱ::



# ምዕራፍ 2

## "የያዝከውን ሃይማኖት አትቀይር"!

"ከአሁን በፊት የነበረ ሃይማኖት ክርስቲያን በክርስቲያንነቱ፥እስላም በእስላምነቱ ጸንቶ እንዲቀመጥ፥ ነገር ግን ክርስቲያን ከአንድ ሃይማኖት ወጥቶ ሌላ ሃይማኖት ተከትሎ፥ቢገኝ እስላሙም ከእስልምና ሃይማኖት ሌላ አዲስ የእስላም ሃይማኖት ሲያስተምር ቢገኝ አስተማሪውም ተማሪዉም አንገቱን በሰይፍ ይቆረጣል፥ ደረቱም በጦር ይወጋል" ሲሉ አውጀዋል:: ማንኛዉም አማኝ ከያዘው እምነት ውጭ ሌላ እምነት ሲማር ቢገኝ ተማሪዉም አስተማሪዉም ይቀጣል:: "እስላም ሆነ ክርስቲያን፤ አረታዊም ከያዘው ሃይማኖት ሌላ ለመቀየር መሞከር የለበትም ነው::

አጤው አባባላቸው ክርስቲያኑም ሆነ እስላሙ አረታዊው ተከባብሮ የኖረባት አገር ኢትዮጵያ ስለሆነች በሃይማኖት አሳበው የአገሪቱ ጠላቶች ገብተው ሕዝቡን ይለያዩታል ብለውም በማሰብ ነው:: ወይም ደግሞ ተዋሕዶና ነባሩ እስላም አገር አፍቃሪ መንግሥት አክባሪ ሁኖ የኖረውን ሕዝብ ፀረ መንግሥትና ፀረ ሕዝብ ትምህርት ያስተምሩታል ብለውም ይሆናል:: ወይም ደግሞ የውጭ ኃይሎች የራሳቸውን ሃይማኖት ሲያስተምሩ ሕዝቡን ከሕዝብ ብቻ ሳይሆን ከቤተሰቡ ጋር ሊለያዩት ይችላሉ ብለው አስበውም ይሆናል:: አልያም ደግሞ ዘመናዊው አዲስ መጤ ሃይማኖት ለአገር ግንባታ አይጠቅምም ብለው ይሆናል::

<u>The Abyssinian Difficulty</u> በተባለው መጽሐፋቸው page 31 "I can give you an assurance then that neither your people nor those of our people who profess your faith will ever be molested or tormeneted in the countries of which Divine Providence has made me master, for not only Christians,our brothers, but also Muslims and Jews can live in our countries on condition that they be. have in conformity with the laws of the country and obey the wishes of the soverign. But if there are people who want to teach another faith, I will inform you

that we have a bishop and a clergy, and that we cannot renounce the beliefs of our fathers::

የሀበሻ ጣጣ የሚለው መጽሐፍ ቀጥታ ትርጉም "መለኮታዊው ጌታ ንጉሥ ባደረገኝ አገር የእርስዎም ሆኑ የእኔ ሕዝብ እምነትዎን በመከተላቸው አይጉላሉም:: የመንፈስ ሽብር አይደርስባቸውም:: የአገሬን ሕግ ሉዐላዊነት እስካከበሩ ድረስ፤ወንድሞቻችን የሆኑት ክርስቲያኖች፤ብቻ ሳይሆኑ ሙስሊሞችና ይሁዲዎችም ችግር አይደርስባቸውም:: የራሳችን ጳጳስና ካህናት ስላሉን ሌላ እምነት እንዲያስተምሩ አንፈቅድም:: የአባቶቻችንን እምነት አንለውጥም" ማለታቸውን ጽፈዋል::ከስም አጥፊው እስተር ያጣላቸው ይኸው አቋም ነበር::

ሌላው የአጤ ቴዎድሮስ ፍራቻ በእስያ ከእስላም ሃይማኖት ላይ የተነሡት አዲስ እስላሞች ኢትዮጵያን ያሰጋታል ብለውም ይሆናል:: ለምሳሌ የያዝከውን ሃይማኖት እንደያዝክ ጽና ማለት ለአንዳንድ ሰዎች ፀረ እስላም አድርገው ተመልክተውታል:: በኢትዮጵያ እስላሞች በኩል በተለይ ከ1984 ዓም ወዲህ የሚጻፉት መሥመራቸውን ለቀዋል:: በቅርቡ በእስላም ወንድሞቻችን በኩል የሚነሣው ቅስቀሳ ግን በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም::

አባባላቸው እንኳን ሌላውን ምእመን መነኮሳቱን ሳይቀር አስልመናል" እየተባለ የሚነዛው ወሬ ገንዘብ ከዐረብ አገር ለማግኘት ተብሎ እንጂ ሳይማሩ እምነቱን ሳይረዱት ወደ እስልምና ሃይማኖት የሄዱት መነኮሳት ቅድሚያ ላደጉበት ለተማሩበት ሃይማኖት ያልሆኑ ለእስላም ሃይማኖት ሊሆኑ አይችሉም:: አጤ ቴዎድሮስ የጠሉት እምነታቸውን የሚቀያይሩትን ግለሰቦች ነበር:: ዛሬ አጤ ቴዎድሮስ ኑረው ቢሆን እነዚህ ለጥቅም ብለው ከክርስቲያንነት ወደ እስልምና የሄዱትን መነኮሳት ነን ባዮች በአዋጃቸው መሠረት ይቀጡአቸው ነበር:: እነዚህ በገንዘብ ስጦታ ከክርስትና ወደ እስልምና ሃይማኖት የሄዱት ግለሰቦች ታሪክ በፎቶ ተደግፎ ወጥቷል::

ተገኘ ብልሃቱ ፍሬ አልባ በለሶች በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 34-38 ላይ ጠቅሰውታል:: ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ችግር እየሳበ ያለው በሃይማኖት ምክንያት መለያየት በመፈጠሩ ነው:: አሁን ወንድሞቻችን ከዐረብ አገር በሚደረግላቸው ልገሳ ክርስቲያኑን



ሕዝብ ለውጠው ለመጨረስ የሚደረገው ጥረት መጥፎ አዝማሚያ ላይ ደርሷል::

ስለዚህ ግራና ቀኙን እምነቶች ባንድ ለማየት የተነሡት አጤ ቴዎድሮስ ሲሆኑ፤ሌላው በደበልጥ ይህን በሃይማኖት መለያየትን ለማጥበብ ጥረት ያደረጉት (አጤ) ልጅ ኢያሱ ሚካኤል ናቸው:: መፈክራቸውም "ሃይማኖት የግል ነው! አገር የጋራ ነው" የሚለውን የእርሳቸውን ፍልስፍና የመኳንንት ደራስያን ለአጤ ኃይለ ሥላሴ ይሰጡአቸው እንጂ መፈክሩ ግን የልጅ አጤ ኢያሱ ነበር::

እግዚአብሔር ለምን ዝም አለን? በተባለው መጣጥፉ በተለያዩ ክፍለ ሀገራት በእስላም ወንድሞቻችን የተሠዉትን ምእመናን በሥዕል አስደግፈው አቅርበዋል:: ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተደረገ ያለው ተግባር አስከፊ መሆኑንና እቅዳቸውን አስመልክቶ እኒሁ ጸሐፊ ገጽ 12-20 ጽፈዋል:: ዛሬ ያለው መንግሥት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስብ አይደለም:: ሕዝቦቹ በሃይማኖት ምክንያት ይህን የመሰለ የግድያ ተግባር ሲፈጸምባቸው እንኳን ሊደርስላቸው ቀርቶ በዜና ማሰራጫ ሊዘግብ አላሻውም::

የወያኔ መንግሥት አሸባሪ ያዙኩ ያላቸው ግለሰቦች በሥነ መንግሥት ፖለቲካ የተጠረጠሩትን እንጂ በሃይማኖት ምክንያት ሕዝብን ከሕዝብ የሚያፋጁትን ሊጠይቅ አይፈልግም:: በፌደራል ፖሊስ ፀረ-ሽብር ግብረ ኃይል ተዘጋጅቶ የቀረበ የካቲት 1999 ዓም የተባለውን ሠነድ በጥሞና ተመለከትኩት:: ከላይ ከዲያቆን ናትናኤል ታምራት ጥናት ጋር የተገናኜ እንደሆነ ብዬ ሳመሳክር አይገናኙም:: ዲያቆኑ ጥቃት ያደረሱበትንና እቅድ መውጣት የጀመረበትን አስመልክቶ ከ1994 ዓም እስከ በ1999 ዓም መሆኑን ጽፈዋል::

የፌደራል ፖሊስ ፀረ-ሽብር ግብረ ኃይል የካቲት 1999 ሰነድ ፀረ-ኢትዮጵያ የሽብር መረብ ሲበጣጠስ በተሰኘ መጣጥፍ ላይ ሁለቱ የሚገናኙበት መሥመር የለም:: የፖሊስ መረጃ የሚጀምረው ሕዳር 1998 ዓም-1999 ባለው የተፈጸመውን የካቲት 1999 ዓም ሲገልጽ ሁሉንም "የሻዕቢያ ገፋፊነት የኦነግ ተባባሪነትና የአርበኞች ግንባር አጨብጫቢነት መሆኑን እንጂ በቤተ ክርስቲያንና በምዕመናኑ ላይ የተፈጸመውን ድርጊት ለወያኔ ምንም ስላልሆነ ሳይጠቅሰው ቀርቷል::

ለዚህም ነው አንዳንድ ግለሰቦች "ክርስቲያኑ ሕዝብና እስላሙ ሕዝብ እንዲተሳለቅ ወያኔ በራሱ የሚያደርገው ሴራ ነው" የሚሉት ሊመስል የሚችለው በሕዝቡ ላይ የሚደርሰው በደል ስለማይሰማው ነው:: ወደ ምዕራፉ መነሻ ልመለስና ዛሬም ነገም ከነገ ወዲያም ቢሆን ለኢትዮጵያውያን የሚበጀን የየራሳችን እምነት አክብረን መያዝ እንጂ ጊዜ አገኘን ብለው ለመጉዳት መነሣት መልካም አይሆንም:: ሕዝብ በሕዝብነቱ መከበር ሲገባው እምነቱም በዚሁ መልክ መከበር ይኖርበታል:: ሰብአዊ መብት ነውና::

<u>እግዚአብሔር ለምን ዝም አለን</u>? በተባለው መጣጥፉ ገጽ 15 "የጥንቶቹ ሸማግሌ እስላሞች በሁኔታው ተደናግጠው ከዚህ ውጭ ነን በማለት ጥቆማ አካሂደው የጦር ማሠልጠኛቸውን ጠቁመዋል" ሲሉ ጽፈዋል:: የጎንደር የእስልምና ሃይማኖት አባቶቻችን መጨረሻው እንዳይበላሽ ያደረጉት ለሰላም ብለው ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሥልጣን የናፈቃቸው ግለሰቦች የሚያነሡት ብጥብጥ ካልሆነ በቀር በሃይማኖት የተጣላበት ጊዜ የለም:: በዚህ አብሮ በመኖሩ በዓለም ዘንድ ያተረፈው ዝና ቀላል አይደለምና:: መንግሥትና የቤተ ክርስቲያኑ መሪዎች ሆኑ የቤተ መስጊዱ መሪዎች እጅ እና ጓንት ሁነው ሕዝቡን ከሕዝብ እያደባደቡ ለመኖር የተስማሙ መሆናቸው ምልክቱ በክርስቲያኖች ዘንድ በደረሰው ጥቃት ቤተ ክህነቱ አፌን በጭማና በውስኪ ብሎ ዝም ብሎአል::

ስለዚህ የግራ ቀኙ ምእመናን ከዚህ በፊት አብረን እንደነበርነው ዛሬም ነገም አብረን እንድንኖር የአጤ ቴዎድሮስ አዋጅ ለሁላችን ጠቃሚ መመሪያ መሆኑን ማስተማር ይገባናል:: ከዚህ በፊት ሱዳን አገር በስደት ስንኖር በአንድ ቤት የምንቀመጠው በሃይማኖት ተቀራርበን ሳይሆን በጸባይ ተግባብተን ነበር:: ከእኔ ጋር አብረን እንኖር የነበረው አቶ ጋሻው ሙሳ፤የተባሉ ባልንጀራዬ በሃይማኖት እስላም ናቸው:: ዛሬም ካሊፎርንያ ይኖራሉ:: ኢትዮጵያ ዘመድ ለመጠየቅ ሂደው የታዘቡትን አጫወቱኝ::

<u>አቶ ጋሻው ሙሳ</u> "እኔ በጎንደር ክፍለ ሀገር ሳድግ ከክርስቲያን ባልንጀሮቼ ጋር አብረን ስንበላ ስንጠጣ ስንጫወት እንጂ መለያየትን ሳላይ ያደኩኝ ነኝ:: በስደት አገርም ከአንተና ከሌሎች ክርስቲያኖች



ጋር በአንድ ቤት የነበርን መሆናችን አንተው ምስክር ነህ:: በዚህ በቅርቡ አገር ቤት ደርሼ መጥቻለሁ:: ያየሁትን ብነግርህ ትደነግጣለህ:: ደብረ ታቦር ባልንጀሮቼ መስጊድ እንሀድ አሉኝና አብረን ሄድን:: ከስግደት በኋላ ሊሰብኩ የተነሡት በእድሜያቸው አዛውንት ናቸው:: ወደ 70 ዓመት ይሆናቸዋል:: ታዲያ ሲያስተምሩ ከነዚህ ከረከሱት ጋር አብራችሁ አትህዱ አትቅረቧቸው!እያሉ ሌላም ሌላ መነገር የማይገባው ቃላት መናገር እንደጀመሩ ትቻቸው ወጣሁ" ሲሉ አጫውተውኛል::

የአጤ ቴዎድሮስን አዋጅ በጥሞና ለመረመረው ሃይማኖትን መቀያየር አገርን መካድ ብቻ ሳይሆን ወላጅ እናትና አባትንም መካድ መሆኑንና በተለይ በዛሬው አቋም የማንነት መሠረት መሆኑን ይገልጻል:: ብልጭልጭ ነገር አላፊ ነው:: ብልጭልጭ የሆነ ነገር ለማንም አይጠቅምም:: ደግሞም በሃይማኖት በኩል አንዱ አንዱን ማስገደድ ፈጽሞ አይገባም:: ለዚህም ነው አጤ ቴዎድሮስ የያዝከውን ሃይማኖት አጥብቅ ያሉት:: ሃይማኖት ብልጭልጭ ፋሽን አይደለም:: ስላላይደለም ነው አትለውጥ ያሉት:: ሌላውን ነገርማ እንግዲያ ለመቀየር ያደረጉት ጥረት ቀላል አይደለም::

በትምህርትና በወታደራዊ፤ዘርፍ አውራ ጎዳና ለማሠራት ሌላውንም ጥበብ አክባሪ ሲሆኑ የነበረውን ደካማ ምግባር ሲነቅፉ ሃይማኖትን ግን አጥብቅ እንጂ አትቀይር አሉ:: ከዚህ ላይ አንድ ነገር ብዬ ይህን ምዕራፍ ልዝጋው:: ማለት የፈለኩት አጤ ቴዎድሮስ የሃይማኖትን ሕፃ ሲያውጁ ቅድሚያ እርሳቸው በተዋሕዶ ሃይማኖት ቃል ኪዳን ገብተው በሥጋ ወደሙ ተወስነው ነው::

አባ ዻብረ ሥላሴ ጥበቡ <u>ድብቁ መለኮታዊ ጥበቃ በኢትዮጵያ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 129 "በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከነገሡ በኋላ በሕጋዊ የኦርቶዶክስ ሥነ ሥርዓት በሥርዓተ ተክሊል ጋብቻቸውን የፈጸሙ ንጉሥ አጤ ቴዎድሮስ ናቸው:: የአጤ ቴዎድሮስ አቋም ከእርሳቸው ጀምሮ በኢትዮጵያ የሚኖር ክርስቲያን በሙሉ አንድ ሴት ለአንድ ወንድ በሚል ክርስቲያናዊ መርሆ ተነሥተው ቅጥ ያጣውን የመሳፍንትና የመኳንንት አምስት ስድስት ቅምጥ ልምድ በጽኑ ተቃወሙት" ሲሉ ጽፈዋል::

ይህን በክርስቲያኖች ላይ ሲያውጁ እስላሞችን ግን እምነታቸው የሚያዝ መሆኑን በመረዳት አንድ ወንድ ለአንድ ሴት አላሉአቸውም:: እርሳቸው የፈለጉት ክርስቲያኑና እስላሙ የአንድ አገር ልጆች በመሆናችን ኅብረት ይኑረን አንድ አመለካከት ይኑረን በማለት ነው::

## ምዕራፍ 3

### የአጤ ቴዎድሮስ ዘመቻ ወደ ወሎ!

አጤ ቴዎድሮስ ያልገበሩትን ክፍለ ሀገራት ለማስገበር ከጎንደር ወደ ደብረ ታቦር ወታደራቸውን እንዲያቀና አደረጉ:: እርሳቸው ብዙ ሳይቆዩ ሠራዊቱን ተከታትለው ደብረታቦር ደረሱበት:: ወሎ በዘመነ መሳፍንቱ ወቅት አንቱ የተባሉ መሳፍንቶች ነበሩበት ከሌሎች ክፍለ ሀገር ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር እስከ 1876 ዓም ኃይላቸው የገነነ የሴት መሳፍንት ነበሩበት::

ወይዘሮ ወርቂትና ወይዘሮ መስታይትን እንደ ምሳሌ ልንጠቅስ እንችላለን:: እነዚህ የሴት መሳፍንቶች ብዙ ዘመን ከገዙ በኋላ ሴትነታቸው ታወቃቸውና በአካባቢው ያለውን ፋቅራ ሰብስበው "ዱዓ ግቡልን" አሉአቸው::

አንቱ የተባሉ ፋቅሮች ተሰበሰቡ ዱዓውን ከመጀመራቸው በፊት "አላህን የምንለምንበትን እንወቀው ይነገረን" አሉ:: የሴት መሳፍንቶችም "እኛ ሴቶች ሁነን ብዙ ተግባራት አከናውነናል:: የበለጠ እንድናከናውን በጸሎታችሁ ሴትነታችንን ወደ ወንድ ቀይሩልን" ሲሉአቸው ምድረ ፋቅራ ሁላ ጭንቀት ገባቸው:: ከመካከል አንዱ ቀልጠፍ ብሎ "እመቤቶች ይህማ ብዙ መቶ ኩንታል ጫትና ማጣፈጫ ያስፈልገዋል" አሉ ይባላል:: ስለነዚህ የሴት ጀግና መሳፍንቶች ክቡር አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ እንዲህ ይላሉ::

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 158 "ከጨጭሆ እስከ ሸዋ ድንበር የሚገዙት ወይዘሮ ወርቂት የሚባሉ ባላባት አሉ፤እርሳቸውም የይማም ዐመዴ ዐሊ እናት



ናቸው:: እኒህም ሴት ወደፊት እንግሊዞች በሚመጡበት ዘመን ብዙ ጊዜ በየምክንያቱ ከወይዘሮ መስታውት ጋር ስማቸው ተነሥቶ ይገኛል::ምሥራቅ ወሎ የወርቂት ሲሆን ምዕራቡን ወሎና የመቅደላን አካባቢ የሚገዙት ወይዘሮ መስታዋት የሚባሉ የአባ ዋጠው (ራስ ኃይለ ማርያም) እናት ናቸው:: ሁለቱም ከላይ የይማም (የደጃዝማች) ሊበን ልጆች ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

በዘመነ መሳፍንቱ የታወቁ የሴት መሪዎች የነበሩበት ክፍለ ሀገር ዋናው ወሎ ነበር:: አጤ ቴዎድሮስ ገና ጨጭሆ ሲደርሱ የወሎ ጦር ገጠማቸው:: እርሳቸውም ይህን የገጠማቸውን ጦር በኃይል እየገፈተሩ ወደ መቅደላ ተራራ ሲጠጉ ጥይት ብቻ ሳይሆን እርሳቸውን የባሳቸው ከተራራው የሚወርደው ናዳ ከባድ ሆነባቸው:: ይህን ከላይ እየተወረወረ የሚመጣውን መርግ ድንጋይ ጦርነት ተቋቁመው መቅደላ አምባውን በድል አድራጊነት ለመያዝ ችለዋል:: ይህን አምባ ከያዙ በኋላ ደጃዝማች ሊበንን በአምባው ላይ ሹመው እርሳቸው ጉዞአቸውን ወደ ወሎ አደረጉ::

<u>አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አምበሳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 106 "የመቅደላን አምባ ሰብረው ያዙት" ይሉና "ወዲያውም ደጃች ሊበንን ሹመው ከመቅደላ ወደ ወሎ ተመለሱ" ሲሉ ጽፈዋል:: ከላይ እንደጠቀስኩት ወሎ በያንዳንዱ አውራጃ የየራሱ ታላላቅ መሳፍንት የነበሩበት ሲሆን አንዱን መስፍ ድል ሲያደርጉ ሌላው መስን ይጠብቃቼዋል:: ወሎ እጅግ ብዙ መሣፍንቶች የነበሩበት ሲሆን የአጤ ቴዎድሮስን ጦር ለመግጠም ቀደም ብሎ ዝግጅቱን ፈጽሞ ነበር:: ወሎዎች ብቻቸውን ሳይሆን ውል የተዋዋሉት ከሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለኮት ጋርም ነበር::

"አጤ ቴዎድሮስ በጎጃም አድርገው ወደ ሸዋ የሄዱ እንደሆነ ወይዘሮ ወርቂት ወደ ሸዋ ሀደው አጤ ቴዎድሮስን ሊወጉ፤አጤ ቴዎድሮስ ወሎ የሄዱ እንደሆነ ንጉሥ ኃይለ መለኮት ጦራቸውን ይዘው ወሎ እንደሚዘምቱ" ተዋውለዋል:: በዚህ ወቅት አጤ ቴዎድሮስ ወደ ወሎ ዘመቻ ሲሄዱ ንጉሥ ኃይለ መለኮት በውላቸው መሠረት ወሎ ገስግሰዋል:: ነገር ግን በውላቸው መሠረት ንጉሥ ኃይለ መለኮት አጤ ቴዎድሮስን ለመዋጋት አልቀረቡም:: ብዙም ሳይቆዩ ከወሎ ወደ ሸዋ ተመልሰዋል:: ይህን የሸዋውን ጦር አመላለስ አስመልክቶ አቶ ጳውሎስ ኞኞ እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል::

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 80 "የቴዎድሮስን መጠጋት የሰሙት ኃይለ መለኮትና የኦሮሞቹ ባላባቶች ባንድነት ተሰብስበው ይህን ሰው አንችለውምና እንበታተን ብለው መከሩ:: በዚህ ምክር ተስማምተው ኃይለ መለኮት ወደ ሸዋ ተመለሱ:: ሲመለሱም በክረምቱ ምክንያት ብዙ ከብትና ሰው አለቀባቸው" ሲሉ ጽፈዋል:: በነገራችን ላይ አጤ ቴዎድሮስ ከጎንደር ወደ ወሎ ሲገሰግሱ ቅድሚያ የሰላም አዋጅ ማወጅ ብቻ ሳይሆን በግል ለመሳፍንቶች ሽማግሌ ተልከባቸው አንቀበልም ያሉ ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

<u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 159 "እነዚህም ባላባቶች እንዲገቡ አስቀድመው ተጠይቀው እምቢታቸውን አስታውቀዋል" ሲሉ ጽፈዋል:: በሽምግልና የማይገቡ ሲሆኑ አጤ ቴዎድሮስ የመጡበት ጉዳይ ነውና ወሎን ገጠሙት:: በዚህ ወቅት የወሎ መሳፍንቶች ኃይላቸውን አጠንክረው ከቦታቸው ሳይደርሱ ለማስመለስ ጥረት አደረጉ::

አጤ ቴዎድሮስ እየተከተሉ የወሎ መሳፍንቶች እየመሩ አይገቡ ገብተው ሁሉንም ድል ሲያደርጉ ከሞት የተረፉት መኳንንቶች ወደ አውሳ በረኃ ገቡ:: በዚህ ወቅት በግራቀኙ አያሌ ሕዝብ ያለቀ ሲሆን በተለይ በወሎ መሳፍንት በኩል ድል ከመሆናቸው የተነሣ ብዙ ሕዝብ በአጤ ቴዎድሮስ ተገድሏል:: ምክንያቱም አጤ ቴዎድሮስ ከላይ እንደተጠቀሰው አስቀድመው "የምሕረት አዋጅ እያወጁ እጃቸውን እንዲሰጡ አስነግረው አልሰማ ባሉት ላይ ከፍተኛ ቅጣት አውርደውባቸዋል::

የተማረከው ብዙው ሰው ሁለት እጁን ተቆርጦ በአንገቱ ተሸክሞ ወደ ቤቱ መሄድ ሲጀምር ተራ ይጠብቅ ከነበሩት መካከል አንዱ እጁን ከመቆረጤ በፊት ለአጤ ቴዎድሮስ ጥያቄ አለኝ፡ አለ:: እርሳቸውም "አቅርቡት ይናገር" አሉ:: በዚህ ሰዓት ተማራኪው ሰው "ጃንሆይ ጥፋቱ የኛ መሆኑን እናውቃለን:: ነገር ግን ንጉሥና እግዚአብሔር መሐሪ ነው:: ይማሩን ዋናው ደግሞ ሁለት እጃችን አይቆረጥብን:: ባይሆን አንዱን ይተውልን::



ጃንሆይ ምግቡንስ ፋጡማ ታጉርሰኝ የጨነቀኝ ነገር ቢኖር እንዴት አድርጌ እሬቤን ልጠርገው ነው" ብሎ ሲናገር አጤ ቴዎድሮስ "ምናለ ቀድማችሁ ይህን ሰው አቅርባችሁት ቢሆን ኑሮ ከዛሬ ጀምሮ ሁለት እጅ አይቆረጥ" ብለው ሌሎች ተራ ይጠብቁ የነበሩት ሁሉም ተማሩ:: በዚህ ተናጋሪ ሰው ምክንያት እንኳን ሁለት እጃቸውን አንድ እጃቸውንም ሳይነኩ ሙሉ ምሕረት ተደርጎላቸው ወደ ቤታቸው ገብተዋል::

ይህ ሁሉ ሕዝብ ሲማረክና ሲገደል እጃቸውን ያልሰጡት አሊ አደራ እና ሰዲቅ ደንቃ የተባሉ የአጤ ቴዎድሮስን ጦር በአዲስ ጉልበታቸው ገብተው ያጣድፉት ጀመር:: አሊ አደራ የተባሉት ሰው የአጤ ቴዎድሮስን ተዋጊ እንደመብረቅ ከመሀል እየገቡ ጣሉባቸው:: በዚህ ጦርነት ከፍተኛ የሆነ ድልን አሊ አደራ ሊቀዳጁ ሲሉ አጤ ቴወድሮስ ወታደራቸው ማለቁን አይተው ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ በሆነው ጦርነት መካከል በፈረስ ላይ ሁነው ከመሀል ገብተው ሽሽት ጀምሮ የነበረውን ጦራቸውን አበረታተው እጅግ ጥቂት በሆነ ጦር መክተው በመያዛቸው ከሽንፈት ወደ ድል ቀየሩት::

አሊ አደራ ድል አድርገው የነበሩት ጀግና በአጋጣሚ እርሳቸው ባሉበት በኩል አጤ ቴዎድሮስ እየገፉ በመምጣታቸው በሰላም እጃቸውን ሰጡና ድል የአጤ ቴዎድሮስ ሆነ:: አጤ ቴዎድሮስ ቀደም ሲል ሱዳን ላይ ቱርክን በተዋጉበት ቀን ነበር ይህን ዓይነት ሽንፈት ደርሶባቸው የነበረ እንጂ ይህ በአሊ አደራ የገጠማቸው ጦርነት ለመጀመሪያ ጊዜያቸው መሆኑ ነው::

"በቴዎድሮስ የለም ጋሻ
ማረሲ ይሻላል በማረሻ
ማረስ ይሻላል መገበር
እጅ እግሩን ይዞ ለመኖር
አላርስም ያሉ አልነግድ
ተመለመሉ እንደግንድ"

ተብሎም ተገጥሟል:: አጤ ቴዎድሮስ አሊ አደራ በሰላም ከገቡላቸው በኋላ የደከመውን ወታደራቸውን አበረታተውና አጠናክረው ሰዲቅ ዳንቃ የተባሉትን ለማስገበር ቆርቆራ ወደ ተባለው ምሽግ ገሰገሱ:: በዚህ ጦርነት ላይ የአሊ አደራ ወታደሮች

ከሞት የተረፉት አብረዋቸው ዘምተዋል:: ሰዲቅ ዳንቃ የተባሉት ግን መገበር ቀርቶ ለሽምግልና የተላኩትን ሰዎች ቁጭ ብለው ለማነጋገር የማይፈልጉ መሆናቸው ለአጤ ቴዎድሮስ ተነገራቸው::

አጤ ቴዎድሮስና ሰዲቅ ዳንቃ ውጊያውን ገጠሙ፤ ታዲያ ይህ የሰዲቅ ዳንቃ ጦር የአጤ ቴዎድሮስን ወታደር ያነጥፍባቸው ጀመር:: ከላይ ከአሊ አደራ ጋር ካደረጉት ጦርነት በላይ ሰዲቅ ዳንቃ አጤ ቴዎድሮስን ገጠማቸው::

በዚህ ጦርነት ከፍተኛ የሆነ ሽንፈት ገጠማቸው:: ቢሆንም ግን ራሳቸውን እንደገና አጠናክረው መልሶ ማጥቃት ማድረግ ጀመሩና ሰዲቅ ዳንቃ ጉድባቸውን ነቅለው አውሳ ገቡላቸው:: ከዚያም አጤ ቴዎድሮስ ከሞላ ጎደል ዋና ዋና የተባሉትን መሳፍንቶች አስገብረውና አንገብርም ያሉትን በረሃ አስለቅቀው በቦታቸው ሌላ ሹም ሹመው እርሳቸው ጉዞአቸውን ወደ ሸዋ አደረጉ::

አጤ ቴዎድሮስ ብዙ ወታደር የሞተባቸው ቢሆንም በኃይል ሸዋን ለማስገበር ጉዞአቸውን ጀመሩ:: ከወሎ ወደ ሸዋ መንገድ ሲጀምሩ ወታደራቸው ፈርቶ ነበር:: ምክንያቱም የሸዋ መሳፍንት ኃይል ከሌሎች ሁሉ ከፍ ያለ ኃይል ያለው ይሆናል ተብሎ ተፈርቶ ነበር:: ወታደሩ ይፍራ እንጂ አጤ ቴዎድሮስ ግን ሁሌም ድል አደርጋለሁ ብለው ስለሚያስቡ ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ጉዞ ጀመሩ::

## ምዕራፍ 4

## የአጤ ቴዎድሮስ ዘመቻ ከወሎ ወደ ሸዋ!

መንግሥቴ ደስታ አምባሳደር ግርማዊት እቴጌ ጣይቱ ብጡል ብርሃን ዘኢትዮጵያ 1832-1910 በተባለው መጽሐፍ ገጽ 17 "ቴዎድሮስም ኃይለ መለኮትን ለማስገበር ወደሸዋ ዘመቱ:: በሕመም በድንጋጤም ሊሆን ይችላል ኃይለ መለኮት ወዲያውኑ ሲሞቱ የ12 ዓመቱን የኃይለ መለኮትን ልጅ ምኒልክን አስረው ወደ ቤተመንግሥታቸው ተመለሱ" ሲሉ ጽፈዋል::



አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ የተወለዱ ለኢትዮጵያ የተሠዉ ንጉሠ ነገሥት ናቸው በተባለው መጣጥፍ ገጽ 3 "ወደ ወሎ ዘምተው ወሎን ድል አድርገው ወደ ሸዋ መጓዛቸውን ለንጉሥ ኃይለ መለኮት ሲነገራቸው በድንጋጤ ታመው ተጉለት ላይ ዐረፉ" ሲሉ ጽፈዋል::

መይሳው ካሣ መጣብህ ቢሉት
ምድረ መሳፍንት ገባበት ቁርጠት::
ሱሪህ አረንጓዴ ጎራዴህ ባለወርቅ
አምሮብኻል ካሣ አንተ ብቻ ታጠቅ
በያይነቱ ነበር የሸዋ ፈረስ
አንድ ጥርኝ ሆነ ቢዘልቅ ቴዎድሮስ
ከቋራ እስከ ወሎ እስከ ሸዋ ድረስ
በወንድ ወንድ አለበት ኧረ ተው ተመለስ
ሰባቱ ደጃዝማች ስምንተኛው ካሣ
ምርት አደረጋቸው ወቅቷቸው ተነሣ"

ተብሎም ተገጥሟል:: ይህ ግጥም ብቻም ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን መምህራን ሁላ ግጥም ገጥመው አጤ ቴዎድሮስን አመስግነዋል::
መይሳው ዳዊት ሶበ አስምአ ምጽአተ
ኃይለ መለኮት ናባል በኃበ ሀለወ ሞተ

የቅኔው ትርጉሙ
"ቴዎድሮስ ዳዊት መጣብህ ሲሉት ኃይለ
መለኮት ናባል ባለበት ድርቅ አለ"::

ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ የንጉሥ ኃይለ መለኮትን አሟሟትና የአጤ ቴዎድሮስን የሸዋን ጦርነት አስመልክቶ በአጭር ዘግተውታል:: "በዚህ መሣሪያና በዚህ ስንቅ ባመቱ ሸዋን ከፈተበት:: የሸዋውን ንጉሥ ልጅ ምኒልክን ይዞ ሄደ" ብለዋል:: የሚገርመው ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የጻፉት ነው::

ብላቴ ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ዋዜማ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 51 "አጤ ቴዎድሮስን የመሰለ ጨካኝ ንጉሥ ሁለተኛ እንዳያነግሥባት ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ ትማጸናለች" ብለው ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስን "አንተ"እያሉ ሲጽፉ አጤ ዮሐንስንና አጤ ምኒልክን አንቱ ይላሉ:: በነገራችን ላይ

አጤ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ እንደሚዘምቱ ታምረ ማርያም የተባለው መጽሐፍ አዲሱ በ1988 ዓም እትም የጸሎት መጽሐፍ ላይ ተጽፎ ይገኛል::

ተስፋ ገብረ ሥላሴ ተአምረ ማርያም በተባለው መጽሐፍ "ሣህለ ማርያም (ምኒልክ)ከተወለደ አሥራ አንድ ዓመት በሆነው ጊዜ የሸዋው ንጉሥ አባቱ ኃይለ መለኮት ሞተና ደብረ በግዕ ተቀበረ:: በዚህም ጊዜ አስቀድሞ እንደተነገረው በጎንደር ቋራ ከምትባል ቦታ ኃይለኛና ቁጡ የሆነ ካሣ (ቴዎድሮስ) የሚባል ተነሣና ነገሠ::

በዚያም ከጎንደር ወደ ሸዋ ሄደና እመቤታችን አስቀድሞ ለሣህለ ሥላሴ እንደ ነገረችው ሣህለ ማርያምን (ምኒልክ) ወደ ጎንደር ወስዶ በእስር አስቀመጠው" ሲሉ ጽፈዋል:: ንጉሥ ኃይለ መለኮት በብሽቀት አልያም ደግሞ በብስጭት ወይም ደግሞ በድንጋጤ መሞታቸው ዛሬ ጥላቻን ማስከተሉ አልቀረም:: በድንጋጤ መሞት በእርሳቸው አልተጀመረም ሌሎች የኢትዮጵያ ነገሥታት ብዙዎች በዚህ አይነት አጣዳፊ ጭንቀት አልቀዋል::

እንኳን ጦር መጣ ተብሎ ቀርቶ ለብዙ ዓመታት የሚወዱትን ቤተሰብ የናፈቀ ሰው በድንገት ሲያየው የሚታመምና የሚሞት ብዙ ነው:: በአክሱም ዘመነ መንግሥት አጤ ዋክና 222 ዓም ላይ የነገሡት በ2 ቀናቸው ጭንቀት ገድሏቸዋል:: በ772 ዓም ላይ የነግሡት አጤ አይዞር 2 ሰዓት ብቻ ነግሠው ጭንቀት ገድሏቸዋል:: ንጉሥ ኃይለ መለኮት አሟሟታቸው በብስጭት ሊሆን ይችላል:: የአጤ ቴዎድሮስን ማንነት ከሌሎች መሳፍንት ውድቀት ተምረዋልና:: የአጤ ቴዎድሮስን ክንድ የቀመሱት ራስ አሊ አሉላ፤ ከእግዚአብሔር የተላከ ነው በማለት መናገራቸው ተዘግቧል::

ደብተራ ዘነብ የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ሊትማን እንዳሳተመው ገጽ 17 "በሐምሌ ንጉሥ ቴዎድሮስ ወደ ጎራ ወጥተው ተመልሰው ቆቃ ሠፈሩ:: ከቆላው ስለክረምቱ ያነግዜም የሸዋው ገዥ ኃይለ መለኮት ወርቂትን እራስ አሊን ለመርዳት መጡ:: ንጉሥ ቴዎድሮስም የኃይለ መለኮትን መምጣት (በሰውም ጊዜ )" ምናልባት (በሰሙ) ጊዜ ለማለት ፈልገው እንደሆነ ቅንፍ የኔነው:: "አያታ ወጥተው አዋ ሜዳ ላይ ሰፈሩ:: እራስ አሊም ኃይለ መለኮት አሮሞዎች አንድነት ሁነው መከሩ:: እንዲህ ብለው እርስዎ ከአገርዎ ሸዋ ይመለሱ ይህንን



ሰው አንችለውም አሉ:: ኃይለ መለኮትም ተመለሱ:: ብዙ ሰው ውሀ ወሰደባቸው ከወሎ ጀምሮ እስከ ሸዋ ዳርቻ እየታመመ ያለቀው ፈረስ ቁጥር የለውም::"

"ኃይለ መለኮት ብርቱ እመም ታመሙ" ይሉና ገጽ 19 "ንጉሥ ቴዎድሮስ ወደ ደብረ ብርሃን በሄዱ ጊዜ ኃይለ መለኮት የሸዋው ጌታ ደብረ ብርሃንን የአንኮበርንም ቤታቸውን አቃጥለው ሸሹ ታመው ነበር" ይሉና ሲያክሉ ገጽ 20 "በሬሳ ወንዝ 4ት መድፍ 300 የሚሆኑ ነፍጥ ኃይለ መለኮት ከባሕር ጥለውት ተገኘ:: ዋኝቶ ላወጣ ሁሉ ፈረስ ሰጡት" ሲሉ ጽፈዋል:: እንደ ደብተራ ዘነብ አተራረክ ንጉሥ ኃይለ መለኮት ብዙ ቀን የታመሙ አይመስሉም::

"ወሎ ሂደው ከራስ አሊ ጋር ያደረጉት ውይይት ራስ አሊ "ከአገርዎ ሸዋ ይመለሱ ይህን ሰው አንችለውም" የሚለውን የራስ አሊን ምክር ሰምተው ወደ ግዛታቸው ተመልሰው ቤታቸውን ማቃጠልና የጦር መሣሪያውን ባሕር መጣል የመሰለውን ለሚመለከት በሽታው የሰነበተባቸው አይመስሉም:: በድንጋጤ ያረፉትም ደረሱ ሲባል ነው::

አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አምበሳ የተባለው መጽሐፍ ገጽ 106 "አጤ ቴዎድሮስ በዚሁ ዓመት ጥቅምት 10 ቀን ከሸዋውና ከወሎው ድንበር ግሼ አደሩ:: ጥዋት ላይ የግሼው መኮንን ሀብተ ማርያም ተያዙ፤ ከዚያም ተጉዘው መንዝ ምድር ፍርኩታ በደረሱ ጊዜ የኤፍራታው መኮንን አቶ በድሉ ለንጉሠ ነገሥቱ ገቡላቸው:: ወይዘሮ ዘመኑ ወርቅም የሸዋው ንጉሥ የሣህለ ሥላሴ እናት ገቡላቸው:: እንዲሁም በመንዝ ላይ ሳሉ የሸዋ ሰው ለመተያያ ያመጣውን በግ ወታደር ስለቀማው ለንጉሥ ጮኸ:: የቀሙትም አሥራ ሦስት ወታደሮች ተይዘው እጅ እጃቸውን ተቆረጡ:: ጉዙአቸውን በመቀጠል ጉሮ ሥላሴ በደረሱ ጊዜ እነ አቶ ሀብቱ እህላቸውን ቤታቸውንም አቃጠሉ፤ ጥቂትም ተዋጉ::"

"በዚህም ግጭት ከንጉሥ ወገን ከደጃዝማች ገለታ በኩል ጥቂቶች ወታደሮች ሲሞቱ ከሼዎች ወገን እነአቶ ሀብተ ማርያምና ጥቂትም ሰዎች ሞቱ:: አጤ ቴዎድሮስ ጉር ሥላሴ የተደረገውን ግጭት ከተመለከቱና የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ሹማምንት አመካከት

ከአመዛዘኑ በኋላ ያላንዳች ሥጋት ንጉሥ ኃይለ መለኮትን ለማደን ወደ ደብረ ብርሃን ገሠገሡ::"

"ንጉሥ ኃይለ መለኮትም በሕመም ላይ ከመሆናቸውም ይልቅ የአጤ ቴዎድሮስ አመጣጥ የማጥቃት ደወሉን ለድፍን ሸዋ ስለሚያሰማ በአካባቢያቸው አብሮአቸው የሚመክት ጽኑ ሠራዊት ስለአስፈለጋቸው ይህ እስኪሆን ድረስ በደብረ ብርሃንና በአንኮበር፣ የነበረውን ቤተ መንግሥታቸውን አቃጥለው ሸሹ"::

"አጤ ቴዎድሮስ ንጉሥ ኃይለ መለኮትን በመከታተል ቡሎ ወርቄ ከገበያው በደረሱ ጊዜ የሚጠብቀኝ ጦር ይኖራል በማለት ስለተጠራጠሩ ሰልፋቸውን አጠንክረው ቢመለከቱ የሚከራከራቸው ባላንጣ በማጣታቸው ፈረሳቸውን እንደልቡ እንዲጋልብ ፈቀዱለት:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከንጉሥ ኃይለ መለኮት ሠራዊት መካከል አቶ በዛብህ በአንድ በኩል ዘልቆ ገጥሞ ጥቂት ሰዎች ገድሎና አቁስሎ አመለጠ:: ቢሆንም አጤ ቴዎድሮስ ንጉሥ ኃይለ መለኮትን ከማሳደድ የሚያግዳቸው አልተገኘም ነበር::"

"አጤ ቴዎድሮስ ንጉሥ ኃይለ መለኮትን ለማደን ከላይ ከታች በሚሉበት ወራት (ጋላ)ኦሮሞ አገሩን የሚጠብቅ ጦር አልተደረገለትም በማለት አማራውን አገር ለመውረር ከቶ መምጣቱን በመስማታቸው ሰልፋቸውን አዙረው አንድ (ጋላ) ኦሮሞ እንዳያመልጥህ ብለው እግረኛውንና ፈረሰኛውን ለቀቁበት:: በዚህም ውጊያ ከደብረ ብርሃን እስከ አንጎለላ የነበረውን (ጋላ) ኦሮሞ አንድም ሳያመልጥ አስደበደቡት:: የሰውም ሬሳ እንደቅጠል ተነጠፈ"::

"አጤ ቴዎድሮስ የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ዕረፍት በመስማታቸው ጓዙን ቁንዲ አምባ አድርገው ወደ ደብረ በግዕ ገሠገሡ:: ወዲያውም የፍትሐት ጸሎት አልቆ የወሪደ መቃብሩ ሥነ ሥርዓት በሚፈጸምበት ሰዓት ደረሱ:: የሆነ ሁኖ የኀዘን ተካፋይነታቸውን በሁኔታቸው አሳይተዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ወደ ደብረ በግዕ በወረዱ ጊዜ ጓዛቸውን ቁንዲ ከንጉሥ ወሰን ሰገድ ከተማ ትተው ሄደው ነበርና ተመልሰው መጥተው ጠምቄ በሠፈሩ ጊዜ ነፍጠኛ ገባላቸው:: የንጉሥ ኃይለ መለኮት ሹማምንቶች በበኩላቸው አቤቶ ምኒልክን ይዘው ወደምንጃር ሸሹ::"



"አጤ ቴዎድሮስ ከቁንዲ ተነሥተው መገዘዝ በደረሱ ጊዜ ራስ እንግዳን ቢትወደድ ብሩን፣ቢትወደድ ውቤን ወደ በረከት አዘመቱአቸው:: ወዲያውም በረከት እንደደረሱ ሕዳር 30 ቀን ከምኒልክ ጋር ጦርነት ገጥመው ኃይለኛ ውጊያ ከሆን በኋላ ምኒልክ ድል ሆነው ሸሹ:: በጦርነቱም መካከል ከምኒልክ ወገን አቶ ሸሽጉና ጥቂት ሰዎች ጭምር ሲሞቱ አቶ በዛብህና አቶ አንዳርጋቸው ተማረኩ:: እነራስ እንግዳ በኩራ አራት የመቶ አለቆችና እንዲሁም ብዙ ወታደር ሞተ:: የበረከት ጦርነት እንደተደረገ የንጉሥ ኃይለ መለኮት ሹማምንት የኃይላቸውን ሚዛን ከአወዳደሩ በኋላ መክረው ምኒልክን ይዘው ለንጉሠ ነገሥቱ ገብተው ተገዥነታቸውን አረጋገጡ" ሲሉ ጽፈዋል::

ክቡር አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ <u>አጤ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 168 "የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ሞት ለማረጋገጥ በነአቶ በድሉ መሪነት ከአታክልት በቶራ መስክና በጠለላ በኩል ቁልቁል ወርደው ደብረ በግዕ ደረሱና መቃብሩን አስቆፍረው የኃይለ መለኮትን ሬሳ አዩ" ሲሉ ጽፈዋል:: በነገራችን ላይ ከሁሉም ደራስያን በፊት በእድሜም በወቅቱ የነበሩት ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ግን ይህን ብለው አልጻፉም::

<u>ታሪክ ዘመን ዳግማዊ ምኒልክ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 46 "ንጉሥ ኃይለ መለኮት በነገሡ በ8 ዓመት በጥቅምት 30 ቀን ዐርብ ሌሊት ዐረፉ፤ በነጋው ቅዳሜ የጎዳር መባቻ ደብረ በግዕ ተቀበሩ" ሲሉ ጽፈዋል:: በትክክል አጤ ቴዎድሮስ የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ሬሳ አስቆፍረው አይተው ቢሆን ኑሮ ለምን የመጀመሪያው በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ጥላቻ የነበራቸው ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ፤ አልጻፉትም ነበር? ይህ በውነቱ ለወደፊቱ መታረም ያለበት መሆኑን ሳስገነዝብ እወዳለሁ:: የክቡር አቶ ተክለ ጻድቅን አባባል አንድም የሚደግፍ የታሪክ ሰነድ ሳላገኝ ቀርቻለሁ::

አለቃ ዘነበ <u>የቴዎድሮስ ታሪክ ሊትማን</u> ያሳተመው ገጽ 18 "ኃይለ መለኮት ሙተው በተቀበሩ ጊዜ ንጉሥ ቴዎድሮስ ደረሱ:: ሞትዎን በሰሙ ጊዜ እጅግ አዘኑ" ሲሉ ጽፈዋል::

አለቃ ተክለ ኢየሱስ የኢትዮጵያ ታሪክ ሐተታ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ110 "አጤ ቴዎድሮስ ይገጥመኛል ብሎ ሠራዊቱን አሰልፎ ሲጠብቅ ተመሃል የኃይለ መለኮት ሞት ወሬ መጣለት:: አጤ ቴዎድሮስም የኃይለ መለኮትን ሞት አላምን ብሎ እንደተሰለፈ ግፍኑን ሄደ:: ቶራ ከሚባል ሥፍራ በደረሰ ጊዜ የሚቀበርበትን ጠይቆ በሰላይ ጥቂት ሰው ሆኖ ደብረ በግዕ ወረደ:: ሠራዊቱን ከደጋው ላይ አስፍሮ ተወው:: ኃይለ መለኮትም መቃብር ሲወርድ ባየ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ አዘነ" ሲሉ ነው የጻፉት::

አስፋው አሊ ይመር ቁስለኛዋ አገር በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 166 "ንጉሥ ኃይለ መለኮት ወዳለበት እስከሬን በደብረ በግዕ ሕንፃ ሞዓ ደብር በ1848 ዓም በክብር ካስቀበረ በኋላ የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ልጅ አቤቶ ምኒልክን ከእናቱ ከወይዘሮ እጅጋየሁ ለማና ከአያቱ ከወይዘሮ በዛብሽ ጋር ወደጎንደር ይዟቸው ሄደ" ሲሉ ጽፈዋል:: አስፋው አሊ ይመር ሁሉንም "አንተ" ብለው የጻፉ ናቸው::

አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 107 "አጤ ቴዎድሮስ የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ዕረፍት በመስማታቸው ኀዘኑን ቁንዲ አምባ አድርገው ወደ ደብረ በግዕ ገሠገሡ:: ወዲያውም ጸሎተ ፍትሐቱ አልቆ የወረደ መቃብሩ ሥነ ሥርዓት በሚፈጸምበት ሰዓት ደረሱ:: የሆነ ሁኖ የኀዘን ተካፋይነታቸውን በሁኔታቸው አሳይተዋል" ሲሉ ጽፈዋል::

አቶ ጳውሎስ ኞኞ ሆኑ ሌሎች የታሪክ ጸሐፊዎች "አጤ ቴዎድሮስ የንጉሥ ኃይለ መለኮትን ሬሳ ከተቀበረ አስወጥተው አዩ" ብሎ የጻፈ የለም:: ለወደፊቱ ይህ ዓይነት አተራረክ ቢቀንስ መልካም ይመስለኛል:: ወደ ነበርኩበት ልመለስና አጤ ቴዎድሮስ አቤቶ ምኒልክን ተከታትለው ጦርነት መግጠማቸው አይዘነጋም::

አቤቶ ምኒልክን ስል እርሳቸው ጠሩን መሩ ለማለት ሳይሆን የአባታቸው መኳንንቶች ናቸው የሚዋጉት:: የእነሱ ኃይል ደክሞ የአጤ ቴዎድሮስ ኃይል አይሎ በማየታቸው እጃቸውን ሰጥተው ገቡ:: በዚህ ወቅት ሸዋን አስተዳድር ብለው አቶ በዛብህን ሹመው ሕዝቡን አረጋግተው ወደ ጎንደር መንገድ ጀመሩ::



# ምዕራፍ 5

## የአጤ ቴዎድሮስ ራእይ ለኢትዮጵያ

አጤ ቴዎድሮስ በልጅነታቸው ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ሲያድጉ ታላቋን ኢትዮጵያ በታሪክ ስማቸው ያልታወቀው መነኩሴ አስተምረዋቸዋል:: ከትልቅ ወንድማቸው ከደጃዝማች ክንፉ ኃይሉ ጋር ሁነው በእርሳቸው ላይ ምን እንዳደረጉ ከላይ የተጠቀሰ ሲሆን ጎጃም ከደጃዝማች ጎሹ ቤት አሽከር በነበሩበት ወቅት ሌላው ዜጋ ቀርቶ በጥቅም አባትና ልጁ ማለት ደጃዝማች ጎሹና ልጃቸው ደጃዝማች ብሩ ሲዋጉ ወጣቱ ካሣ ከደጃዝማች ጎሹ ጋር ሁነው የዘመቱ ናቸው::

ከዚህ መልስም ወደ ሱዳን እየዘለቁ ከቱርኮች ጋር በተዋጉ ጊዜ ዝናቸው ጎንደርና ደብረታቦር ደርሶ ለጋብቻ ታጭተው ጎንደር መጥተው ሳለ ከእቴጌ መነን የደረሰባቸውን ውርደት ተመልክተዋል ይህ የዘመነ መሳፍንቱን መጥፎ ተግባር ከሸንኮፉ ሙልጭ አድርገው ጥለው አዲስ ተስፋ አዲስ ሕልም ለኢትዮጵያ ይዘው ተነሡ::

ዶ/ር ላጵሶ ጌ ድሌቦ የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ በተባለው መጽሐፍቸው ገጽ 261 "የኢትዮጵያን በሐውርታዊ ኅብረተሰብ በአንድ ማዕከላዊ የአጤ መንግሥት ሥርዓት ለማደራጀት ከሁሉ በፊት
1ኛ ብሔራዊ የፖለቲካ ማዕከል አመራር፤
2 ብሔራዊ የጦር ድርጅት፤
3 ብቃት ያለው ብሔራዊ የኢኮኖሚ መሠረትና መሣሪያ ሦስት በአንድነት የተያያዙ ቅድመ ሁኔታዎች ነበሩ:: የተጠቀሱት ቅድመ ሁኔታዎች እንደተጠበቀ ሁነው የኢትዮጵያ ከባድ የአገር ግንምባታ ፖለቲካና ተግባር በ1850ቹ በአጤ ቴዎድሮስ አመለካከት ለዘመናዊ የኢትዮጵያ አገር ግንምባታ"

"1 የአካባቢ ሥርዓቶችና የጦር አበጋዞች በማዕከላዊ የመንግሥት ቁጥጥር ሥር፤
2 በንጉሥ የሚመራ አዲስ ብሔራዊ የጦር ድርጅት፤

3 የአጤው መንግሥት የሥልጣን ምዕክልና፤
4 የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠረፎች ከውጭ ኃይሎች ተጽዕኖ ነጻ መሆን፤
5 የባሕር ንግድ መፍጠር፤
6 ከአውሮፓ መንግሥታት ጋር ሉዓላዊ ግንኙነት መፍጠር፤
7 በአገር ዘመናዊ የመገናኛ የንግድ የትምህርት የሳይንስ የቴክኖሎጅና የኢንዱስትሪ ሥራዎች ዕድገትና መስፋፋት በመጀመሪያ የሚጠቀሱ መሠረታዊ የፖሊሲና የተግባር እርምጃዎች ናቸው" ሲሉ ዓላማቸውን ዘርዘር አድርገው ጽፈዋል።

ዶ/ር ላጲሶ ጌ ዴሌቦ ታህሳስ 26 ቀን 2003 ዓም በስልክ አጤ ቴዎድሮስን አስመልክቶ ጠይቄአቸው ነበር። የእኔ ጥያቄ ከላይ ከተነበበው የተለየ ሊነግሩኝ የሚፈልጉት ታሪክ ካለ ይንገሩኝ በማለት ስጠይቃቸው ከዚህ በታች የተጻፈውን መልሰውልኛል "አጤ ቴዎድሮስ በዘመናቸው የፈጸሙት ተግባር ሊደነቅ ይገባዋል። የጎንደርን ሕዝብ አስተባብረው ከውጭ ተጽዕኖ ነጻ የሆነ አሠራር እንዲለመድ በር የከፈቱ ናቸው።"

"ባይበዛም አጤ ተክለ ጊዮርጊስ ይህን የወሎን ሕዝብ አስተባብረው የአጼ ቴዎድሮስን ዓላማ ተከትለዋል። አጤ ዮሐንስ የትግራይን ሕዝብ አስተባብረው የኢትዮጵያ አንድነት ከውጭ ነጻ የሆነ ፖሊሲ ተከትለዋል አጤ ምኒልክ የሸዋን ሕዝብና የደቡብ ኢትዮጵያን ሕዝብ አሮሞውንና ሀዲያውን፤ከምባታውንና አደሬውን፤ ቆቱውንና ጉራጌውን...ሌላውን ሕዝብ አስተባብረው የኢትዮጵያ አንድነት ከውጭ ነፃ የሆነ ፖሊሲያቸውን አጠናክረው በመነሣት የአጤ ቴዎድሮስን ዓላማ ተከትለዋል። ትሰማኛለህ ልናገር?" አሉኝ። እኔም እየሰማሁ ነው ዶክተር ይንገሩኝ ከኮምፒውተሩ ላይ እየጻፍኩት ስለሆነ እስክጠይቅ ድረስ ይንገሩኝ" አልኳቸውና እርሣቸው "ጎሽ አኬ" አሉኝና መናገር ጀመሩ።

"አጤ ቴዎድሮስ የጀመሩት ኢትዮጵያን የማሳደግ ዓላማ በአጤ ምኒልክ ባለቤት በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን በተወለደችው እቴጌ ጣይቱ ብጡል አዲስ አበባ ለኢትዮጵያ ማዕከል ሁና እንድትመሠረት አደረጉ። ዛሬ የኢትዮጵያውያን ማዕከል ብቻ ሳትሆን ለአፍሪካውያን ሁሉ ማዕከል መሆንዋን እናንተ በውጭ አገር ያላችሁ እንደአንተ ያለ ታሪክ ለመጻፍ የተነሣውን ትውልድ አፍርታለች። አጤ ቴዎድሮስ የተጋፈጡት ኢምፔርያሊዝምን ነው።



እንግሊዞች ለዜጎቻቸው ብለው ሳይሆን ጦር ወደ ኢትዮጵያ ያዘመቱት አጤ ቴዎድሮስ በወታደራዊ ፖሊሲ አነዳደፋቸው ለወደፊቱ በማስፈራታቸው ነው።"

"ቴዎድሮስ ፀረ ኢምፔርያሊዝምን የተዋጉ ኢትዮጵያውያን ሪፓብሊክ እንድትሆን የጣሩ ጀግና ናቸው። የተማሪው ማኅበር ሆነ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጣረው የእርሳቸውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ብሎ ነው። ዛሬ አጤ ቴዎድሮስ የሉም። ነገር ግን ለኢትዮጵያ አንድነት የተገበሩት ተግባር ሕያው ሁኖ የሚኖር በመሆኑ አልሞቱም አሉ። አጤ ኃይለ ሥላሴ ከላይ ጀምሮ የተዘረዘሩት ነገሥታት የገነቡትን የኢትዮጵያን አንድነት መመሥረትና የውጭ ፖሊሲ ተቀብለው ዛሬ ከደረሰችበት ደረጃ ኢትዮጵያን አድርሰዋል። ለዚህ ነው አጤ ቴዎድሮስ አልሞቱም የምልህ ትሰማኛለህ ልናገር" አሉኝ። ካርዱ አለቀ መልሼ ልደውል አልኩኝና ደወልኩኝ አሁንም በደስታ ያስተምሩኝ ጀመር።

"ኢትዮጵያ የሰው ልጅ የተገኘባት አገር መሆንዋ በታሪክ ብቻ ሳይሆን በአርኪሎጅስት ምርምር የተገኘ ውጤት ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ቀደም ሲል በዳማታውያን ሥርዎ መንግሥት ጀምሮ ያደግን የሃይማኖት መፍለቂያዎች ነን። ይህን አንድነታችን አጠንክረን ሪፓብሊካችንን መጠበቅ ይገባናል። በዘመነ መሳፍንት የጠፋው ጥፋት እንዳይመጣብን ጥረት ማድረግ አለብን። ከላይ እንዳልኩህ አጤ ቴዎድሮስን በወቅቱ የነበሩ አጤዎች ለሥልጣን ሲሉ ወግተዋቸዋል። ነገር ግን እርሳቸው የተነሡበትን ዓላማ ከግቡ አድርሰዋል። ይህን ያደረጉት በጠላትነት ሳይሆን ለሥልጣን ሲሉ መሆኑን መገንዘብ አለብን"።

እያሉ በመናገር ላይ ሳሉ አልሰማኝ ማለት ጀመሩ። እኔ ስናገር ለእርሳቸው የማይሰማ መሆኑን በመገንዘባቸው "አልሰማኝ አለ እስኪ ልጄን ልጥራት" አሉና መጥራት ጀመሩ። ነገር ግን ልጃቸውም እርሳቸው ችግሩ ከእርሳቸው መስሏቸው ነው እንጂ ሌላ የስልክ ችግር አልመሰላቸውም ነበር። ነገር ግን ችግሩ ስልኩ በሌሎች የተጠለፈ ሳይሆን አይቀርም። አንዳንዴ ድምጽ ጨርሶ እልም ይልና መልሶ ደግሞ ንፋስ ይለቅበታል። ይህን የመሰለ ጨዋታ ጀምረን ሳንጨርሰው ዘጋን።

# ምዕራፍ 6

## የአጤ ቴዎድሮስ የውጭ ግንኙነት

አጤ ቴዎድሮስ ወሎንና ሸዋን አስገብረው ወደ ጎንደር እንደተመለሱ የውጭ ግንኙነት አልያም ደግሞ በዘመኑ ቋንቋ "የውጭ ፖሊሲ"ንደፉ:: ይህ በእርሳቸው የተነደፈው የውጭ ግንኙነት ለአንድ አገር ክብር መሆኑን ቀደም ሲል የማኅበረ ሥላሴ ገዳም መነኩሴ የኢትዮጵያን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የዓለምን ታሪክና ሕግ አስተምረዋቸዋል::

ያም ቅድሚያ ዳር ደንበር መከበርና ከውጭ መንግሥታት ጋር አቻ ላቻ መግባባቱን የድርድር አልያም ደግሞ በዘመኑ ቋንቋ "ዲፕሎማሲ"ሥርዓት በኢትዮጵያ የተበላሸ መሆኑን ጥሩ አድርገው አስተምረዋቸዋል::

በተለይም ቤል ዮሐንስና ፕላውዴን የተባሉት እንግሊዛውያን ከላይ ከተጠቀሱት መነኩሴ በተጨማሪ የዓለምን ሕግ አስጠንተዋቸዋል:: በተለይም ጉዳይ ፈጻሚ ፕላውዴን ለአጤ ቴዎድሮስ እንደ አንድ ወታደር ከመዝመት በላይ አሽከርና የቅርብ አማካሪ ነበሩ:: እነዚህ ሁለቱ እንግሊዛውያን ለአጤ ቴዎድሮስ ትልቅ አማካሪ ከመሆናቸው በላይ ለአጤ ቴዎድሮስ ታላቅ ሰዎች ነበሩ:: አሚሚታቸውን አስመልክቶ በወቅቱ አብረው የነበሩት ደራሲ እንዲህ ይገልጹታል::

<u>ስማቸው ያልታወቀው</u> ደራሲ ገጽ 22 "ባሻ ብላውደን ወታደሮቻቸውን ይዘው በጎንደር መንገድ ሲጓዙ ዋሉና በነገታው ጎንደር ሊገቡ ቸኩለው ነበርና ከበቅሎ ወርደው በፈረስ ተቀመጡና ጋሻ ጃግሬያቸው በበቅሎ ሁኖ እርሳቸው ፈረሱን ቀስ ብየ እሄዳለሁ እየመሰላቸው ይጓዙ ጀመር:: ጎንደር በቶሎ ስለ መግባት ያስባሉ እንጂ የሚቆያቸውን ነገር አላሰቡም ነበር::"

"ሰዎቻቸውም ደክመው እንደርሳለን እያሉ ቢከተሉ የማይደርሱ ሆኑ ባሻ ብላውዴንም ቀሀ ከጎንደር አጠገብ ከዝያ መልካም ወንዝ



ከፈረሴ ወርጄ ሰዎቼ ሲመጡ በአጀብ ጎንደር እገባለሁ እያሉ እየጋለቡ ሲሄዱ ሳሉ ቀሀ ከወንዙ ሊጠጉ ጥቂት ስትቀራቸው የጋረድ ሰዎች በቀኝና በግራ ፈሰሱባቸው::"

"አባ ነፍሶ ብለው ፈክረው ወደ ጋሻ ጃግሬ ጠበንጃ ሊቀበሉ ዘወር ሲሉ የጋረድ ሰዎች በሩምታ ተኰሱባቸው:: ጋሻ ጃግሬውም በበቅሎ እየጋለበ ፍኒጥ ፍኒጥ ቢል ሳይደርስባቸው ቀረ የሕልም ሩጫና በቅሎ መጋለብ አንድ ነው ካሰብኸው አያደርስም እና:: ባሻ ፕላደውን አንድ ሰው ሳይገድሉ ያንጊዜው ወደቁና በስከወዲያ ሞቱ:: ሰዎቻቸውም ተማረኩ ጠበንጃቸው ሳይተኮስ ከጋሻ ጃግሬው እጅ የጋረድ ወታደሮች ወሰዱት" ሲሉ ጽፈዋል::

ስማቸው ያልታወቀው ደራሲ ከላይ የተነበበውን ሲጽፉ ሌሎች ደግሞ ቆስለው ሳይሞቱ ስለነበር አጤ ቴዎድሮስ አንድ ሺህ ብር ከፍለው አስለቅቀዋቸው ነበር:: ነገር ግን ቁስሉ በርትቶባቸው ስለነበር ጎንደር ገብተው ሞቱ ይላሉ:: የማዕረግ ስማቸውን ደግሞ "ባሻ" ይሏቸዋል:: ሌላም ሌላ ብዙ ውስብስብና አስቸጋሪ የሆነ ታሪክ ተጽፎ ይገኛል:: ያም ሆነ ይህ የቤል ዮሐንስን አሚሚትና የጉዳይ ፈጻሚ ፕላውዴንን ደም ምለሳ አስመልክቶ ከላይ

ስማቸው የተገለጸው ደራሲ ገጽ 24 "ክንፉ ጋረድ አጤ ቴዎድሮስን ገድየ እሞታለሁ ብሎ ማኸል ለማኸል በፈረስ ጨሬውን እየሰበቀ አንድ ጀግና ፈረሰኛ አስከትሎ ንጉሥ ወደ አሉበቱ ደረሰ እንደ እብድ በፊቱ ያለ ሁሉ እየሸሸ ንጉሥ ጦር ሲወረውር ሲቃጣ ሊቀ መኳስ ዮሐንስ የማነን ጌታ ብለው ጋረድን ደረቱን በጠበንጃ ሰነጠቁት እና ወደቀ::

ያ የጋረድ ጀግና ደግሞ የማነን ጌታ አለና በፈረስ መጥቶ ሊቀ መኳስ ዮሐንስን በጦር ካይናቸው ወግቶ ገደላቸው:: አጤ ቴዎድሮስ ደግሞ ያ ሊቀ መኳስ ዮሐንስን የወጋ ጀግና የማንን ሎሌ ገድለህ ልትሄድ ብለው በጠበንጃ ገደሉት" ሲሉ ጽፈዋል::

ከጋረድ ጋር የተገኘው ሁሉም መቀጣቱን አስመልክቶ አጤ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ መንግሥት የጻፉት ደብዳቤ ዋቢ ነው "የገንዛ ወገኖቼን አንድም ሳይቀር ፈጀኋቸው" ሲሉ ጽፈዋል:: አጤ ቴዎድሮስ ይህን ያደረጉት የውጭ ግንኙነታቸውን ለማጠንከርና

በአገራቸው ያለውን ጸጥታ ለማስከበር አቻ ለአቻ ወዳጅነት በመፈለጋቸው ነው።

ዶ/ር ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ <u>የምዕራባውያን ሥልጣኔና ኢትዮጵያውያን</u> በአሜሪካ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ትንተና በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 93 "የአጤ ቴዎድሮስ ፍልስፍና በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ ቦታ ያለው ነው። አጤ ቴዎድሮስ የሥልጣኔ መሠረቱንና ውሉን ለመያዝ እንጂ ሙሉ በሙሉ በውጭ ኃይል ሥር መውደቅ እንዳይደለ በተግባር አሳይተዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ከውጭ መንግሥታት ጋር ግንኙነት ሲያደርጉ የነበሩት ለአገር ግንባታ እንጂ የዛሬዎቹ ባለሥልጣኖች እንደሚያደርጉት የአገርን ክብር ለማስደፈር አልነበረም።

ሜ/ጄኔራል ነጋ ተገኝ <u>የኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመናት ትግልና የዘመናዊ ሠራዊት</u> አመሠራረት 1855-1974 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 14 "አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ለማሠልጠንና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማስተባበርና አንድ ለማድረግ የተጣደፉት ዋናው ምክንያት።"

"በአንድ በኩል በመዘኑ ኢንዱስትሪ የሠለጠኑ አውሮፓውያን እስያንና አፍሪቃን በቅኝ ገዥነት በመቀራመት ላይ ስለነበሩና እንዲሁም ቱርኮች (ኦቶማን ኤምፓየር) ሰሜን አፍሪካን በተለይ የዓባይ ወንዝ ድርጎኛ የሆነችው ግብፅንና ሱዳንን በቁጥጥራቸው ሥር ካደረጉ በኋላ በቀይ ባሕር በተለይ በኢትዮጵያ ድንበሮች ብቅ ጥልቅ ይሉ በነበረበት ወቅት ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

የውጭ ግንኙነት ዓላማ ለአንድ አገር አቻ ላቻ የጥቅም ወዳጅነት የሚመሠረት ሲሆን የባሕርና የየብስ ንግድን ሌላም ዳር ደንበርን ማስጠበቅ ይጨምራል። ዳር ደንበር ለማስጠበቅ የአገር ውስጥ ፀጥታን ለማስጠበቅ አቅም ያለው አገር ራሱ የጦር መሣሪያ ያመርታል። አቅም የሌለው መንግሥት ደግሞ በገንዘቡ የሚገዛው ማንነቱን ለማስከበር አስቦ ነው።



ናደው ከበደ <u>ሙዳይ መጽሔት</u> ጥቅምት-ሕዳር 1986 ዓም ገጽ 20 "ከምዕራባውያን ጥበብን በመቅሰም አቅደው የተነሡ የመጀመሪያው ንጉሥ ዳግማዊ ቴዎድሮስ መሆናቸውን በተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት ተጠቅሷል። እርግጥ ቴዎድሮስ የፈለጉት እደጥበብ በጦር መሣሪያ ጥይት ላይ ያተኮረ መሆኑ አይዘነጋም። ይህም ፍላጎታቸው ራሱን የቻለ ምክንያት ነበረው። ቴዎድሮስ የውስጥ ተቃዋሚዎቻቸውን ለማንበርከክና የውጭ መሪዎችን ለመቋቋም መሣሪያ ያስፈልጋቸው እንደነበር አያጠራጥርም።"

"እኒያ ከጊዜያቸው ቀድመው አገራቸውና ሕዝባቸው ሳይዘጋጁ አንዷት ኢትዮጵያን ለመመሥረት የጦር መሣሪያ እደጥበብን በዘዴ ሳይሆን በኃይል ወደአገራቸው ለማስገባት የሞከሩት ቴዎድሮስ የራሳቸው እቅድ መሰናክል ሁኖ ጥሏቸዋል።"

"የቴዎድሮስ ዓላማ በውጭ ወረራና በአገር ውስጥ የወገን ጠላቶቻቸው ደባ ከተጨናገፈ በኋላ አገራችንን ከሥልጣኔ ጎዳና ያስተዋወቋት ዳግማዊ ምኒልክ መሆናቸው አሌ ሊባል የማይችል ሀቅ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

የውጭ ግንኙነት ለአንድ አገር መንግሥት ዋና ቁልፍ ነው። የምጣኔ ሀብት እርዳታ ሆነ የምክር አገልግሎት የጦር መሣሪያ እርዳታ ሌላም ሌላ ግንኙነት የሚደረገው ቅድሚያ ራሱን አደራጅቶ አንቱ መባል አለበት። በሀገሩ ውስጥ ፀጥታ ማስከበርና አውደልዳይ ወመኔን ማጥፋት ትውልዱን በአዲስ ሥርዓት ኮትኩቶ አንጾ ማሳደግ ከሌላው አገር ጋር የሚያገናኝ ቋንቋ ማስተማርና ሌላም ሌላ ጉዳይ ይመለከታል።

አጤ ቴዎድሮስ ከእርሳቸው በፊት የነበሩት ነገሥታት ያልፈጸሙትን እርሳቸው ብዙ ተግባራት ጀምረው ነበር። ከውጭ አገር ጋር የሚያስተረጉሙ ሦስት ቋንቋ የሚናገሩ ለምሳሌ 1ኛ ዐረብኛ፤2ኛ እንግሊዘኛ፤3ኛ ፈረንሳይኛ የሚያስተረጉሙ ባለሞያዎች ነበሩአቸው አጤ ቴዎድሮስ ብዙ ተግባር አከናውነዋል።

# ምዕራፍ 7

## ወታደር ደመወዝተኛ ሆነ!

የኢትዮጵያ ሕግ አስከባሪ አልያም ዘበኛ ወይም ደግሞ ወታደር እንበለው ደመወዝ መከፈል የተጀመረው በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ሳይሆን ቀደም ብሎ ይከፈል ነበር። ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ሰባታህ ለወታደሮቹ ደመወዝ ይከፍሉ ነበር። ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት አጤ ሰባታህ የነገሡት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ2800 ዓመተ ዓለም እንደሆነ ይገመታል።

ዳግማዊ ንጉሠ ነገሥት ሰባታህ የነገሡበት በ2545 ዓመተ ዓለም ነው። ነገር ግን የሰላም አስጠባቂ አልያም ደግሞ የሕዝብ ዘበኞች ደመወዝ መከፈል የጀመሩት ቀዳማዊው እንጂ ዳግማዊው ሰባታህ አይደሉም። ለዚህ ብዙ የታሪክ ሠነድ ዋቢ መጥቀስ ይቻላል። ይህን በሁለቱ ሰባታህ በኩል ያለውን ክርክር እንለፈውና የሕግ አስከባሪ ወታደር ደመወዝ መክለፍ የጀመሩት ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት አጤ ሰባታህ ናቸው።

አእምሮ ንጉሤ <u>ጥንታዊ የኢትዮጵያ የሰላም ጥበቃ ታሪክ ከቅራት ዘመናዊ ፖሊስ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 7 "ንጉሠ ነገሥት ሰባታህ ሐሳቡን ከተቀበለ በኋላ በዚህ ወርና ቀን ወደ ማታ እኔ ኤባል ስመ መንግሥቴ ሰባታህ እጅግ ገናናነቴንና ለሕዝብ አሳቢነቴን ዓለም እንዲያውቀው የማስተዳድረው የኢትዮጵያ ኩሽ ሕዝብ ንብረቱ እንዳይባክን ሲሠራ ውሎ ሌሊት ለጥበቃ እንዳይዞር ሕጉን የሚያስከብርለትና ንብረቱ እንዳይባክን ሆነ የቀን ውሎ ሌሊት ለጥበቃ እንዳይዞር ሕጉን የሚያስከብሩለትና የሌሊቱንም ሆነ የቀኑን ኮረኮሬ ወንበዴ የሚይዝለት የሚያስከብርለትና የሌሊቱንም ጠባቂ የሚስማማ ሠራዊት አቋቋምኩ፤ ስሙም መሪ ፈረሰኛ አገር ጠባቂ እንዲባል አዝዣለሁ።"

"ሕዝብ ሆይ! ከእንግዲህ ወዲህ ፈረሰኛ አገር ጠባቂ ሠራዊት በቀር ገበሬው ሕዝብ ማረስና ለመንግሥት የሚገባውን ከምርቱ ከአሥር



አንድ በቀር ሌላ የሚፈልግበት የለም። አሶራውያንና ፍልስጤሞች ፓለስታይኖች የሚያደርጉትን የድንበር ማለፍ የሚቋቋመው ይኸው መሪ ፈረሰኛ አገር ጠባቂ ሠራዊት ነው። የሕዝቡን ፀጥታና መብት የሚያስከብረውም ይኸው ሠራዊት ነው። እንዳለፈው ጊዜ ለሰላም ጥበቃም ሆነ ለጦርነት አይወጣም" የሚል አዋጅ አወጣ" ሲሉ።

ከዚህ ወዲህ ደግሞ በዛጉዌ ነገሥታት ዘመን ለሕግ አስከባሪ ወታደር ደመወዝ መከፈል ተጀምሮ እንደነበር አንዳንድ የታሪክ መጻሕፍት ዘግበዋል። ከመሐል ላይ ደግሞ ቀርቶ ነበር። በጎንደር ዘመነ መንግሥት በተለይ በአጤ በካፋ ዘመን ይህ የሕግ አስከባሪ አልያም ደግሞ የከተማ ጸጥታ ጠባቂ ወይም ደግሞ የከተማ ዘበኛ ሠራዊት የተመሠረተ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በትክክል ደመወዝተኛ ሁኖ እንደነበር ታሪክ የዘገበው ሲሆን የኢትዮጵያ ድቀት የመጣው በዘመነ መሳፍንቱ ሲሆን ይህን ብልሹ አስተዳደር ደምስሰው የኢትዮጵያን አንድነት መሠረት ከጣሉ በኋላ አጤ ቴዎድሮስ ለወታደር ደመወዝ መክፈል ጀምረው ነበር። ከዚህ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው መጽሐፍ በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ለወታደሩ የሚከፈለውን ደመወዝ መዝግቦታል።

<u>የኢትዮጵያ ጥበቃ ታሪክ ከቅራት ዘመናዊ ፖሊስ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 138 "በውሳኔው መሠረት ለቢትወደዶች ለራሶችና ለደጃዝማቾች አርባ አርባ ብር ለወታደሮችና ለአምሳ አለቆች ስምንት ስምንት ብር ለስላም ዘበኞች አለቃ አርባ ብር ለላም ዘበኛ ወታደር አምሳ አለቆች ለወህኒ የሰላም ዘበኞችና አምሳ አለቆች ስምንት ብር ለወህኒ አዛዦች አርባ አርባ ብር ደመወዝ ተመድቦላቸው ነበር" ሲሉ ጽፈዋል።

ታሪኩ ከላይ ያለው ሁኖ ከአጤ ቴዎድሮስ ሲደርስ ይኸው ወታደር ደመወዝተኛ ሆነ። ከአጤ ቴዎድሮስ ወዲህ ምናልባት በአጤ ተክለ ጊዮርጊስና በአጤ ዮሐንስ ብሎም በአጤ ምኒልክ አልያም ደግሞ በአጤ ልጅ ኢያሱ ዘመን ለወታደር ደመወዝ መክፈል ቀንሶ ይሆናል እንጂ በምንም ይሁን በምን ለአገር ጠባቂ ኃይል ክፍያው አልቆመበትም።

የአውሮፓውያንና የቱርክን ኃይል ለመቋቋም አጤ ቴዎድሮስ ቅድሚያ ወታደር መሰብሰብ ከዚያም ደግሞ ለወታደራቸው ደመወዝ

መክፈል ይህም ብቻ አይደለም:: መሣሪያም ማምረት አስፈላጊ መሆኑን ከተረዱት በኋላ ነው ለአንዲት ኢትዮጵያ አለኝታ ለመሆን የተነሡ:: ቆርጠው የተነሡት ቀደም ብሎ ሲሆን ዋናው ግን ደግሞ ወታደር ደመወዝ መክፈል ብሎም ደግሞ የጦር መሣሪያ ከአገር ውስጥ ማምረት ዋናው ዓላማቸው ነበር:: በተለይም ከልጅነት ጀምረው የቱርክን ኃይል ያዩት በመሣሪያ ብልጫና በወታደራዊ ሥነ ሥርዓት የታነጸ በመሆኑ እርሳቸውም ይህን ሲያደርጉ ኢትዮጵያ ስትከበር ታየቻቸው::

ታደሰ ቴሌ ሳልቫኖ <u>የአናብስት ምድር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 15"አጤ ቴዎድሮስ ወታደራዊ ስለነበሩና ወታደራዊ ውጥኖቻቸውም ከኃያሷ የቱርክ መንግሥት ጋር ያጋፋኛል ብለው ራሳቸውን ስላሳመኑ፤ወታደሩና ባላገሩ መካከል በምግብና በተመሳሳይ ፍላጎቶች የተነሣ የነበረውን አለመፈቃቀዶች ለማስቀረት ለወታደር ቋሚ ደመወዝ መክፈል ጀምረው ነበር::"

"ጦሩ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የሚያጋጥመውን የምግብ ችግር ለመቆጣጠር የእህል ጎተራ ሲያቋቁሙ ቱርኮች ምጽዋን ዘግተው ስለነበር ንጉሡ የሚያስፈልጋቸውን የጦር መሣሪያና ጥይት ለማግኘት ስለተቸገሩ ራስን በሀገር የማስታጠቅ ጥረት አደረጉ" ሲሉ ጽፈዋል:: ይህ ሁሉ የተደረገው እንግዲህ ጎንደር ደብረታቦር ጋፋት ላይ ነበር::

<u>መይሣው ጋዜጣ</u> ሚያዝያ 16 ቀን 1992 ዓም ገጽ 3 "በዘመኑ አብዮት የመራ ሠራዊትን በቋሚ ደመወዝና ማዕረግ የመራ፤ባርነትን የከለከለ፤የመጀመሪያውን የመንገድ ሥራ ያስጀመረ፤አብሮ እየቆፈረም የሠራ ባሕር ኃይል የማቋቋም ዓላማውን በጣና ሐይል ላይ ታንኳ በማሠራት ያሳየ፤ኢትዮጵያ ራሷን ከጠላቶቿ ሁሉ ለመከላከል ጠንካራና የተደራጀ የተማከለ ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ያለው በዲሲፕሊን የሚመራ ሠራዊት::"

"እንደሚያስፈልጋት አምኖ ተግባራዊ ለማድረግ ቀን ከሌት የጣረ የማሰነ፤የተንከራተተ ታክስና ግብር ለአገርና ለመንግሥት አስፈላጊ መሆኑን አምኖ የደነገገ ግን ደግሞ መሃይምነትና ድንቁርና በፈነጨባቸው እንቅፋቶች ተግባሩ የተሰናከለ ከድሀው ሕዝብ መካከል መጥቆ እግዚአብሔር ጉልበቱን ብርታቱንና ፅናቱን ሰጥቶት



ጠላቶቹን ሁሉ በጦር ሜዳ ገጥሞ እየረታና እያሸነፈ ስሙና ታሪኩን ለዝንታለም የተከለ:: ወታደሩን በደመወዝ የቀጠረ መሪ ቴዎድሮስ ነበር" ሲል ጋዜጣው ጽፏል::

ቀደም ሲል የነበረው የመንግሥት ወታደር ከአርሶ አደሩ ቤት ገብቶ ያገኘውን በልቶ ነበር የሚኖረው እንጂ ደመወዝ አልነበረውም:: በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ተማሮ ኑሮአል:: ምክንያቱም ከቤቱ ሊያድር የመጣው ወታደር "በቂ ምግብ አላበሉኝም" ብሎ መክሰስ ይችል ነበር:: መንግሥት "ወታደሬን ያልቀለብክ እኔን በመናቅ ነው"ብሎ አርሶ አደሩን ያሰቃየው ነበር::

አንዳንዱማ ምግብ ብቻ ሳይሆን ሚስትህንም ስጠኝ የሚል ጣፋርዲ ነበር:: በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ የመንግሥትን ወታደር "ተሠሪ" ይለዋል:: ይህ ተሠሪ ሕዝቡን ያሰቃየ መሆኑን አጤ ቴዎድሮስ ስለተረዱ ገና ሳይነግሡ ልጅ ካሳ ሲባሉ ጀምሮ ሰዎቻቸው ከሰው ቤት ገብተው አይበሉም ነበር::

"ቸር ተመኝ ቸር እንድታገኝ"የሚባለው በእርሳቸው ደርሶ ሲነግሡ ዓላማቸውን በተግባር ለማዋል ሲሉ ቅድሚያ በቤተ ክሕነቱ ተይዞ የነበረው መሬት የመንግሥት መሆኑን አወጁ:: አከታትለውም ሕዝቡ ለመንግሥት ግብር ይከፈል እንጂ ወታደር ከቤቱ አይገባበትም ብለው ሲያውጁ በተሠሪ ላይ ጥላቻ የነበረው ሕዝብ አዋጁን በደስታ ተቀብለ::

•

Richard Pankhurst <u>STATE & LAND IN ETHIOPIAN HISTORY</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 93 **Tewodros endeavoured at the same time to establish a regular paid army on modern lines, and soon after his coronation in 1855,introduced payments for his troops, obliging them to pay the peasantry for whatever food they required This great reform** ትርጉም::

"በተመሳሳይ ጊዜ አጤ ቴዎድሮስ ደመወዝ የሚከፍለው ዘመናዊ መደበኛ ሠራዊት ለማቋቋም በ1855 ዘውድ እንደጫኑ ወዲያው ለወታደሮቻቸው ክፍያ በመፈጸም ከገበሬው ለሚሰበስቡት ማንኛውንም ምግብ እንዲሰበስቡ በማስገደድ ይሄንን ትልቅ ማሻሻል አደረጉ" ሲሉ ጽፈዋል::

የቀድሞ ባሕር ኃይል መለዮ ለባሾችና ሲቪል ሠራተኞች የኅብረት ሥራና መረዳጃ ማኅበር የኢትዮጵያ የባሕር ጠረፏና ባሕር ኃይሏ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 97 “አጤ ቴዎድሮስ በመጀመሪያ የወሰዱት እርምጃ ወደ 60 ሺህ የሚጠጉ በመንግሥት ደንብና ወጭ የሚተዳደሩ በንጉሡ ወይም በጦር አበጋዛቸው እዝ ሥር የሚውሉ ቋሚ ጦር ማቋቋም ነበር። ቀጥሎ የዚህን ጦርና ማዕከላዊ መንግሥት ወጪውን የሚሸፍን የገቢ ምንጭ ለመፍጠር ከሕዝቡ ከእርሶ አደሩና ከቤተ ክርስቲያን መሬት በመውሰድ ለማዕከላዊ መንግሥት የሚሰበሰብ ግብርና አስራት ተደነገገ” ሲሉ ጽፈዋል።

## ምዕራፍ 8

### የጋፋት እንዱስትሪና በጣና ባሕር መርከብ ሥራ!

ስለ አጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ለማወቅ ሲጀመር ቅድሚያ የምትነሣው ጋፋት ናት። ጋፋት የምትገኘው ጎንደር ክፍለ ሀገር ደብረታቦር አውራጃ ፋርጣ ወረዳ ለደብረ ታቦር ከተማ ቢበዛ 5 ኪሎ ሜትር (ጋሻ) ይርቅ ይሆናል። ባሁኑ ወቅት የደብረ ታቦር ከተማ ባሕር ዛፍ እየሰፋ ሂዶ ሳይጠጋት አይቀርም።

በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ሥልጣኔ ጮራ የፈነጠቀበት ጋፋት፤የምትገኘው ደብረታቦር ከተማ በሰሜን በኩል ነው። ይህ ቦታ በስማቸው የሚጠሩባት ነገደ ጋፋት የእጅ ሥራ አዋቂዎች ሸማኔዎችና ቀጥቃጮች ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በሰላምኮ አካባቢ ይኖሩ ነበር። ጋፋት በኢትዮጵያ ታሪክ ሠፊ ምዕራፍ የሚሰጠውና ሊሰጠውም የሚገባው በተለያዩ ምክንያቶች ነው።

አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን ለማሰልጠንና ዘመናዊ ለማድረግ የነበራቸውን ሕልም እውን ለማድረግ ባቀዱት መሠረት ማንበብና መጻፍ እንዲሁም የቴክኒክ እውቀት የሚሰጥበት የዘመኑ የኢንዱስትሪ ማዕከል ትምህርት ቤት የተጀመረበት አጤ ቴዎድሮስ ከአውሮፓ አገሮች የጦር መሣሪያ በስጦታ ወይም በሽያጭ ከማግኘት ይልቅ መሣሪያዎቹን በአገራቸው ማሠራቱ ከጥገኝነት እንደ



ሚያድናቸውና የፖለቲካ ነጻነታቸውን እንደ ሚያስከብርላቸው ስለተገነዘቡ በወቅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን አውሮፓውያንን አሰባስበው አንድ ላይ በማስቀመጥ መድፍ፤አዳፍኔ፤የመድፍ ቀለሀና መኅተቻ ጋሪ ያሠሯቸው ጋፋት ላይ ነው። በ1850ዎቹ ዓመታት ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ አስደናቂ የሆኑ የአውራ ጎዳና መንገድ አውታሮች ተዘርግተዋል።

ፍቅሬ አቦሰጥ፤ የደብረ ታቦር ዳግማዊ ቴዎድሮስ ት/ቤት 50ኛ ዓመት በዓል በተባለው መጽሔት
ገጽ 10 “ትንሿ ኮረብታ የታጠቅ ባድማ
የጠቢባን መንደር የታሪክ አውድማ
ጋፋት የትላንቱን ንገሪን እንስማ
መሪና ተመሪን አፈርና ሠሪን ዘመን አጣምሯቸው
በአንድ ይኖሩ ነበር ጋፋት ላይ ቤት ሠርተው።
ጥበብ በጨለማ ጥበብ በጥቁር ዓለም
አጎንቁሎ ነበር የአገር ልጅን ሊያድም
ዳሩ ምን ያደርጋል ማጥፋት አይችግርም
ውጥን በትካዜ የነመዩ መንደር
ጥበብ በዚህች አገር ተጀምሮ ይቅር” ሲሉ ጽፈዋል።

የጋፋት ሠራተኞችና ወታደሮች አንዳንድ የበሰሉ ካህናት “የተቀደሰ ሥራ ነው ተባበሩ” እያሉ ይሰብኩም ነበር። የሕዝብ ኃይል ተጨምሮበት የሞገድ ፍጭት ሰበቃ ከብርሃን ላንቃ መንጭቆ እንዲፈነጣር የብርሃን መብረቅ በድንገት ደመናን ሰንጥቆ የትውልድ የዘመን ድንቅ የጦር መሣሪያ ማምረቻ ሲሠራ አጤ ቴዎድሮስ ተደሰቱ። አጤ ቴዎድሮስ ሕልማቸው ከምዕራባውያን ጥበብን ለመቅሰም አቅደው የተነሡ የመጀመሪያ ናቸው። እርግጥ እርሳቸው በተለይ ያተኮሩበት ሀገራቸው የተቸገረችበትን ጉልበት ያጣችበትን የጦር መሣሪያ የማምረት ፍላጎት ከአእምሮአቸው ተቀርጾ ገና ደጃዝማች ሲባሉ ሳለ ጀምሮ ያልሙት ነበረ።

ደብተራራ ዘነብ የቴዎድሮስ ታሪክ ሊትማን ያሳተመው ገጽ 11“ደጃዝማች ካሣም ጣቁሳ ሰው ድባ ላይ የእንጨት መድፍ አስፈልፍለው በላይ በላይ ብረት (ጠምጥመው) ብረት ገጥመው የብረት አፈር አድርገው ለጉመው ደግመው ባሩድ በሸክላ አድርገው ምድሩን ጎፍረው የሚዋጋቸው ጦር ከሚሰፍርበት ውስጥ ቀብረው

በረጃጅም ቀርቅሃ ባሩዱን (ቀረ ጠንቅ)አድርገው ውስጥ ለውስጥ ከምሽጋቸው ድረስ አመጡት ለመተኮስ እንዲመች ያን ጊዜም ከደጃች ካሣ አንድ ሰው ተያዘ ያደረጋችሁት ጥበብ ምንድር ነው ንገሩን ያለበለዚያ እናርድሃለን ባሉት ጊዜ ይህን ሁሉ ምሥጢር ተናገረ" ሲሉ ጽፈዋል።

የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1848 እስከ 1966 በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 34"የግብጽን መድፍ አይበገሬነት በተከታዮቹ መሥዕዋትነት ከተገነዘበ በኋላ ግንድ ፈልፍሎ ባሩድ በመቅበር ከሩቅ የሚፈነዳ መድፍ ለመሥራት ሞከረ። ይህንንም ሥራ ላይ ለማዋል እየተዘጋጀ እያለ ከወታደሮቹ አንዱ በጠላት እጅ ወድቆ ሲመረመር ሥቃይ ቢበዛበት ምሥጢሩን ስላወጣ የዚህ የመጀመሪያ ሙከራ ውጤት ሳይታወቅ ቀረ። በኋላም ቴዎድሮስ የውጭ መንግሥታትን ያለመታከት ይወተውት የነበረው መሣሪያ ስጡኝ በማለት ሳይሆን ለኢትዮጵያውያን መሣሪያውን የመሥራት ጥበብ የሚያስተምሩ ጠቢባን ላኩልኝ እያለ ነበር" ሲሉ ሊቀ ጠበብት ባሕሩ ዘውዴ ከግንድ አስፈልፍለው ለማሠራት ያደረጉትን ጥረት ጽፈውታል።

አንዳንዴ ዛሬ ላለን ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሌሎች ዓለም ይልቅ ሠልጥኖ የነበረ በጀግንነትም አንቱ ተብሎ የነበረ የባሕር ኃይል ከፍተኛ ጀብድ ይሠራ እንደነበረ ሀብታም አገር እንደነበረች፣ በሃይማኖት ከሕገ አበው እስከ ሕገ ኦሪት ከሕገ ኦሪት እስከ ሕገ ወንጌል ብሎም ሕገ ቁራን ሲጀመር ጀምሮ።

ኢትዮጵያውያን ምሁሮቿ ከፍተኛ የሆኑ ታላላቅ ሰዎች ነበሩባት ብዬ ከባልንጀሮቼ ጋር ስንወያይና በተለያዩ መጣጥፎችና የስዕል ድምጽ ቴሌቪዥን በዘመናዊ ጭንቅላታቸው በተሰረቀው ምሁራን የሚነገረውን ንግግር ስመለከትና የታሪክ መጻሕፍትን ሳነብ ከማን ጋር መተማመን እንደምችል ግራ ይገባኛል። ዛሬ ያለው ትውልድ የሚያምነው "ኢትዮጵያ ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸውን ዕውቀቶች ከነበሯት ለምን ትንሽ ጭላንጭል ቢጤ የላትም" እያሉ ይከራከሩኛል።

በእርግጥ አባባላቸው ትክክል ነው ትውልዱ የሚያምነው በዓይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን ስለ ሆነ አልፈርድም። በመጀመሪያ ኢትዮጵያን ሊወሩ የመጡት ሕንዶች በ1985 ዓመተ ዓለም ንጉስ



ራማ የሚባል ገዥያቸው በኢትዮጵያዊው ንጉሠ ነገሥት አጤ ጲኦሪ ዘመን የዘመቱ ሲሆን ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ሲሞት ወራሪው ራማም ሙቶ ቀርቷል። ግብጽም ኢትዮጵያን ልትወር መጥታ ተሸንፋ ስትመለስ የኢትዮጵያ መንግሥት ግብጽን ተከትሎ በመያዝ ለ400 ዓመታት ገዝታለች። ይህን ታሪክ አውሮፓውያን መግዛቷን ባይክዱም የገዛችበትን ዓመት ግን ዝቅ ለማድረግ ሞክረዋል።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ-አክሱም-ዛጉዬ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 118"40 ዓመት" ይሉና ዝቅ ብለው "61 ዓመት" ይሉና "75 ዓመት" የመጨረሻው ደራሲ ያለውን ሲዘግቡ" 293 ዓመት" ኢትዮጵያያውያን ግብጽን ማስተዳደራቸውን አውሮፓውያን የተለያዩ ደራስያን ከላይ የተዘገበውን ቁጥር በመስጠት ጽፈዋል።

ሁሉም ኢትዮጵያ ግብጽን በቅኝ ግዛት የያዘች መሆንዋን ይስማማሉ። ስለዚህ ኢትዮጵያውያንንም ከግብጽ አባሮ ያስወጣ የፋርስ ሥርዎ መንግሥት ሲሆን ኢትዮጵያውያን ከዛሬው የሱዳንና የግብጽ ደንበር ላይ ወራሪውን መልሰዋል። የግሪክ አሌክሳንደር ግብጽን ወሮ ኢትዮጵያን ለማንበርከክ አስቦ ሳይሳካለት መቅረቱ እንዲያውም ለስለላ ኢትዮጵያ መጥቶ መታሰሩን የታሪክ መጻሕፍት ዋቢ ናቸው።

ጳውሎስ ኞኞ የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት በተባለው መጽሐፍ ገጽ 7 "አሌክሳንደር ዝቶ እንደተነሣው ከግብጽ ጀምሮ እስከ ሕንድ ድረስ አስገበረ። በመሐል ግን ኢትዮጵያ ከገባሪዎች ተነጥላ ቀረች። አሌክሳንደር ስለ ኢትዮጵያውያን ጀግንነት ሰምቶ ነበርና ከኢትዮጵያውያን ጋር ጦርነት ለመግጠም ፈራ። ስለኢትዮጵያውያን የሚነገረው ጀግንነትም እውነት ስላልመሰለው ራሱ አሌክሳንደር ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ለመሰለል ተነሣ።"

"ክሮኒክልስ ኦፍ ጆን ቢሾፕ ኦፍ ኒኩ በሚባለው መጽሐፍ ላይ እንደሚተርከው አሌክሳንደር ከምርጥ የጦር አለቆቹ ጋር ሁኖ ሁሉም ተራ ሰው መስለው ለመሰለል ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ህንደኬም አሌክሳንደር ተራ ሰው መስሎ ወደ ኢትዮጵያ ለመሰለል መግባቱን ሰማች።"

"ንግሥቲቱ እነኚያን እንግዳ ተራ ሰዎች ወደ ቤተ መንግሥትዋ አስጠርታ እንዲህ አለች። ዓለምን አንቀጥቅጠህ የገዛህ ታላቁ እስክንድር ሆይ ዛሬ በሴት እጅ ተይዘሃል ስትለው ንጉሡ በመታወቁ ደንግጦ ጥበቧን አደነቀ። የኢትዮጵያን ወታደር ብዛትና የሰላዮቿን ጥበብ አድንቆ ንግሥት ሆይ የተነገረኝ ሁሉ እውነት ነው። ይህ በጦር የማይፈታ ሕዝብ ነውና እኔና አንቺ ተጋብተን ዓለምን እንግዛ አላት" ሲሉ ግሪኮች የጻፉትን አቶ ጳውሎስ ኞኞ ወደ አማርኛ ተርጉመው ጽፈዋል።

የግሪክን ኃይል ከግብጽ ያስወጣው የሮማውያን ኃይል ቢሆንም እንዲሁ ኢትዮጵያን ሊወር ሲመጣ አባቶቻችን ቀጥተው መልሰውታል። የሮማውያንን ኃይል ከግብጽ ያስወጣው መሀመዳውያን ነበሩ። እየዋሉና እያደሩ ግብጽን በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው የዓባይን ጥቅም ከተረዱ በኋላ በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ሲያደሚት ቆይተዋል። ሌሎች አገሮች ለማደግ ሲጀምሩ ቅድሚያ የሚወሩት ግብጽን ሲሆን ግብጽን ከያዙ በኋላ የሚታያቸው ኢትዮጵያን ማንበርከክ ነበር።

ይህም ከቀድሞ ጀምሮ ተያይዞ የመጣው የዓባይን ወንዝ ለመያዝ ኋላ ደግሞ ቀይ ባሕርን ለመንጠቅ ነበር። ታዲያ ኢትዮጵያ ይህን ሁሉ የመጣባትን ጦር የምትመልሰው ኋላ ቀር በሆነ መሣሪያ ነበር። ከውስጥ በሚነሣው የሥልጣን ሽኩቻ እየታገዙ ቱርኮች ለኢትዮጵያ ጥፋት አስተዋጽኦ አድርገዋል። በ18ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ በዘመነ መሳፍንት ተከፋፍላ በመኖርዋ ጠላቶች ዳር በዳር እንደጉንዳን ከበው ያዋክቧት ጀመር። በዚህ ወቅት በ19ኛው ክፍለ ዘመን ግማሽ ላይ አጤ ቴዎድሮስ ከልጅነታቸው ጀምረው በተደጋጋሚ ቱርክን ይደበድቡ ነበር።

በተለይ የቆሰሉ ጊዜ የተማረከውን የጦር መሣሪያ በጥሞና ካስተዋሉ በኋላ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ካልሠራች በቀር ከወረራ አትድንም ብለው በማቀድ በሀገራቸው የጦር መሣሪያ ለማምረት ጥረት አድርገዋል። ጥረታቸው ግቡን ሊመታ ችሎ ነበር ነገር ግን "ንቅናቂ ሳለ ማን ጥሩ ይጠጣል" እንደሚባለው ይህ የበስማም ቂስና ለሥልጣን እንጂ ለአገር እድገት ፍላጎት የሌላቸው መኳንንቶች ከውጭ ኃይሎች ጋር ተባብረው ጥረታቸውን አከሸፉት።



ለእንግሊዝ መንግሥት የጻፉት ደብዳቤ መሣሪያ የሚሠራ ጥበበኛን እንዲልኩላቸው እንጂ እነሱ የሠሩትን ጠበንጃ እንዲሸጡላቸው አልጠየቁም! አጤ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ብረታብረት የሚሠሩትን አሪታውያን ብረት ቀጥቃጮችን ወሎና ጎንደር፣ጎጃምና ሸዋ ሞረቴ፣ ደንቢያ ደብረታቦር ጋፋት ላይ እንዲሰበሰቡ በማድረግ ተፈላስፈው መድፍ እንዲሠሩ አድርገዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ከዛሬ 152 ዓመት በፊት ጀምረው ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ታምርት ብለው ጣሩ። ከዚያ ወዲህ የተፈጠሩት ነገሥታት በዘረኝነት መደባደብ እንጂ የራሳችን መሣሪያ ይኑረን ብሎ የተነሣ መሪ ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ብቻ ናቸው። ይህ ደግሞ በታሪክ ሊካድ የማይችል ሐቅ ነው። እርሳቸው ዓለም አቀፍ ጥላቻ እያለባቸው ከአገር ውስጥ በዘረኞችና በሴረኞች እየተደበደቡ አገሪቱ መሣሪያ እንዲኖራት ራሷን እንድታስጠብቅ ለማድረግ ታጥቀው ተነሡ። እንዲያውም አንዳንዶች መቀለጃ አደረጉአቸው።

ዮሐንስ ሙሉጌታ <u>አጥፍቶ መጥፋት</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 151 "የጦረኝነት ስሜቱ ከፍተኛ የሆነውና ግዙፍ የጦር ሠራዊት ያቋቋመው መሪ ደግሞ ታላቅ ግምጃ ቤት መፈለጉ የታወቀ ነው። በኢትዮጵያ የአርበኞች ታሪክ ውስጥ ቴዎድሮስን ማንሣት በመንግሥቱም በተቃዋሚውም በኩል ፋሽን ሆኖ ነበርና።"

"በአጤ ቴዎድሮስ ጋፋት የመድፍ ሥራ ስያሜ ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር በሆነ ወጭ ፋብሪካ ሊቋቋም ቻለ። በተመሳሳይ ሁኔታ ከአምቦ 12 ሜትር ርቀት ላይ ባለው ሥፍራ ልዩ ልዩ ዓይነት የጦር መሣሪያ ከጥይት እስከ መድፍ ድረስ የሚያመርት ታላቅ ፋብሪካ ሆርሜት በሚል ስያሜ ተቋቁሞ በሰኔ 1982 ብቻ ከ3500 ሠራተኞች በላይ ቀጥሮ ሥራ እንዲጀምር ተወሰነ።"

ይሉና "የፕሬዚዳንቱ የዘወትር ሕልም መጨናገፍ ስለሌለበት በኮሪያ ባለሙያዎችና በኢትዮጵያውያን መሐንዲሶች አማካኝነት ሲሠራ የነበረው የሆርማት ኮንስትራክሽን ሥራ አልቆ በየካቲት 1983 በሠውር የምረቃው በዓል ተካሄደ። ብዙ የተወራለትና ለብዙዎች አገሮችም የጦር መሣሪያ ሊያቀርብ ይችላል ተብሎ የተገመተው ፋብሪካ ሳይንቀሳቀስ ጦርነቱ ሌላ መልክ እየያዘ መጣ። ኢሕአዴግ

ወደ ሆርማት ቀጥሎም ወደ አዲስ አበባ ተጠጋ የተረቱ መጨረሻ ሆነ" ሲሉ ጽፈዋል።

ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አገር ጥለው ወጥተዋል መሣሪያው ተሠርቶ ቢሆን በ1990 ዓም ከሻዕቢያ ጋር ጦርነት ሲጀመር ከተለያዩ አገሮች ሩጫ ባልተደረገም ነበር። ወያኔዎች እንኳን አዲስ መሣሪያ ሊሠሩ ቀርቶ ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በግዥና በልመና ያከማቹትን መሣሪያ ሻዕቢያ የወሰደውን ወስዶ የተረፈውን ሲያቃጥለው ዝም ነው ያሉት።

እስግድ ገ/ሥላሴ ወ/ሚካኤል ጋሀዲ በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 168 "ህወሓት ኢሕአዴግ እነዛ በሕዝባዊ ግምባር የተፈጸሙትን አሻጥሮችን በቅሎ ቤት የነበረውን የትጥቅ መጋዘን ማቃጠልና ሌሎች አደጋዎችን አሣምሮ ያውቃቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል። ደርግ ማለትም ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አገርን ለማዳን ለፍተዋል ሴረኞች በእርሳቸው እያመካኙ አገሪቱን ገድለዋል። ዛሬ ደርግን አመስግኖ መጻፍ ከሰይጣን አይለይም። ደርግ ሁሌም ሲሰደብ ሲወቀስ እንጂ ይህን ተግባር ተግብሯል ተብሎ በተለይም በምሁራን አይነገርም።

ሆዳሞችና መኳንንቱ የሚመኙት ጦርነት
ሥልጣን የናፈቃቸው ግለሰቦች የዘሩት ዘረኝነት
የበስማም ቄሶች አሾክሿኪነት
መቼ ይሆን አንድ ኢትዮጵያ ብሎ ጀግና የሚነሣባት?

ነገ ጎረቤቶቻችን እንደ ልማዳቸው ሊወሩን ቢመጡ እንዴት አድርገን ነው ልንመልሳቸው የምንችለው? ጎበዝ ከውሻ ጎብረት መማር ያቃተን ሴረኞች ጀግና ገዳይ ሁነናል። እንደ ትናንቱ ጋፋት፥ሆርማት ኩባንያንም አዘጉት ታሪክ ብቻ ይዘን ቀረን። አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን ታሪክ ጠንቅቀው ከማወቃቸው የተነሣ ከቱርክ ጋር ተደጋጋሚ ጦርነቶች በማድረጋቸው ኢትዮጵያ ዳር ደንበሯን ልታስጠብቅ የምትችለው በራሷ መሣሪያ ማምረት ስትችል ነው በማለት ነበር ጋፋትን የጀመሩት።

የውጭ ኃይሎች ቀይ ባሕርን ነጥቀዋል አሰብንም እንዳናገኝ ለማድረግ አፋሮችን ወያኔ ኢሕአዴግና ሻዕቢያ በማጥፋት ላይ ናቸው



ዓባይና አጋዴ የሚያመጣውን ጠንቅ ጠንቅቀን አለመረዳታችን ያሳዝነኛል። ወታደራዊ ልምድ ያላቸው የኢትዮጵያን ታሪክ ጠንቅቀው የተረዱ ሻለቃ ዳዊት ወልደ ጊዮርጊስ መዘንጋት እንደሌለብን አስጠንቅቀዋል።

ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ ክህደት በደም መሬት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 46 "የኢትዮጵያን ምድር የውጭና የመከላከያ ፖሊሲን የሚወስኑት ሦስት ዐበይት ጉዳዮች፤ ቀይ ባሕር፥ዓባይና አጋዴን ናቸው። በሰሜን ምሥራቅ በቀይ ባሕር በኩል ቀይ ባሕርን የዐረብ ባሕር ለማድረግና አክራሪ እስልምናን ለማስፋፋት የሚደረግ ግፊት ነው። በሰሜን ምዕራብ ሱዳንና ግብጽ የዐባይን ውሃና ምንጩን ለመቆጣጠር የሚያካሂዱት ትግል አለ።"

"በምስራቅ በኩል ሱማሊኛ ተናጋሪ የሆነውን ሕዝብ በአንድ ሀገር ውስጥ ለማጠቃለል ባለው የመስፋፋት ፖሊሲ ላይ የተመሠረተው ትግል ሌላው የፈተና ግንባር ነው" ይሉና ገጽ 61 "የመጀመሪያው የሶማሊያ ሕገ መንግሥት በሰኔ ወር 1961 ሲወጣ አንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በኢትዮጵያ፥በጅቡቲና በኬንያ የሚኖሩት የሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች ከሶማሊያ ጋር ወደፊት የሚዋሐዱበት ሁኔታ የሶማሊያ መንግሥት መከተል እንደሚገባው በመደንገጉ በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል ለሚቀጥሉት ዓመታት ሰላም እንዲጠፋ ያደረገ ዋናው የሶማሊያ መንግሥት የተስፋፊነት ፖሊሲ ሆነ" ሲሉ ጽፈዋል።

ሻምበል ተስፋ ደስታ የጦር ዐቅድና ብልሀት በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 88 "ዘመቻ ሁልጊዜ ያልታሰበና አዲስ ኑሮ የሚፈጥር በመሆኑ በሀገሩ ላይ ወደፊት ይደርሳል ተብሎ የሚታሰበው ሁሉ ገና በሰላም ሰዓት ተጠንቶ አስፈላጊው ቁሳቁስ ሊታሰብበት ይገባል" ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ የፈሩት አውሮፓውያን ፊታቸውን ወደ አፍሪካ ማዞራቸው የአፍሪካን ሕዝብ ሃይማኖት እናስተምር ብለው መነሣታቸው አፍሪካ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ካላመረተች ራስዋን መጠበቅ እንደማትችል ገና ልጅ ካሣ ሲባሉ ሳለ ጀምሮ ተረድተዋል። የእርሳቸውን ውጥን ሌሎች ነገሥታት አገሪቱን አንድ ለማድረግ እንደተነሡት ሁሉ የጦር መሣሪያ መሥራት አለብን ብለው ጀምሩን

አጠንክረውት ቢሆን ኑሮ ዛሬ ማንም የኩታራ መሪ ኢትዮጵያን አይደፍራትም ነበር::

**Richard Pankurst <u>A SOCIAL HISTORY OF ETHIOPIA</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 323 "Gafat was manufacture of cannon,which was the most remarkable technological event of the reign.Tewodros, whose power base lay in the north-west of Ethiopia,where it was extremely difficult to import cannon,was deeply conscious of the need to manufacture such weapons in the country. He seized the opportunity of attempting to do so in 1861 when a French metal-caster called Jacquin declared his willingness to make a mortar if assisted by the other craftsmen at Gafat" ሲሉ ጽፈዋል::**

**እንደገና ከዚሁ መጽሐፍ ሲያብራሩ ገጽ 322 foundry at Gafat, which desrves an honurable place in the history of Ethiopian technology, made use, according to waldmeier, of three feet high furnaces, which were operated with the help of traditional skin bellows worked by hand,and from cega and the of 700 degrees centigrade"::**

ትርጉም የኢትዮጵያ ማህበራዊ ታሪክ ሪቻርድ ፓንክረስት "በጋፋት የመድፍ መፈብረክ የአጤ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት እጅግ በጣም አስደናቂ የቴክኖሎጂ ኩነት ነበር:: የሥልጣን መሠረታቸው ሰሜን ምዕራብ የነበረው አጤ ቴዎድሮስ መድፍ ከውጭ አገር የማስገባት የከፋ ችግር ነበረባቸው::

በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ያለውን የጦር መሣሪያ መፈብረክ ስለሚያስገኘው ጥቅም ቴዎድሮስ ጥልቅ ንቃት ነበራቸው:: እ.አ.አ. 1861 ዓም ፈረንሳዊው ብረት አቅላጭ ካኩዌን በሌሎቹ የእደ ጥበብ ሠራተኞች ከታገዘ አዳፍኔ ለመሥራት ፈቃደኛነቱን ሲገልጽ አጤ ቴዎድሮስ በእድሉ ተጠቀሙ::" 2ኛ " የጋፋት የብረት ማቅለጫ በኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ታሪክ ተገቢውን ስፍራ ሊሰጠው ይገባል ዋልድሜር እንደጻፈው ሦስት ጫማ ከፍታ የነበራቸው ምድጃዎች በባህላዊ የቆዳ ወናፍ በእጅ እየተገፋ እስከ 700 ሴንት ግሬድ ይግል ነበር::"



አበባው ይግዛው <u>የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ</u> ጥር 25 ቀን 1965 ዓም "አጤ ቴዎድሮስን ለሞት ያበቃቸው የጥበብ ፍቅር እንደሆነ ግልጽ ነው" ሲሉ ጽፈው ነበር:: የዛሬው ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የአጤ ቴዎድሮስ ብረታብረት ፋብሪካ በሚል ርእስ ከቦታው ተገኝተው የሀገር ሽማግሌዎችን እነብላታ አግማሴ መኮንንን አነጋግረው ዘርዝዘር ያለ ሰፊ ዘገባ ጽፈው ነበር:: ክፍል አንድ "መግቢያ" ላይ ገልጸውታል::

**<u>Darrell Bates The Abyssinian Difficulty</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 31 two years later when emperor gave them a place of their own at Gaffat, near his own new headquartters at Debra Tabor, whre they could at last build themselves proper houses, a worshop, and a school.**ትርጉም "ከሁለት ዓመታት በኋላ አጤ ቴዎድሮስ በጋፋት ጠቅላይ ሠፈራቸው በነበረው በደብረታቦር አጠገብ የራሳቸውን ቦታ ሰጡአቸው:: እዚያም ተስማሚ መኖሪያ ቤቶች የሥራ ክፍሎችና ትምህርት ቤቶችን ገነቡ::

ጋፋት የአጤ ቴዎድሮስ መድፍ የተሠራበት ቀደም ሲል ጋፋት የሚባለው ጎሳ ይኖርበት የነበረ ከመሆኑም በላይ ከዚህ ቦታ ጥበብ ይሠራ ነበር:: ለምሳሌ ሸክላ፥ማጭድና መጥረቢያ የቆዳ ሥራ ይሠራበት ነበር:: ዛሬ ከባሕር ዳር ጎንደር ስትሄዱ ወረታ ገቢያውን ሞልቶት የምታዩት የተለያዩ የቆዳ ሻንጣና አገልግል ሌላም ሌላ የጋፋት ውጤት ነው::

አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ ታላቅ ራእይ ነበራቸው:: የዛሬ 154 ዓመት የጦር መሣሪያ ሊሠራ የተነሣ ከእርሳቸው በመቀጠል ማንም አልነበረም:: ከዚያ ወዲህም ደግሞ ርእሰ ብሔር መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ብቻ ናቸው:: እርሳቸው እንዲያውም በ1981 ዓም ግንቦት 8 ቀን መገልበጠ መንግሥት እንዲደረግባቸው በራሻ ጄኔራሎችና በሰላዩ ድርጅታቸው አማካኝነት የተጠነሰሰ ሴራ የጦር መሣሪያ ለመሥራት በማቀዳቸው ምክንያት ነው:: ለዚህም <u>ነበር ቅጽ</u> ሁለት የተባለውን መጽሐፍ ማንበብ ይጠቅማል::

<u>ሊቀ ጠበብት ሮቢንሰን</u> ስለ አጤ ቴዎድሮስ ብዙ ጽፈዋል:: ብዙም በንፋስ ድምጽ በራዲዮን ተናግረዋል:: እርሳቸው በጀርመን_ሬዲዮ

እንዲህ ይላሉ "የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ አባት አጤ ቴዎድሮስ ናቸው። የኢትዮጵያ አባትነታቸውን ስለ ግዛት አንድነቷ ጥንካሬ እና ተራማጅነት ያላቸውን ራእይ በግልጽ አሳይተዋል። በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያው ንጉሠ ነገሥት ናቸው ብዬ አምናለሁ።"

"በጊዜው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ የውጭ ኃይሎች ተጽዕኗቸውን በአፍሪካ የጦር መሣሪያ ባለቤትነት ወሳኝ መኾኑ በግልጽ የታወቀበት የአፍሪካ ቅኝ ገዥዎችም ይህንኑ የተረዱበት ወቅት ነበር። ይህን የዲፕሎማሲ ጥበብ እና የጦር መሣሪያ ሀብት ሚና ጠንቅቀው ከተረዱት ንጉሠ ነገሥታት መካከል አጤ ቴዎድሮስ አንዱ ናቸው ብዬ አምናለሁ" ብለዋል።

ናደው ከበደ <u>ሙዳይ መጽሔት</u> ጥቅምት-ሕዳር 1986 ዓም ገጽ 20 "ከምዕራባውያን ጥበብን ለመቅሰም አቅደው የተነሡት የመጀመሪያው ንጉሥ ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ መሆናቸውን በተለያዩ የታሪክ መጻሕፍት ተጠቅሷል። እርግጥ ቴዎድሮስ የፈለጉት ዕደ ጥበብ በጦር መሣሪያና ጥይት ላይ ያተኮረ መሆኑ አይካድም። ይህም ፍላጎታቸው ራሱን የቻለ ምክንያት ነበረው።"

"አጤ ቴዎድሮስ የውስጥ ተቃዋሚዎቻቸውን ለማንበርከክና የውጭ ወራሪዎችን ለመቋቋም መሣሪያ ያስፈልጋቸው እንደነበር አያጠራጥርም። እኒያ ከጊዜያቸው ቀድመው አገራቸውና ሕዝቦቻቸው ሳይዘጋጁ አንዲት ኢትዮጵያን ለመመሥረት የጦር መሣሪያ እደ ጥበብን በዘዴ ሳይሆን በኃይል ወደአገራቸው ለማስገባት የሞከሩት ቴዎድሮስ የራሳቸው እቅድ መሰናክል ሆኖ ጥሏቸዋል" ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ካሰቡት ለመድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ አስተዳደር መተዳደር አለበት ማለት ብቻ ሳይሆን ለብዙ መቶ ዓመታት ቀጥቃጭ ተብሎ ይናቅና ይሰደብ የነበረውን ክፍል ከፍ አድርገው በማየት በልማት ተግባር እንዲሰለፉ አድርገዋል።

<u>አዲስ ነገር ጋዜጣ</u> ቅዳሜ መጋቢት 13 ቀን 2000 ዓም ገጽ 17 "አጤ ቴዎድሮስ ባለ እጆችን መናቅ እንዲቀር ባለ እጆቹ ለአጤ ቴዎድሮስ ሠረገላ የሠሩላቸው ሲሆን ነፍጣቸው ሲበላሽም ይጠግኑላቸው ነበር። የውኃ ወፍጮም በአቅራቢያው ተክለው ነበር። ባለ እጆቹ ይሠሩበት



የነበረው ወርክ ሾፕ በደብረታቦር አቅራቢያ በጋፋት እስከ አሁን አለ። ሚሲዮናውያኑ በአንድነት ትምህርት ቤት ከፍተው ነበር።"

"አጤ ቴዎድሮስ በአገራቸው የሚናቁትን ዘመናዊነት ለማየት የሚያስችሉ ተቋሞች ማኅበራዊ መሠረቶች ብሔራዊ አስተዳደር የከተማ ምሥረታ እና የመሳሰሉት አልነበሩም! አይታወቁምም ነበር። የፊውዳል መደቡ ያልደረጀ እና አገሪቱ የሚያስፈልጋትን የውጭ ርዳታ ያላገኘች ነበረች" ሲል ጽፎአል።

ዮሐንስ መሸሻ <u>ኢትዮጵያ አስተዳደር እና ፖለቲካዊ ሂደት</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 37 "አጤ ቴዎድሮስ በሀገሬ ውስጥ መድፍና ጠመንጃ የሚሠራበት ቤት ለማቆም በጋፋት ጀምሬአለሁና የዚህን ጥበብ የሚያውቁ በርከት ያሉ ሰዎች ከነመሣሪያቸው የእንግሊዝ መንግሥት ካላከልኝ እስረኞቹን አልለቅም በማለታቸው ከመዋረድ ይልቅ ሕይወታቸውን አሳልፈው የሰጡት በጦር መሣሪያ ፍለጋ መንሥኤ ጭምር ነበር።"

"ቦምባ የሚሉት መድፍ በኢትዮጵያ ታይቶ የማይታወቅ ታላቅነቱም ሰው እየገባ የሚወጣበት ይህንን አሠርተው ይዘው ነው። ቦታውም ደብረታቦር አጠገብ ጋፋት ይባላል። ሠሪዎቹም ከፈረንጅ አገር እነ ዋልትማየር ነበሩ ይላል አለቃ ወልደ ማርያም" ሲሉ ጽፈዋል።

በጋፋት የተሠራው ከዚህ በላይ ያለውን ጥቅሶች አንብበናል። ከዚህ በታች የምናየው ደግሞ አጤ ቴዎድሮስ በጣና ኃይቅ ላይ መርከብ ለመሥራት የጀመሩ ጀግናም ናቸውን ነው።

ፍሥሐ ይሁን <u>መጽሐፈ ቡዳ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 47 "ጋፋት በተባለች ከደብረታቦር አራት ኪሎ ሜትር ያህል እርቃ ከምትገኝ አንዲት ጎጥ መንደር ውስጥ ሰፍረው ሥራቸውን እንዲጀምሩ አዘዙአቸው። በዚህም ቦታ የአውሮፓውያን ዓይነት ቤት ሠርተው የብረታ ብረት መቀጥቀጫ ቤት አሰናዱ።"

"አጤ ቴዎድሮስ እነዚህን አውሮፓውያን በበለጠ ለመያዝ እንዲያመቻቸውና ከአበሻ አገርም ለመውጣት እንዲያግታቸው ለማድረግ አስበው ሚስት እንዲያገቡ ሲያዟቸው ሁሉም በደስታ አገቡ። ይህችም ትንሽ የአውሮፓውያን ከተማ በለጸገች። አጤ

ቴዎድሮስ የተግባረዕድን ሥራ እንደጀመሩት ቀጣዩ መንግሥት ቢገፋበት ኖሮ ይህጊዜ ባለጅ ቀጥቃጩ ሁሉ በጥበብ ሰልጥኖ ጥበብ ይሠራ ነበር::"

"እንብቤአለሁ ብዙ መጻሕፍት
የሚያስደንቀኝ ትልቅ ታምራት
ታሪክ አላገኘሁ እንደ ቴዎድሮስ
የሳቸውን ታሪክ ሳስብ ሳስታውስ
የሚያስቡት ሁሉ ለሀገር እድገት
ኢትዮጵያ እንድትሆን የጥበብ ባለቤት" ሲሉ ጽፈዋል::

<u>የእሥራት ዘመን በሐበሻ አገር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 116 "አጤ ቴዎድሮስ በጣና ባሕር ላይ የሚንሳፈፍ ጀልባዎችን ለማሠራት ያላቸው እምነትና ፍላጎት የጸና ስለነበር ሌሎች እንዲረዱላቸው ሲሉ ራሳቸው ወርደው መርከብ መሥራት ጀመሩ:: ስፊ ወለል ያለውና በከባድ መንኮራኩር የሚንቀሳቀስ ጀልባ ሠሩ:: እንዲያውም ፓድል ስቲመር ፈልፍለው ሠርተው ነበር:: ዳሩ ግን የሎኮማቲቭ ክፍል ሳይሠራ ቀረ::"

"ጀልባዋ ብዙ ጊዜ ከባሕሩ ውስጥ እናያት ነበር:: ጀልባዋን የሚያንቀሳቅሰው ሁለቱ መንኮራኩር በጣም ትልቅ ስለነበር ወደ ውኃው ውስጥ ጠልቆ እንዲገባ ለማድረግ በመቶ የሚቆጠር ሰው ያስፈልገው ነበር:: በዚሁ ጀልባ ሥራ መንፈሳቸው በጣም ተመስጦ ስለነበረ ጊዜያቸውን በሙሉ ለዚህ ተግባር ስላዋሉት ከሠፈራቸው አራት ማይልስ እርቀ ከሚገኝ ሥፍራ ላይ ኃይለኛ ጠላት ተነሥቶ ሳይሰሙ ቆይተዋል" ሲሉ ጽፈዋል::

<u>የኢትዮጵያ የባሕር ጠረፏና ባሕር ኃይሏ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 99 "የጀልባው ግንባታ ሆነ የጀልባ ሥልጠናው ለተዋጊው ኃይል የተሰጠው በድብቅና በስውር ነበር"ሲሉ ጽፈዋል::

ከላይ በሊቅ ዶ/ር ብላንክ አጻጻፍ የመርከብ ሥራው ሲሠራ ያዩ መሆናቸውን ሲሆን ኢትዮጵያውያን ከጻፉት ላይ ደግሞ "በድብቅና በስውር ነበር" ይሉና" አጤ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ እንግበውት የተነሡበትን ትልቅ ዓላማ ለመተግበር የወሰዷቸው የአገር መሻሻል እርምጃዎች ተራው ሕዝብ ወዶ ቢቀበልም የዘመኑ የቀበሌ



መሣፍንት ባላባቶችና ቤተ ክህነት ስላልተቀበሉት ራሳቸው ከድተው ሕዝቡንና ወታደሩንም በማስከዳት ጀግናውና ቆራጡ ቴዎድሮስ የእንግሊዝን ከፍተኛና ዘመናዊ ጦር ከጥቂት ታማኝ ወታደሮቻቸው ጋር ብቻቸውን እንዲቋቋሙ ፈረደባቸው::

አንዳንዴ ደግሞ ከመሬት ላይ ሁነው ድርጊቱን በተመስጦ ያያሉ:: ጀልባዎቹ በገመድ የታሠረ የጦር ውርወራ ያለበት ሲሆን አንደኛው ኃይል አጥቅቶ ከጀልባው ላይ የተጫነውን ቁሳቁስ መውሰድ ዋናው ተግባር ሲሆን ልክ እንደ ፈረስ ጉግስ አይነት ጀልባውን ከጀልባው አስጠግቶ አንዱ ካንዱ ጀልባ ያሉትን በትግል አጥቅቶ ንብረቱን መዝረፍ እንዴት እንደሚቻል ጥናቱን ራሳቸው እተየመለከቱ ተፈጸመ:: ጀልባ ቀዛፊዎች የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ ተለማመዱ:: ይህም ትሪት በጣና ባሕር ላይ ተፈጽሟል::

ከዚህ ላይ የምንረዳው እውነታ ቢኖር መርከብ ጀልባ መሠራቱን ነው:: አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ ወታደር ማብዛት ብቻ ሳይሆን የተጠናከረ የባሕር ኃይል እንዲኖራቸው ወሰኑ:: ይህን የመርከብ ሥራ በጥንቃቄ አስበውበታል:: ለምሳሌ በቅድሚያ ስለ ጣና ሐይቅ ሁለንተናዊ ጥናት ማስደረግ ብቻ ሳይሆን የዓባይን ወራጁን ወንዝ ሳይቀር የማዕበሉን የጉዞ አቅጣጫ ጥናት አከናወኑ::

በጣና ሐይቅ ዙሪያ የሚገኙትን በርካታ ጀልባዎች እንዲሰበሰቡ ትእዛዝ ሰጡ:: የጎብረተሰቡ የሆኑት ጀልባዎችም በእርሳቸው ትእዛዝ መሠረት ስብስቡ ተከናወነ:: ጀልባዎቹንም ለባሕር ውጊያ የተዘጋጁ አደረጉ:: ለዚህ ሙከራቸው በነዚህ ጀልባዎች ላይ ወታደሮቻቸውን በሁሊት ቡድን ከፍለው እርስ በርሳቸው እንዳይጎዳዱ ሁነው የውጊያ ልምምድ እንዲያደርጉ አደረጉ::

አሠግድ <u>ዘጋቢ ጋዜጣ</u> 1ኛ ዓመት ቁጥር 42 ታኅሳስ 11 ቀን 1990 ዓም ገጽ 7" ከአሥገራሚው የአጤ ቴዎድሮስ ታሪክ ውስጥ አንደኛው ክፍል ባሕር ላይ የሚንሣፈፍ መርከብ ለምሥራት እራሳቸው በሥራው ላይ ያበረከቱት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው:: እማኙ ታሪክ መዝጋቢ በዚሁ ጉዳይ ላይ አሥገራሚውን ሁኔታ እንዲህ ሲል ገልጾታል::"

“አጤ ቴዎድሮስ በጣና ባሕር ላይ የሚንሣፈፍ ጀልባዎችን ለመሥራት ያላቸው እምነትና ፍላጎት የጸና ስለነበረ የሌሎችን እርዳታ ለማግኘት እንዲረዳቸው ሲሉ ራሣቸው ወርደው መርከብ በመንኮራኩር የሚንቀሣቀሥ ጀልባ ሠሩ” ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ጀግና ነበሩ የምንለው ይህን የመሰለ ሥራ በመሥራታቸው ነው። ዛሬ ላለን ትውልዶች አጤ ቴዎድሮስ በጣና ደሴት ላይ መርከብ ለመሥራት ጀምረው ነበር ብለን ስንጽፍ ሕልም እንጅ እውነት አይመስላቸውም። ይህን ታሪክ በሥዕል አስደግፈው ፍሥሐ ይሁን አጤ ቴዎድሮስ ሚሠሩ የሚያሳይ ምስል ከመጽሐፋቸው ላይ አቅርበዋል።

<u>መጽሐፈ ቡዳ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 47 “አጤ ቴዎድሮስ በጣና ላይ የሚንሳፈፍ ጀልባዎች ለመሥራት ያላቸው እምነትና ፍላጎት ገና የጸና ስለነበር የሌሎቹን እርዳታ ለማግኘት እንዲረዱላቸው ሲሉ እራሳቸው ወርደው መርከብ መሥራት ጀመሩ” ሲሉና 46 አጤ ቴዎድሮስ መዶሻ በጃቸው ይዘው የጀልበዋን ጠርዝ ጨብጠው የተሣለው ምሥል ያሳያል።

ከዚያም ረዘም ያለ ግጥም ገጽ 55።
“የእቃ መጓጓዣ መርከብ ያስፈልጋል
የወታደር ድጋፍ ይሆናል የጦር ኃይል
በመርከብ እንዲሆን ምዕዋ ጉዟችን
ወደፊት አይቀርም እንሠረዋለን
አሁን ለሙከራ በጣና ባሕራችን
ጀልባ ለመሥራት ጀመረኩ ሥራውን
ዕረፍት ሳይኖረኝ ይገፎ መዶሻዬን
ከረዳቶቼ ጋር ሰብስቤ ባለጁን
ጦርነት ከሌለ ያልቃል በቅርብ ቀን
ሁሉንም ለመሥራት ጊዜ ሰላም ሲኖር
ምኞት ትርጉም የለውም ከተስፋ በሥተቀር”
ብለው አጤ ቴዎድሮስ ተናገሩ ሲሉ ጽፈዋል።



# ምዕራፍ 9

## “የኢትዮጵያ ባል የኢየሩሳሌም ውሽማ”!

በኢትዮጵያ ባህል መሠረት ብዙ ባህላዊ ጨዋታዎች አሉ። የውሃ ዋና ጨዋታ ዋሽንት መንፋት፣ገና መጫወትና ትግል መግጠም ምክቶሽ፣ ጃሎ ብሎ ወኒ ቀስቅሶ ማስፈከርና መፈከር፣ አልያም ደግሞ ግጥም መግጠምና በገና መደርደር ባህላዊ ጨዋታዎች ናቸው። ታዲያ አጤ ቴዎድሮስ በገና መደርደር ይወዱ ነበር። በተለይ እሑድ ማታ የሚያሰሙት በገና እየደረደሩ ስለ ኢየሩሳሌም ያስቡ ነበር። የኢየሩሳሌም በቱርክ መያዝ ያበሳጫቸው ስለነበር በበገና ድርደራው እንዲህ ይሉ ነበር።

“እሱም ጌታ አይደለ እኔም የእርሱ ሎሌ
የኢየሩሳሌም ሰው ካልጫነ በርሙሌ”
በማለት ስሜታቸውን በበገናው ያሰሙ ነበር። ይህን የእርሳቸውን ድርደራ ዛሬ ድረስ ዜማው ሳይለወጥ በተለይም የሃይማኖት ዘማርያን ይዘምሩታል። ይህ እርሳቸው የሚያሰሙት የነበረውን በገና ድርደራ በአርባ ጾም በብዛት የምናደምጠው ሲሆን የተወሰኑ ግጥሞች እስከ ዜማቸው የእርሳቸው ናቸው።

አበጋዝ የምሩ <u>መይሣው</u> ጋዜጣ መስከረም 16 ቀን 1992 ዓም ገጽ 3“ ባሕር ተሻግሮ ኢየሩሳሌምን ነጻ ሊያወጣ ሲመኝ ቱርክን የማንበርከክ ትጥቁን ሲያበጃጅ” ሲሉ ጽፈዋል። መይሳው ቴዎድሮስ በበገና ድርደራው እንጻቀረበት ሁሉ ሐሣባቸውን በተግባር ለማዋል ማሠብ የጀመሩት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትና የተሰቀለበት ቅድስት አገር በቱርክ መያዙ አሳስቦአቸው ነው።

የአውሮፓውያን ካህናት በተለይም የፈረንሳይ፣ክርስቲያኖች ግንባር ቀደም ሁነው በ12ኛው ክፍለ ዘመን ኢየሩሳሌምን ነጻ ለማውጣት ከፍተኛ ትግል አድርገው ነበር። ነገር ግን ያ ሁሉ ሕዝብ አልቆ ተጠቅተው ተመልሰዋል። በዚህ ዘመን የተደረገውን ታሪክ አጤ ቴዎድሮስ ገና ወጣት ሳሉ ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ሳሉ ስማቸው

ባልታወቀው መነኩሴ መማራቸው አልቀረም። ስለዚህም ነው ተናደው እርሳቸው ነጻ ሊያወጡ ያሰቡት።

<u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 76-77 "ምንም እንኳ ሐሳባቸው ከግቡ ሳይደርስ ቢሞቱ አጤ ቴዎድሮስ የቱርክን እስላም ከኢየሩሳሌም ለማስወጣት የማያወላውል ሐሳብ ነበራቸው። በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ይዞታ የነበሩትን ሁሉ የቱርክ መንግሥት ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በመስጠቱ ተናደው ስለነበር የጦር መሣሪያ ከእንግሊዝ መንግሥት ጠይቀው በቱርክ ላይ ለመዝመት ቁርጥ ሐሣብ ነበራቸው።"

"ይህንንም ሐሳባቸውን ለመፈጸም በዘመናቸው የእንግሊዝ ንግሥት ለነበሩት ለቪክቶርያ መልእክት ልከው ነበር። ነገር ግን አጤ ቴዎድሮስ የክርስቲያን ንግሥት ስለሆንች ትረዳኛለች ብለው ለቪክቶሪያ ቢጽፋላትም የእንግሊዝ መንግሥት ከቱርክ ጋር የጦር ቃል ኪዳን ስለነበራቸው ጥያቄአቸው መልስ አላገኘም። በዚህም የተነሣ አጤ ቴዎድሮስ ከእንግሊዞች ጋር ተጣሉ። በኢትዮጵያ ታሪክ እንደምናውቀው ከሞትም ያደረሳቸው የዚሁ ጠንቅ ነው" ሲሉ ጽፈዋል።

ገድለኛው ዘለቀ <u>ምኒልክ መጽሔት</u> ቅጽ 1 ቁጥር 7 ጥቅምት 1992 ዓም ገጽ 27 "አጤ ቴዎድሮስ ከቱርክ አገዛዝ ኢየሩሳሌምን ነጻ የማውጣት ዕቅድ እንደነበራቸው በተደጋጋሚ በፍክራ ይገልጹ እንደነበር" ሲሉ ጽፈዋል። የኢትዮጵያ ባል የኢየሩሳሌም ውሽማ ማለታቸው በውጭ ኃይሎች ያስጠላቸው ዋናው ነው። ኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያውያን ቅድስት አገር ናት!በተለይ ለመሪዎች እንደ አጤ ቴዎድሮስ ላሉ የተዋሕዶ ሃይማኖት አፍቃሪ ለሆኑት ማለቴ ነው። በአጤ ቴዎድሮስ እምነት ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ኢየሩሳሌምን ከቱርክ ነጻ ለማውጣት ነበር ሕልማቸው።

በእርሳቸው እምነት ከጠነከሩ ቱርክን ከኢየሩሳሌም ማስወጣት ይቻላል የሚል ምኞት ነበራቸው በዚህ ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን ከቱርክ ነጣ ለማውጣት ታግለዋል። እንዲያውም አጤ ቴዎድሮስን ከሚገርማቸው አንዱ አውሮፓውያን ክርስቲያን ሁነው ከእስላሞች ጋር ተባብረው ክርስቲያኖችን



መደብደባቸው ያናድዳቸው ነበር። ለምሳሌ አጤ ቴዎድሮስ ያሠሩትን መድፍ አሰያየም ብንመለከት ታሪካዊነቱን ያረጋግጣል።

<u>አደራ</u> መጽሔት ቅጽ 1 ቁጥር 1 1985 ዓም ገጽ 23 "በ1854-1855 ዓም ላይ በሩሲያ መካከል የክርሚያን ጦርነት ክርስቲያኖቹ መንግሥታት እንግሊዝና ፈረንሳይ፤ጣሊያን ለጥቅም ሲሉ ከእስላም ከቱርክ ጋር በማበር ክርስቲያኗን የሩሲያ ከተማን ሴባስቶፓሉን በማስደብደባቸው ምክንያት እንዴት ለጥቅም ሲሉ ክርስቲያኗን አገር አስደበደቡ ብለው ይቆጩ ስለነበር ያሠሩትን መድፍ ሴባስቶፖሉ ብለው ሰየሙት" ሲል ጽፎአል።

አጤ ቴዎድሮስ ኢየሩሳሌም ከቱርክ ነጻ እንድትወጣ ሕልም ነበራቸው። ይህ ጠንካራ ሕልማቸው እንዳይፈታ ቤተ ክህነቱን በበላይነት የሚመሩት አቡነ ሰላማ ለግብጹ ከሊፋ መልእክት መላካቸው አልቀረም። ግብጾች የኢትዮጵያን የበላይነት አይወዱምና ፍርሃት አደረባቸው። አጤ ቴዎድሮስ ኢየሩሳሌምን ከቱርክ ለማስለቀቅ የነበራቸው ሕልም ሳይፈታ ቢቀርም ሕልማቸው ግን እርሳቸው ከሞቱ 12 ዓመት በኋላ በሎንዶን የሚኖሩ የኦሪት አማኞች ተቀበሉት። ለዚህም እነዚህ ሁለት መጻሕፍት አስተዋጽኦ አድርገዋል።

Acton Roger The <u>Abyssinian Expedition</u>, የተባለውና <u>The Abyssinian Difficulty</u> መጽሐፍ በ1860 ዓም መጨረሻ ላይ ሎንዶን ታተሙ። ከዚህ በኋላ አውሮፓ ነዋሪ ከነበሩት መካከል ጋዜጠኛውና ተዋናዩ ቴወዶር ሕርዜል የተባለው የጽዮናውያንን ድርጅት እንዲመሠረት ቅስቀሳ ማድረግ ጀመረ። ብዙም ሳይቆይ የእንግሊዝ ምክር ቤት የተቋቋመውን ጽዮናውያን ድርጅት ተቀበሉት። ቀስ በቀስ የኦሪት አማኞች ወደ እስራኤል መግባት ጀመሩ። ብዙም ሳይቆይ ልክ የአክሱም ጽዮን በምትከበርበት ኅዳር 21 ቀን 1940 ዓም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እስራኤል የምትባል አገር መሆንዋን አወቀ።

ለዚህ ለኢየሩሳሌም ነጻ መውጣት ቅድሚያ የታገሉት በሀገር ደረጃ ኢትዮጵያ ስትሆን በመሪ ደረጃ አጤ ቴዎድሮስ ናቸው። አሁን የአጤ ቴዎድሮስ ሕልማቸው ተፈታ፤ ያም ጊዜው ሲደርስ የቴዎድሮስ ልጆች ዛሬ በእስራኤል ከአንድ መቶ ሺህ በላይ ይገኛሉ።

ምንም እንኳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አልተወለደም ብለው የሚያምኑ ቢሆኑም ቤተ እስራኤላውያን ኢትዮጵያውያን የአጤ ቴዎድሮስን ሕልም ለመፍታት በእስራኤል ውስጥ ችግርን ተቋቁመው ከፍተኛ ማዕረግ የደረሱ ናቸው::

<u>ዘኢትዮጵያን ጁውሽ ኦፍ እስራኤል)</u> የሚለውን መጽሐፍ ሳነብ የአጤ ቴዎድሮስ ምኞት ተፈጸመ አልኩ:: ብዙ መቶ ሺህ ኢትዮጵያውያን በምንኖርበት አሜሪካን አገር ስንቶቻችን ነን በኢትዮጵያ ታሪክና ቅርሳቅስ የምንኮራው? ቤተ እስራኤላውያን በኢትዮጵያዊነታቸውና በቅርሳቅርሷ ኮርተው ልጆቻቸውን የሚያስተምሩአቸው በግእዝ ፊደል በአማርኛ ጭምር ነው:: ሌላም ገጠመኝ ላውጋችሁ::

የካቲት 20 ቀን 2000 ዓም ሲያትል ከአንድ ሱቅ መጽሐፍ ልገዛ ቁሜ ሳለ ሹርባ የተሠራ ወጣት ገባ:: የአማርኛ እጥረት አለበት ባለሱቋ ከዚህ በፊት አይቼህ አላውቅም እንግዳ ትመስላለህ ሲሉ ጠየቁት:: ወጣቱ ከእስራኤል የመጣ መሆኑንና እስራኤል ሳለ ወታደር አገልግሎት የጨረሰ መሆኑን ከነገረን በኋላ ባለሱቋ ታዲያ ከእስራኤል ከመጣህ ይህን ሹርባ እንዴት ልትሠራ ቻልክ ሲሉ ጠየቁት:: ወጣቱም ከተደረደሩት የታሪክ መጽሐፍ መዘዝ አድርጎ የአጤ ቴዎድሮስን ሥዕል እያሳየን "እኛ የቴዎድሮስ ልጆች ነን! ሹርባ መሠራት የብልግና ሳይሆን የጀግና ምልክት ነው" አለን::

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግሥት የኦሮሞ ሕዝብ በላቲን ይማር ብሎ ሕግ አጽድቆአል ከአገር ውጭ ያሉት ደግሞ በተለይ ቤተ እስራኤላውያን ለልጆቻቸው የግእዝን ቅርስ እንዳይረሱ በማስተማር ላይ ናቸው:: ይህም ከሆነ የአጤ ቴዎድርስን ሕልም ለመፍታት እስራኤልን ለመጠበቅና የኢትዮጵያንም አንድነት ለማስጠበቅ ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱ ለወደፊቱ ለኢትዮጵያም አለኝታ ናቸው ማለት ነው::

በእስራኤል አገር ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ወታደር ሁነው መልካም ዝና ያተረፉ መኖራቸው ከፍ ተብሎ ከተጠቀሰው መጽሐፍ ለናሙና ያህል አለፍ አለፍ እያልኩ ከብዙ ሥዕሎች ትንሾችን መርጬ ለአንባብያን አስቀምጫለሁ:: አጤ ቴዎድሮስ እስራኤልን ከቱርክ ነጻ



ለማውጣት የነበራቸው ምኞት በዓለም ላሉ ቱርኮች ወይም ደጋፊዮዎቻቸው አስፈሪ ነበር::

"ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሳ ብሎ ስም
ዓርብ ዓርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም"

የሚለው ስንኝ ዐረቦች ዓርብ ቀን ሲሰበሰቡ አጤ ቴዎድሮስ ኢየሩሳሌምን አስለቅቃለሁ እያሉ ይፈክራሉ ተብሎ ይነገራቸው ስለነበር ነው:: ለዚህም ነው የግብጹ ከሊፋ ጳጳሱን ወደ ኢትዮጵያ የላከው ታዲያ ምሥጢሩ ሳይገባው የአገሬ ደብተራና ይህ የበስማም ቄስ ሁላ ፀረ አጤ ቴዎድሮስ ቅስቀሳ ያደርግ ጀመር:: ቄሶች ገዝግዘው ገዝግዘው ጠልተው አስጠልተው የተነሡበትን ዓላማ ግብ እንዳይመታ አደረጉ::

**LEN LYONS The <u>Ethiopian Jews 0f Israel</u>** በተባለው መጽሐፍ **page 102 "about 200 Ethiopian officrs in the Israel Defense Forces. in past years, Ethiopian soldiers have been promoted to higher rank and admitted to the eliet fighting units because of their bravery and. combat skills.**

ትርጉም "በእስራኤል የመከላከያ ኃይሎች ወደ ሁለት መቶ የሚጠጉ መኮንኖች አሉ:: ባለፉት ዓመታት በትውልድ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የእስራኤል ወታደሮች ወደ ከፍተኛ ማዕረግ በማደግ በጀግንነታቸው ብውጊያ ክህሎታቸው የምርጥ ተዋጊዎች ክፍል አባል ሁነዋል::"

"ኢትዮጵያውያን በእስራኤል ውስጥ ከፍተኛ ጀብድ የሠሩ ናቸው:: ምክንያቱም እነሱ ሃይማኖቱን ይቀበሉት እንጅ በደማቸው ኢትዮጵያዊ ናቸው:: ከዚሁ መጽሐፍ ውስጥ አቶ አዲሱ የኢትዮጵያ ይሁዲዎች አጠቃላይ ድርጅት በእስራኤል ዋና አላፊ መጽሐፉን ያዘጋጁትን ጠይቀዋቸው ሲመልሱ **Adissu Mesele page 170 "There are 3,000 university students. There is a big motivation to integrate,"**ሲሉ መልሰዋል:: ከዚሁ መጽሐፍ የተለያዩ ሞያ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን በምስል አስደግፈው ጽፈዋል::

ለምሳሌ ሕፃናት የግእዝን ፊደል የአማርኛውን ቋንቋ ከኒብሩ ቋንቋ ጋር ጎን ለጎን ሲማሩ ያሳያል:: ወታደሮችን፤እንዲሁም ሠዓልያንንና

ባሕላዊ ቁሳቁስ የሚያዘጋጁትን ብሎም ቤተ እስራኤላውያን ኢትዮጵያውያን በጋብቻ የተቀላቀሉ መሆናቸውን ሕፃናቱንና ሬዲዮ ጣብያ ያላቸውን እንዲሁም ኳስ ተጨዋቹን ሌሎችንም በተለይም ካህናቱንና የኢትዮጵያውያንን ማኅበራት አስመልክቶ ሰፋ ያለ ማብራሪያ መጽሐፉ ይሰጣል:: ይህን ካልኩኝ በኋላ በእስራኤል አገር ያለው ዴር ሡልጣን ገዳም በቤተ እስራኤላውያን ክንድ ላይ የወደቀ መሆኑ ለማሳሰብ እወዳለሁ::

የእስራኤል መንግሥት የዓረቡን ዓለም በተለይ የግብጽን ጠባይ የሚመረምርበት በዴር ሡልጣን ገዳም ዙሪያ መሆኑ አይዘነጋም:: ስለዚህ ይህን ገዳም ደግሞ ባላቸው ተሰሚነት ኢትዮጵያውያን ይሁዲዎች ባለጉዳዮች ናቸው:: አንድ መገንዘብ ያለባቸው ታሪክ ቢኖር ደግሞ ይህ ገዳም የኢትዮጵያውያን የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ርስት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ይሁዲዎችና የኢትዮጵያ እስላሞችም ቅርሱ የክርስቲያኖች ነው ብለው ዝም ሊሉት አይገባም::

በተለይም የዚህ ገዳም ጉዳይ እስራኤል አገር በሚኖሩ ዘራቸው ኢትዮጵያዊ በሆኑት ትከሻ ላይ የወደቀ ነው:: ደግሜ የምለው ዋናው የታሪክ ቅርሳችን የሁላችን መሆኑን ተረዱ እላለሁ:: ታሪክ ሕያው ሁኖ ይኖራል! ለዚህም የዴር ሡልጣን ገዳም በእጃችሁ ያለ መሆኑን አሳስባለሁ:: ይህ ቦታ ከንግሥተ ነገሥታት ሳባ ጀምሮ የኢትዮጵያውያን ርስት ነው::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያሳተመው ክብረ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ ገጽ 13 "አንድ ስሙ ታምሪን የተባለ አስተዋይ የነጋዴዎች አለቃ ነበር:: አምስት መቶ ሃያ ግመሎችንም ይጭን ነበር:: ሰባ ሦስት ያህል መርከቦች ነበሩት:: ያን ጊዜ ንጉሥ ሰሎሞን የእግዚአብሔርን ቤተ ይሠራ ዘንድ ወደደ:: ነጋዴዎችም መጥተው ከእሱ ወርቅና ብር እንዲቀበሉና እሱም ከእነሱ ለሥራው የሚያሻውን እንዲቀበል"ሲል ጽፏል::

በዚህ ሰዓት ከሌሎች ነጋዴዎች ተለይተው ታምሪን ዴር ሡልጣን ላይ ዐረፉ:: እርሳቸውም የንጉሥ ሰሎሞንን ጥበብ ተመልክተው ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሱ ለንግሥተ ነገሥታት ሳባ በመንገራቸው ንግሥተ ነገሥት ሳባም ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ ከዚሁ ዴር ሡልጣን



ገዳም ከተሠራበት ቦታ ላይ ሰፍረውበታል:: ኋላም ልጃቸው ቀዳማዊ ምኒልክ እና ወንድማቸው ዛግ አባታቸውን ሊጠይቁ ሲሄዱ አብረዋቸው የመጡት መኳንንቶችም ከዚሁ ከዛሬው ዴር ሥልጣን ገዳም ከተሠራበት ቦታ ላይ ለ4 ዓመታት ሰፍረውበታል::

የኦሪት እምነት በኢትዮጵያ ከተሰበከ ጀምሮ በየመቱ ኢትዮጵያውያን ወደ ቅድስት አገር ሲሄዱ የሚያርፋበት ከዚሁ ዴር ሡልጣን ዛሬ ገዳም ከተሠራበት ቦታ ላይ ሲሆን ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ወዲህ በተለይም በ34 ዓም ግንቦት 8 ቀን በቅዱስ ጴጥሮስ ትምህርት የተማረኩት ግማሾች ኢትዮጵያውያን ከዚህ ቦታ ላይ አርፈውበታል:: ከነዚህም አንዱ በሐዋ ሥራ 8 ተጽፎ የምናገኘው ባኮስ ጃንደረባው ያረፋበት ከዚሁ ቦታ ላይ መሆኑ አይዘነጋም:: ስለዚህ ይህ ዴር ሥልጣን ገዳም ከነጋድራስ ታምሪን ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ያፈፉበት ነበር::

መኮንን ዘውዴ ኢትዮጵያ እና ኢየሩሳሌም በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 1 "ዴር ሡልጣን ገዳም የሚገኝበት ቦታ ንግሥት ማክዳ ለመጀመሪያ ጊዜ በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ የታሪክ የባለመብት ርስት የመሠረተችው ከ4490 ዓመተ ዓለም ጀምሮ መሆኑን የታሪክ ማኅደር ያስረዳል::"

"ይህ የታሪካዊ ይዞታ የቃል ኪዳን መሸጋገሪያ በመሆን ብዙዎችን ኢትዮጵያውያንን ከዓለም ክርስቲያኖች ጋር እያገናኘ የቆየ፣ በበለጠ ሲያገናኝ የኖረና የሚኖር ታላቅ መሠረት ስለሆነ በተለይ ኢትዮጵያውያን የንግሥቲቱን ታሪካዊ ምግባር ሲመሰክሩ ኖረዋል፣ ይኖራሉ" ሲሉ ጽፈዋል::

ስለዚህ በእስራኤል አገር ያላችሁ ኢትዮጵያውያን የኦሪትን ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የምትቀበሉት ታሪኩንም ጭምር መሆን አለበት:: ያ ማለት ደግሞ ዴር ሡልጣን ገዳም የናንተም ርስት በመሆኑ ግብፆችና የዓረብ ተስፋፊዎች ከኢትዮጵያውያን ቀምተው ሊወስዱ እየጣሩ ናቸው:: ታዲያ እናንተ እያላችሁ እንዴት ከኢትዮጵያውያን እጅ ሊወሰድ ይችላል::

አጤ ቴዎድሮስ ኢየሩሳሌምን ከቱርክ ቅኝ ግዛት ለማላቀቅ የነበራቸው ምኞት ሳይሳካ ቢቀርም የእርሳቸው ልጆች እነሆ

ታግላችሁ የእርሳቸውን ሕልም እንዲፈታ ስታደርጉ አንድ የቀረ መኖሩን አትርሱ። እርሱም የዴር ሡልጣን ገዳም ጉዳይ መሆኑን አትዘንጉ። ግብጾች በሀገራቸው ያሉትን ክርስቲያኖች መብት እያሳጡና እያስጨነቁ ናቸው። ነገር ግን የዴር ሡልጣን ገዳም ጉዳይ ሲነሣ እስላሞች ከክርስቲያኖች በልጠው ሲጮኹ ይሰማሉ? በዚህ በዴር ሡልጣን ገዳም ዙሪያ በሚነሣው ጭቅጭቅ ዝም ማለታችሁ ለታሪካችሁ የማታስቡ ናችሁ ብሎ ትውልድ እንዳይንቃችሁ አስቡበት።

የኦሪት አማኞች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር የምትለዩበት አዲስ ኪዳንን አለመቀበላችሁ ብቻ እንጂ በሌላው ታሪክ ከማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጋር ዘራችሁ አንድ ነው። ቅድሚያ በዚህ መተማመን ይኖርብናል። የኢትዮጵያውያን አይሁድ ከማንኛውም ክርስቲያን ሆነ እስላም ሃይማኖት አማኞች ጋር በዘርና በታሪክ አንድ መሆናችን ታሪክ ምስክር ነው። ምናልባት በዚህ ጉዳይ ላይ ራሱን ችሎ መጽሐፍ ቢጻፍበት መልካም ይመስለኛል። እኔ የሰነድ እጦት ባይኖርብኝም ቅሉ የጊዜና የቁሳቁስ እጥረት ግን ሊያራምደኝ አልቻለም።

አጤ ቴዎድሮስ ኢየሩሳሌምን ከቱርክ ነፃ ለማውጣት የነበራቸው እምነት ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን በታሪክ ግንኙነታችን በማመናቸው ነው። ምናልባት ቤተ እስራኤላውያን "ተንቀናል፤ ተሰድበናል" የሚል ሮሮ እንዳላችሁ አውቃለሁ። ነገር ግን በእናንተ በአይሁድ አማኝነታችሁ ብቻ ሳይሆን ያለው ጥላቻው በሌላው ሕዝብ እርስ በርሱ የሚናናቅ መሆኑን አትረሱትም።

ለምሳሌ ዲቃላ ከሆነ የሚባለውን አትዘንጉትም። ሌላው ቀርቶ በአጤ ቴዎድሮስ ላይ ያለውን "የኮሶ ሻጭ ልጅ ናቸው" በማለትና በሌላው ኀብረ ተሰብ ውስጥ ያለውን የንቃተ ሕሊና ገምግማችሁ ማየት ያለባችሁ ይመስለኛል። በዘር ከኢትዮጵያውያን ጋር አንድነታችሁን እናንተ ብትፍቁት ታሪክና መልካችሁ ግን ግልጽ ሁኖ ሲያሳይ ይኖራል። ለማንኛውም አንድ የታሪክ ሰነድ ጠቅሼ ይህን ምዕራፍ ብዘጋው መልካም ይመስለኛል።

በሪሁን ከበደ <u>የዋልድባ ገዳም ታሪክ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 184 "በኦሪት ሕግ ፈንታ የወንጌል ሕግ ሲተካ አንዳንዶቹ ወንጌልን



አንቀበልም፤ኦሪትን አንለቅም ብለው ሲለዩ ቤተ እሥራኤል ተባሉ። ከወንጌል በፊት የሁላችንም አባቶች ቤተ እሥራኤል ነው ይባሉ የነበሩ የሰሜኑ በተለይም በጎንደር በትግራይ በወሎና በጎጃም በሸዋ የሚኖረው የአማራው ሕዝብ ይልቁንም ጎጃም ከታናሽ ወለተ እሥራኤል ሸዋ ከአቤቶ ያዕቆብ ተወላጅ የሆነው ሁሉ ከእሥራኤል የማይወለድ የለም።"

"አሁን የአሉት ፈላሾች ቤተ እሥራኤል የተባለውን መጠሪያ የአገኙት የአባታቸውን የኦሪትን ሃይማኖት ይዘው በመቅረታቸው ነው እንጂ ከኛ አባቶች የተለየ የእሥራኤል ትውልድ ኑሮአቸው አይደለም። እነዚህ አሁን የአሉት ቤተ እሥራኤሎች ወይም ፈላሾች በደም ጥልቀት በሥጋ ልደት የማይለዩን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል። ከአለባበስ ጀምሮ እስከ አበላል አልፎም ክርስትና ሃይማኖት እኛ ብንቀበልም በብዛት ከኦሪት ሃይማኖት ጋር የተቆራኘን መሆናችን ብዙዎቹ የረሱት ይመስላሉ። በእርግጥ ብዙዎቹ ያውቃሉ አይክዱም።

SHMUEL AVRAHAM <u>MY ESCAPE FROM ETHIOPIA</u> በተባለው መጽሐፋቸው page 6 Even today;s Ethiopian Christians acept the fact that Judaism was once the official relion of the land precisely because of those strong Jewish root;s Ethiopian Christan practices are stil more Jewish than the practices of other Christian sects. ሲሉ ጽፈዋል።

አንድነታችን ሃይማኖታችን በዚህ መልክ መግለጽና ማቀራረብ ሲቻል ኢየሩሳሌም ያሉ የአይሁድ ቄስ ኢትዮጵያዊ ሲሰብኩ "እባካችሁ ወደ ኢትዮጵያ ሂዳችሁ ክርስቲያኖችን እያመጣችሁ ኢየሩሳሌምን አታርክሱ"ሲሉ ተናገሩ። ይህ ንግግር ትክክል አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስቲያን ቢሆንም የእሥራኤል አምላክ ብሎ እንጂ የኢትዮጵያ አምላክ አይልም።

ዶ/ር ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል <u>በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ</u> ትርጉም በግእዝ ቋንቋ በተባለው መጣጥፋቸው ገጽ 12 "ኢትዮጵያ ከእሥራኤል ጋር የነበሯት እነዚህ የበዙ የቅርብ ግንኙነቶች በተለይም በሃይማኖትና በባህል መስከ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በመላው

የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ የአኗኗር ሥርዓት ውስጥ ሥር ሰደው በኖሩ የአይሁድ ወይም አይሁድ መሰል ልማዶች ሊረጋገጡ ይችላሉ:: እነዚህም ልማዶች እንደ ቅዳሜ አከባበር በምግብ አጠቃቀም ረገድ ንጹሕ ባልሆነ እንስሳት መካከል ያለው ልዩነትን ሥርታዊ ንጹሕና እና የግዝረት ሥርዓቶች ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል::

ስለዚህ አንድነታችን ለመበጠስ አትሞክሩ:: ይሁዳውያን በዓለም ላይ ያሉት የነበረባቸውን ችግር ከእኛ ከኢትዮጵያውያን ጋር ስናወዳድረው በኢትጵያ የነበሩት ዛሬም ያሉት ሰላም ኗሪ ናቸው ማለት ይቻላል። የሮማ ቤተ ክርስቲያንና አውሮፓውያን በኢትዮጵያ ከነበሩት ክርስቲያኖች በላይ ጨክነውባቸው ነበር::

ለምሳሌ እንግሊዝ አገር በ1290 ዓም ሕግ አይሁዳዊ በእንግሊዝ ምድር እንዳይኖር ከልክላ ነበር። ይህ ሕግ 200 ዓመታት በላይ ጸንቶ በመቆየት የእንግሊዝ ፀረ ይሁዳ አቋም አንፀባርቃለች። እንግሊዝ ብቻ ሳትሆን በሌሎች አውሮፓ አገሮች በራሽያ የአይሁድ ሕዝብ የነበረበት ግፍ በሌሎችም አውሮፓ አገሮች የነበረውን ታሪክ ስንመረምና አሁን ትናትና በጀርመን የደረሰባቸውን የጥፋት ዘመቻ ታሪክ አምጥተን ከኢትዮጵያ ጋር ስናወዳድር ቀሎ እናገኘዋለን::

እንዲያውም ኢትዮጵያውያን ሰሜን ተራራ ተጠግተው የራሳቸው ንጉሥ አንግሠው ይተዳደሩ የነበሩ ናቸው:: ንጉሥ መሆን ብቻ ሳይሆን ለ42 ዓመታት ንግሥት ዮዲት ኢትዮጵያን መርተዋል:: መጥፎውን ብቻ ሳይሆን ደጉንም ማንሳቱ መልካም ይመስለኛል:: ስለዚህ እናንተ የኦሪት አማኞች ሆናችሁ በግቢ ወደ ኢየሩሳሌም የሚሄዱት ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ትእዛዝ የተወሰነ ነው::

<u>ኢሳ 11፤10</u> "በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል፤የቀረውን የሕዝቡን ቅሬታ ከአሦርና ከግብፅ፤ከጳትሮስና ከኢትዮጵያ፤ከኤላምና ከሰናዖር፣ ከሐማትም ደሴቶች ይመልስ ዘንድ ጌታ እንደገና እጁን ይገልጣል:: ለአሕዛብም ምልክትን ያቆማል:: ከእሥራኤልም የተጣሉትን ይሰበስባል:: ከይሁዳም የተበተኑትን ከአራቱ የምድር ማዕዘኖች ያከማቻል" ብሎ በጻፈው መሠረት ኢትዮጵያውያን ሆኑ ሌሎች አይሁድ ወደ እሥራኤል መሰባሰባቸው የአምላክ ትእዛዝ ነው:: ስለዚህ በዘር አንድ ከሆን በታሪክም አንድ ነንና በሚያለያየን ነገር ብቻ ሳይሆን በሚያገናኘን ነገር ላይ ተግባብተን ታሪካችን እንጠብቅ ዘንድ አሳስባለሁ::



# ምዕራፍ 10

## አዳሪ ትምህርት ቤት ጀመሩ!

<u>የአጤ ቴዎድሮስ</u> ደብዳቤ ለአባ ሳሙኤል "ዛቲ መልእክት ዘተፈነወት እምሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ትብጻሕ ኀበ ጳጳስ እንግሊዝ ዘኢየሩሳሌም ሳሙኤል ጉባ። እጅጉን እንዴት አለህ:: ከክራፍን ከመርጢን ፍላጥ የሰደድህልኝ ወረቀት ደረሰኝ፥ እኔን በመጠየቅህ ደስ አለኝ። እነዚኽን ግን ቢኖሩ ጠብቅልኝ ቢመጡም ጠብቀህ ስደድልኝ ያልኸኝን ሰዎች እንሄዳለን ቢሉኝ በፍቅር ተቀብዬ በፍቅር ሰደድኋቸው::"

"ሠራተኞችን ግን እሰድልሃለሁ በማለትህ ደስ ብሎኛልና ስደድልኝ:: ነገር ግን የሀገራችነን ነገር ታውቀው አለህ የነበርህበት ነው:: እርስ በእርሱ እንኳ ከሦስት ተከፍሎ ነበር:: አሁን በእግዚአብሔር ኃይል አንድ አድርጌዋለሁና ሃይማኖት የሚከፋፍሉ ቀሳውስት አይምጡብኝ:: ፍቅራችን እንዳይጎድል:: ከዚህ ቀደም አባ ያዕቆብ የሚሉት እንደ ገና ክርስትና አንሥቶ ዲቁና ቅስና ሰጥቶ ብዙ ሀገር አፋልሶ ነበር::"

"በእግዚአብሔር ኃይል አስለቅቄ ሰደድሁት:: ሌላ ግን ቢመጣ በፍቅር ተቀብዬ በፍቅር እሰዳለሁ የሚኖረውንም ደስ አሰኝቼ አኖረው አለሁ:: ከሠራተኞች ግን አንዱ በእሳት መዘወር የሚያርስ ከነመዘወሩ ይዞልኝ ይምጣ አለ ሲሉ ሰምቼአለሁ አንተም ጠይቀኝ እኔም አስጠይቅሃለሁ:: ለእግዚአብሔር ደስ ይበለው ብዬ ባርያ አይሸጥ ብዬ 3 ዓመት አዋጅ ነግሬ ከልክዬው አለሁ" ሲሉ አጤ ቴዎድሮስ ለአቡነ ሳሙኤል ደብዳቤ ጽፈው ነበር::

ደብዳቤው የሚያመለክተው "ሠራተኞችን ግን እሰድልሃለሁ በማለትህ ደስ ብሎኛልና ስደድልኝ" የሚለው አጤ ቴዎድሮስ የጥበብ ሰዎችን ለማግኘት የነበራቸውን ጥረት ከዚህ ደብዳቤያቸው መረዳት ይቻላል:: አስተማሪ እንዲልኩላቸው መማጸናቸው የግል ጥቅም ሳይሆን ለአገራቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም እንዲሆን አስበው ስለ ነበር ነው::

ካልተማሩ አያውቁ
ካላወቁ አይራቀቁ
መማር አበባ ነው
ማስተማር ፍሬ ነው።

"ማስተማር ፍሬ ነው" የሚለውን መፈክር በመያዝ እንደነገሡ ጀምሮ ኢትዮጵያውያንን አንብቦ መረዳትና ጽፎ ማስረዳት እንዲቻል አንዳንድ መልካም አሳቢ ደብተራዎችን በመሰብሰብ ቅድሚያ በጋፋት አዳሪ ትምህርት ቤት ከፈቱ። በዚህ ትምህርት ቤት ከጎንደርና ከትግሬ ከወሎና ከጎጃም የተወሰኑ ልጆች በአዳሪ ተማሪነት ጀምረው መልካም ውጤት ማስመዝገባቸው አይዘነጋም። ከዚህ ትምህርት ቤት ቅድሚያ ከጀመሩት ተማሪዎች መካከል ኋላ በአጤ ምኒልክ ዘመን የኢየሩሳሌምን ገዳም ጭቅጭቅ ለመፍታት ዴር ሡልጣን ገዳምን በተመለከተ ለመደራደር ለድፕሎማሲ ሥራ ቱርክ ከሄዱት መካከል ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ አንዱ ናቸው።

ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ ሕንድ አገር ተምረው የተመለሱ ናቸው። ደጃዝማች መሼሻ ወርቄ ብዙ ቋንቋ አዋቂ በመሆናቸው 4ኛው አጤ ዮሐንስ ለራስ ዳርጌ በጻፉት ደብዳቤ "የዓለምን ቋንቋ አውቆ የሰይጣንን ቋንቋ ለማወቅ ጥረት የሚያደርገው ያ በጌምድሬ ደጃዝማች መሼሻ ወርቄ በሕይዎት እያለ እኔ በመንግሥቴ አልኖርም" ሲሉ በ1881 ዓም ጽፈዋል። ደጃዝማች መሼሻ ወርቄ በ4ኛው አጤ ዮሐንስ የተጠሉት የተማሩ በመሆናቸው እንጂ አጤ ዮሐንስን የበደሉአቸው ኑሮ አይደለም።

ወደ ነበርኩበት ልመለስና አጤ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን አንድነት ለመመሥረት ሲጥሩ የተማረ የሰው ኃይል እንደሚያስፈልጋቸው ተረድተዋል። ለዚህም የተማረ ኃይል ለአገር እድገት ጠቃሚ መሆኑን ተረዱ። ቅድሚያ በአገራቸው ውስጥ ልጃቸውንና የመኳንንት ልጆችን ሰብስበው በአንድ እንዲማሩ አድርገዋል። ይህን የቤተ መንግሥት አስተዳደር እና ሥርዓት እንዲማሩ ከተደረጉት መካከል 3ቱ ኢትዮጵያን መርተዋል።

3ኛው አጤ ተክለ ጊዮርጊስ፣4ኛው አጤ ዮሐንስና 2ኛው አጤ ምኒልክ አጤ ቴዎድሮስ በአንድ ላይ ከሌሎች የመኳንንት ልጆችና



ከልጃቸው ከራስ መሸሻ፣ ከደጃዝማች ጥሶ ጎበዜና ኋላ በአጤ ምኒልክ ዘመን ልዑል ራስ መንገሻ አትኬም ቅድሚያ በአጤ ቴዎድሮስ ከቤተ መንግሥታቸውና ኋላም ማኅበረ ሥላሴ ገዳም ያስተማሩአቸው መሆኑን ታሪክ ዘግቦታል።

<u>አደራ መጽሔት</u> ቅጽ 1 ቁጥር 1/1985 ዓም ገጽ11 "በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን አዳሪ ትምህርት ቤት በጋፋት ከፍቶ ማስተማሩን ቀጠለ። ይህንንም ንባብ፣ጽሕፈት፣ሂሣብና፣ጅኦግራፊና ታሪክ የሚማሩ ጥቂት ተማሪዎች ነበሩበት። ማንኛውም ነገር ፈጥነው በመረዳት ችሎታቸው በጣም ይደነቅ ነበር በማለት ዋልድሚዬር በራሱ አባባል ገልጾታል" ሲሉ መጽሔቱ ጽፏል።

አጤ ቴዎድሮስ ለትምህርት ከፍተኛ ፍቅር ስለነበራቸው ኢትዮጵያውያን እንዲማሩ ይፈልጉ ነበር። ለዚህም የትምህርትን ጥቅም ከአጤ ቴዎድሮስ የተማሩት አጤ ምኒልክ ለኢትዮጵያውያን መብራት ሁነዋል። ዛሬ አንዳንድ ተምረው ያልተመራመሩ አጤ ምኒልክን ቢሳደቡም ታሪክ ግን ለኢትዮጵያውያን የታገሉ መሆናቸውን ነው የሚመሰክረው። ለዚህም እርሳቸው በልጅነታቸው የተማሩት ትምህርት ነው የረዳቸው።

<u>አጤ ቴዎድሮስ</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 144 "በዚህ ቤት ሙሉ ወርቅ ብትሰጠኝ ጥቅሙ ምንድነው? እምመኘው ጥበብን ነው። ቅጣት የማበዛው አገሬ በሥርዓት እንድትተዳደር ለማድረግ ነው" ብለው መናገራቸውን አቶ ጳውሎስ ኞኞ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ሥርዓትና ትምህርት ለማስተማር ጥረት ሲያደርጉ ምድረ መሳፍንት እንቅፋት ቢሆኑባቸውም ጅምራቸው ተስፋፍቶ ብዙ ልጆች አውሮፓ ሊማሩ ወጥተው ነበር። በእርሳቸው ዘመን ኢየሩሳሌምና አውሮፓ ሕደው የተማሩ ብዙ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በእርሳቸው ዘመን ለትምህርት ወጥተው ተምረው የተመለሱት ግን ደጃዝማች መሸሻ ወርቄና እስከአሁን ድረስ ስሙ ያልታወቀው ጀርመን ሀዶ ፍልስፍና ተምሮ የመጣው ናቸው ሊያዩት ያልፈለጉት የተማረው ፍልስፍና በመሆኑ ነው።

ደጃዝማች መሸሻ ወርቄም አጤ ቴዎድሮስ የፈለጉትን ተምረው ባለመምጣታቸው መልካም አቀባበል አልተደረገላቸውም። ለዚህም

ነው አጤ ምኒልክ ከመቅደላ ሲያመልጡ አብረው ሸዋ ሄዱ። ሌሎች ከላይ እንደተጠቀሰው በጋፋት የተማሩ ውጭ አገር ሕደዋል። በእርሳቸው ዘመን ውጭ የወጡ በአጤ ምኒልክ ዘመን ወደ አገራቸው ከተመለሱት መካከል ከንቲባ ገብሩ አንዱ ናቸው።

ከንቲባ ገብሩ ኢትዮጵያ አሜሪካ ጋር በጉዳይ ፈጻሚነት መጀመሪያ ብላቴን ጌታ ሕሩይ ወልደ ሥላሴ ሲመጡ አስተርጓሚ ሁነው መምጣታቸውን ልጃቸው ኮሎኔል ዳዊት ገብሩ ጽፈዋል። እኒህ በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ውጭ የወጡ ከንቲባ ገብሩ የጎንደር ከንቲባም ነበሩ። በነገራችን ላይ የከንቲባ ገብሩ ልጃቸው ወይዘሮ ስንዱ ገብሩ የመጀመሪያ ሴት የምክር ቤት አባል የነበሩ ሲሆኑ ልጃቸው የወያኔ ኢሕአዴግ አምባሳደር በዋሽንግተን ዲሲ የነበሩት ሊቅ ዶ/ር ሳሙኤል ናቸው። ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ውጭ አገር ወጥተው ተምረው የተመለሱ ናቸው።

አማከለ ገበየሁ <u>ቅድስት አገር</u> በተባለው መጽሐፋቸው ገጽ 269 "ደጃዝማች መሼሻ ወርቄ በ1895 በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ተልከው ከቱርክ ባለ ሥልጣን አብደል ሐሚድ ጋር በመነጋገር የዴር ሡልጣንን ገዳም ቁልፍ ለማስመለስ ብዙ የደከሙ ባለውለታችን ናቸው" ሲሉ ጽፈዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት ወጭውን መድቦ አዳሪ ትምህርት ቤት ከፍቶ ወጣቱ ይማር ያሉ አጤ ቴዎድሮስ ነበሩ። ከእርሳቸው በፊት የነበረው የአብነት ትምህርት ቤት መምህራን ያለ ደመወዝ እየተራቡ ያስተምሩ ነበር።

ሕዝቡ እስላም ክርስቲያን ሳይል ከትምህርት ቤት የዋሉትን ተማሪዎች ማታ ራታቸውን ለማግኘት ደበሎ ደርበው አኮፋዳ በክንዳቸው አንጠልጥለው ረጃጅም ዘንጎች ይዘው መንደር ለመንደር "በእንተ ስማ ለማርያም ስለ እመብርሃን ብለው" እያሉ ለምነው ያገኙትን ቁራሽ ይዘው ወደ ማደሪያቸው ይሄዱ ነበር።

እንግዲህ ይህን ትምህርት ቤት አዳሪ ትምህርት ቤት ብለን ከጠራነው የመንግሥት ትምህርት ቤት ሳይሆን የሕዝብ ትምህርት ቤት ማለት ነው። አጤ ቴዎድሮስ ያን ያህል ጦርነት እየወረደባቸው ወጣቱን ለማስተማር ከፍተኛ የሆነ ጥረት አድርገዋል። ኢትዮጵያውያን አንዳንድ መልካም አሳቢ ደብተራዎች ብቻ ሳይሆን



ከውጭ አገር ለስለላ የመጡ ፈረንጆች ሳይቀሩ እንዳስተማሩ አይዘነጋም።

ኮሎኔል ዳዊት ገብሩ <u>ከንቲባ ገብሩ ደስታ የኢትዮጵያ ቅርስ</u> በተባለው መጽሐፍ ገጽ 28-30 የሚያትቱ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ውጭ አገር ሂደው የተማሩ መሆናቸውን ገጽ 29 "በሺህ ስምንት መቶ አምሣዎቹ ዓመታት በስዊስ አገር ይማሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ገብሩ ደስታ፤ ሚካኤል አረጋዊ፥ ኃይሉ ወሰን፤ እንግዳሸት ሺምፐር፥ሰንበቱ ዳንኤል፤አረጋጂ ማህሉ እና ሠመረ ዳንኤል"ሲሉ ጽፈዋል።

አጤ ቴዎድሮስ ቅድሚያ ደብረ ታቦር የንባብ ትምህርት እንዲማሩ ካደረጉ በኋላ ወደ ውጭ አገር ተምረው እንዲመጡ ልከዋቸዋል። አቶ ጳውሎስ ኞኞ አጤ ቴዎድሮስ በተባለው መጽሐፋቸው ሲገልጡ ጀርመን ሂዶ ፍልስፍና ተምሮ በመምጣቱ አጤ ቴዎድሮስ ምን ተምሮ እንደመጣ ሲጠይቁት "ፍልስፍና" በማለቱ ተቆጥተው ከአካባቢያቸው እንዲርቅ አድርገውታል በማለት" ጽፈዋል።

እነዚህ ተማሪዎች ሚካኤል አረጋዊ የደንቢያ አሪት አማኝ የነበሩ ሲሆን ኋላ የሚሲዮን ሃይማኖት ተቀብለው ሲኖሩ አውሮፓ ከጀርመን ወደ ስውዲን ሲሄዱ ባቡር አምልጦአቸው ከባቡር ጣቢያው ከዘበኛው ጋር ሲያድሩ ባንድ ቀን አስተምሮ ክርስትና ሃይማኖት እንዲያምን ያደረገ ሲሆን በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ አማርኛ ሲተረጎም አንዱ ተርጓሚ እንደነበሩ ታሪክ አይረሳቸውም።

ገብሩ ደስታ ኋላ ከንቲባ ገብሩ የተባሉት የወይዘሮ ስንዱ ገብሩ አባት አጤ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያውያን አውሮፓ ሂደው ተምረው እንዲመለሱ የሚፈልጉት የቀለም ትምህርት ሳይሆን ብረታብረት መሥራት ተምረው እንዲመጡ ይመኙ ነበር። አንጥረኛው ብልሃተኛው በዝቶ መድፍ ተሠርቶላቸው ኢየሩሳሌምን ከቱርክ ነጻ አውጥተው የኢትዮጵያን ዳር ደንበር አስጠብቀው ነበር ሕልማቸው። በጥሞና ስትመለከቱት የአጤ ቴዎድሮስ ምኞት እንኳን በዚያን ጊዜ ዛሬም ብረታብረት ተምሮ ወደ አገሩ የተመለሰ የለም።